የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን

ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች ረቂቅ መመሪያ

መመሪያ ቁጥር....../2017

ማውጫ

መግቢያ 8

ምዕራፍ አንድ፡ ጠቅላላ ድንጋጌዎች 9

1. አጭር ርዕስ 9
2. ትርጓሜ 9
3. የተፈጻሚነት ወሰን 13

ምዕራፍ ሁለት፣ የፈንዱ መስፈርቶች 13

4. የፈንዱ የሕግ ቅርጽ 13
5. አስፈላጊ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች 14
6. የኢንቨስትመንት ፖሊሲ 14

ምዕራፍ ሦስት፣ የፈንድ ዓይነቶች 16

ክፍል 1፡ ጠቅላላ 16

7. በባለስልጣኑ የሚመዘገቡ የፈንድ ዓይነቶች 16
8. የህዝብ ገንዘብ ገበያ ፈንድ መስፈርቶች 16
9. የህዝብ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ መስፈርቶች 17
10. የህዝብ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ 17
11. የአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ መስፈርቶች 18
12. የልዩ ስያሜ መስፈርቶች 18
13. የፈንድ ፖርትፎሊዮ መስፈርቶች 19
14. ተፈጻሚ የሚሆኑ የብድር ገደቦች 20
15. በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማበድር ላይ የተጣሉ ገደቦች 20
16. በፈንዱ ሃብቶች ላይ የተጣሉ ገደቦች 20
17. የተከለከሉ ዋስትናዎች እና ካሳዎች 20

ክፍል 2፡ የገንዘብ ገበያ ፈንድ 20

18. የገንዘብ ገበያ ፈንድ መስፈርቶች 20
19. የገንዘብ ገበያ ፈንድ የፖርትፎሊዮ ስብጥር መስፈርቶች 21

ክፍል 3፡ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ 21

20. የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ መስፈርቶች 21

21. የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ ፖርትፎሊዮ ስብጥር መስፈርቶች 21
ክፍል 4: የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ 22
22. ወሰን እና ገደቦች 22
23. የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ፖርትፎሊዮ ስብጥር መስፈርቶች 22
24. በሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ የአከናዋኙ ሚና እና ኃላፊነት 23
25. የሪል ስቴት ንብረት አስተዳዳሪ ሹመት 23
26. የንብረት አስተዳዳሪው ሚና 24
27. የንብረት አስተዳዳሪውን ስለመለወጥ 25
28. በሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንዱ ውስጥ የጠባቂው ሚና እና ኃላፊነት 25
29. ስለ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንዱ አስተዳደር 26
30. የሪል ስቴት መረጃን ይፋ ስለማድረግ 26
31. የሪል ስቴት ግመታ ሪፖርት 26
ክፍል 5፡ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንዶች 27
32. ወሰን እና ገደቦች 27
33. በንብረት ኢንቨስትመንት ላይ ኢንቨስት ስለሚያደርግ አማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ 27
34. በአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ በቋሚነት መረጃን ይፋ ስለማድረግ 28
ምዕራፍ አራት፣ ምዝገባ 28
ክፍል 1 ፡ የፈንድ ምዝገባ 28
35. ክልከላ 28
36. የምዝገባ ማመልከቻ አቀራረብ 29
37. የማመልከቻ ቅጽ 29
38. የማመልከቻ ደጋፊ ሰነዶች 31
39. የማመልከቻው ሂደት 32
40. የምዝገባ ማመልከቻው መጽደቅ 33
41. የማመልከቻው ውድቅ መደረግ 33
ክፍል 2: ምዝገባ የሚያስፈልጋቸው የፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮች 34
42. ተፈፃሚነት 34

43. የክፍልፋዮች የምዝገባ መግለጫ 34
44. በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች 35
45. የፈንዱ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ቅርጽ እና ይዘት 36
46. የፈንዱ ይፋ የማድረግ መስፈርቶች 36
47. ፈንዱን የተመለከተ ዝርዝር መረጃ 37
48. ኢንቨስትመንት ፖሊሲውን የተመለከተ መረጃ 38
49. ስለ ፈንዱ የድርሻ ክፍልፋዮች መረጃ 39
50. የትርፍ ክፍፍል ፖሊሲ 39
51. ስለ ፈንድ አከናዋኙ ዝርዝር መረጃ 40
52. ስለ ጥበቃ አደረጃጀት ዝርዝር መረጃ 40
53. የፈንዱ ቦርድ 41
54. ከፈንዱ ፖርትፎሊዮ ላይ ስለሚከፈሉ ክፍያዎች 41
55. ሌሎች ወሳኝ መረጃዎች 42
56. ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነድ 42
ክፍል 3፡ ከምዝገባ ነጻ የተደረጉ የፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮች 43
57. ከምዝገባ ነጻ የተደረጉ የአማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ አቅርቦት 43
58. ከምዝገባ ነጻ ለሆኑ ሽያጮች የኢንቨስተር መረጃ 44
59. የግዥ ቃልኪዳን ስምምነቱ ይዘት 45
ክፍል 4፡ የውጭ ፈንዶችን ስለመመዝገብ 45
60. የውጭ ፈንዶችን የሚመዘገቡበት ተጨማሪ መስፈርቶች 45
61. የውጪ ፈንድ አስተዳደር እና አመራር 46
62. ማስታወቂያዎች 46
63. በማስታወቂያዎች ላይ የአከናዋኙ ኃላፊነት 47
ምዕራፍ አምስት፣ ባለሞያ አካላት 47
ክፍል 1፣ አከናዋኝ 47
64. የአከናዋኝነት ውል 47
65. የአከናዋኙ በፈንዱ ዉስጥ ስለሚኖረው ድርሻ 47
66. የአከናዋኝ ኃላፊነቶች 47

67. ስለ አከናዋኙ ምግባር 48
68. የተገቹነት ዝግጅት 49
69. የአከናዋኙ የሥጋት አስተዳደር ግዴታዎች 50
70. የአከናዋኙ መረጃ የመስጠት ግዴታ 50
71. አከናዋኙ ሪኮርዶችን መያዝ ያለበት ስለመሆኑ 51
72. አከናዋኙ ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ 51
73. አከናዋኙ ስራዎችን በውል ለሦስተኛ ወገን አሸጋግሮ ስለማሠራት 51
74. የአከናዋኙ ከሥራ ስለመልቀቅ 52
75. አከናዋኙን ስለማሰናበት 52
76. አከናዋኙ ከሥራ ከለቀቀ ወይም ከተሰናበተ በኋላ ስለሚኖሩበት ግዴታዎች 53
77. አዲስ አከናዋኝ ስለመሾም 53
ክፍል 2፣ የፈንዱ ጠባቂ 53
78. የፈንዱ ጠባቂ ለመሆን የሚያስፈልግ ብቁነት 53
79. የጠባቂነት ስምምነት 54
80. የጠባቂው ኃላፊነቶች 54
81. የፈንድ ጠባቂው የጥበቃ ግዴታ 55
82. የጠባቂነት ስራዎችን በውል ለሦስተኛ ወገን አሸጋግሮ ስለማሠራት 56
83. የጠባቂው ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ 56
84. የጠባቂው ከሥራ መልቀቅ እና መተካት 57
85. ጠባቂውን ስለማሰናበት 57
ክፍል 3፣ ሌሎች ባለሞያ አካላት 58
86. የሌሎች ባለሞያ አካላት ሹመት 58
87. የውጭ ኦዲተሮች 58
88. የሸሪዓ አማካሪ 58
89. የአማካሪዎች ከሥራ መሰናበት ወይም መልቀቅ 59
ክፍል 4፣ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች 59
90. ክፍያዎችና ወጭዎች 59
ምዕራፍ ስድስት ፣ አስተዳደር 60

ክፍል 1፣ ፈንዱን ስለመቆጣጠር 60
91. የዳይሬክተሮች ቦርድ 60
92. የቦርዱ ሚና 61
93. የቦርድ ኮሚቴዎች 62
94. የጥቅም ግጭቶች 62
ክፍል 2፣ የአሰራር ሁኔታ 63
95. በፈንዱ ላይ የሚደረጉ ለውጦችን በክፍልፋይ ያዦች ስለማፅደቅ 63
96. የክፍልፋይ ያዦች ጉባዔ 64
ምዕራፍ ሰባት፣ በቋሚነት መረጃን ይፋ ስለማድረግ 64
ክፍል 1 ፡ ጠቅላላ ግዴታዎች 64
97. ተፈጻሚነት 64
98. መስፈርቶች 65
99. ወዲያው ይፋ መደረግ ያለባቸው መረጃዎች 65
ክፍል 2፣ ወቅታዊ መረጃን ይፋ ስለማድረግ 65
100. ወቅታዊ መረጃን ይፋ የማድረግ መስፈርቶች 65
101. በወቅታዊነት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ይዘት 66
102. የተዛማጅ ወገን ግብይቶችን ይፋ ስለማድረግ 67
103. የግማሽ ዓመት ሪፖርት 67
104. ዓመታዊ ሪፖርት 68
ክፍል 3 ፣ ከባለሙያ ወገኖች ስለሚቀርቡ ሪፖርቶች 68
105. የአከናዋኙ ሪፖርት 68
106. የጠባቂው ሪፖርት 69
107. ከሌሎች ባለሞያ አካላት ስለሚቀርቡ ሪፖርቶች 69
ክፍል 4፣ የፈንዱ አፈጻጸም ሪፖርት 70
108. ከአፈጻጸም ጋር የተገናኙ መረጃዎች 70
109. የአፈጻጸም ምዘና ሪፖርት 70
110. አፈጻጸም ስለሚሰላባቸው ዘዴዎች 71
ክፍል 5 ፣ የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ዋጋ ግመታ 72

111. የዋጋ ግመታ ሪፖርት 72
112. የዋጋ ግመታ መረሆዎች፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች 72
ምዕራፍ ስምንት፡ ስለ መዋሃድ፣ ለቁጥጥር የሚያበቃ የክፍልፋዮች ግዢ እና ስለመፍረስ 73
113. ስለመዋሃድ፣ ለቁጥጥር የሚያበቃ የክፍልፋዮች ግዢ እና ሌሎች አይነት ጥምረቶች 73
114. የፈንዱ መፍረስ 74
115. የሂሳብ አያያዝ እና ሪፖርቶች 74
116. የመጨረሻ ሪፖርት 75
ምዕራፍ ዘጠኝ፣ ተገዥነት፣ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ህግ ማስፈጸም 75
ክፍል 1፣ ጠቅላላ 75
117. የህግ ተገዥነት ሪፖርት 75
118. አስተዳደራዊ እርምጃዎች 76
ክፍል 2፣ ቅጣቶች፣ የገንዘብ መቀጮዎች እና ሌሎች ሕግ የማስከበር ተግባራት 76
119. ያልተፈቀደ ህትመት 76
120. ያልተፈቀዱ ተግባራት 77
121. ለህዝብ ሽያጭ የሚቀርቡ የፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮች ጋር የተያያዙ ሰነዶችን አዘግይቶ ማቅረብ 78
122. በቀጣይነት ይፋ መደረግ ያለባቸውን መረጃዎች አዘግይቶ ይፋ ማድረግ 79
123. የአከናዋኝ ግዴታዎችን አለመዎጣት 79
124. ሌሎች ጥሰቶች 79
ምዕራፍ አስር፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 79
125. አለመግባባቶችን ስለመፍታት 79
126. ተፈጻሚ አለማድረግ 80
127. ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች 80
128. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ 80

መግቢያ

የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶችን የካፒታል ገበያ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር በመሆኑ፣

አዋጁ ከጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ጋር በተያያዘ በመመሪያ ሊወሰኑ የሚገባቸውን ጉዳዮች የዘረዘረ በመሆኑ፣

ለኢንቨስተሮች ጥበቃ በማድረግ የገበያውን ፍትሐዊነት፣ ታማኝነትና ቅልጥፍና እያረጋገጠ ካፒታልን ለማንቀሳቀስ፣ የፋይናንስ ፈጠራን ለማስፋፋት እንዲሁም የኢንቨስትመንት የአደጋ ስጋቶችን ለመጋራት የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀፅ 86(4)፣ 87(1)፣ 90(3) እና 108 ድንጋጌዎች መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ምዕራፍ አንድ፡ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ መመሪያ፣ ቁ. …./2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ነው።
2) **"አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ"** ማለት ከምዝገባ ነጻ በተደረገ አቅርቦት የተቋቋመ ፈንድ ነው።
3) **"ቅርበት ያለው ሰው"** ማለት ሀ) የሰውን ወይም የድርጅቱን አምስት በመቶ (5%) ወይም ከዚያ በላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የያዘ፣ ቁጥጥር ወይም የባለቤትነት ጥቅም ያለው ማንኛውም ሰው፣ ለ) ይህ ሰው አባል የሆነበት ማንኛውም ድርጅት፣ ወይም ሐ) ቅርበት ያላቸው ሰዎቻቸውን ጨምሮ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ቁልፍ ስራ አስፈጻሚዎች ነው።
4) **"ግመታ"** ማለት በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አንቀጽ 2(2) መሰረት የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።
5) **"ቦርድ"** ማለት የአክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም እንደ ሁኔታው ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር የቁጥጥር ስራ የሚሰራ አቻ አካል ነው።
6) **"የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት"** ማለት ፈንዱ ሲመዘገብ በባለስልጣኑ የሚሰጥ ህጋዊ ሰነድ ነው።
7) **"የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የምዝገባ የምስክር ወረቀት"** ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ ማቅረቢያና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 2(10) ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።
8) **"የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት"** ማለት በንግድ ሕጉ፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እንዲሁም ማሻሻያዎች ወይም ህጉን ተከትለው የሚወጡ ሌሎች ሕጎች መሠረት የንግድ ድርጅትን ሕጋዊ ሕልውና እና ምዝገባ ለማረጋገጥ በኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጥ ሕጋዊ ሰነድ ነው።
9) **"ሰነድ ማረጋገጥ"** ማለት የአንድን ድርጅት ሰነዶች እውነተኝነት ለማረጋገጥ ፊርማ እና ማህተም ባረፈበት ደብዳቤ በድርጅቱ የሚፈጸም የማረጋገጥ ተግባር ነው።

10) **“የንግድ ሕግ”** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 እንዲሁም ማሻሻያዎች ወይም ህጉን ተከትለው የሚወጡ ሌሎች ህጎች ነው።

11) **“አግባብነት ያላቸው የገንዘብ ሰነዶች"** ማለት ባላቸው አሰራር መሰረት በተወሰነ የጊዜ ሂደት ውስጥ ወደ ገንዘብ ሊቀየሩ የሚችሉ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ፣ የገንዘብ ፍሰት ወይም ሌሎች የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችትን ሳይጨምር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ ወጭ ማድረጊያ ጊዜ የተበጀለት ተቀማጭ፣ የአጭር ጊዜ የመንግስት የግምጃ ቤት ሰነዶች እና የንግድ ወረቀት ነው።

12) **"የማቋቋሚያ ሰነዶች"** ማለት የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ መመስረትን፣ አወቃቀርን እና አሠራርን የሚመለከቱ ህጋዊ ሰነዶች ማለት ሲሆን በውስጡም እንደ አግባብነቱ የፈንዱን የኢንቨስትመንት ፖሊሲ፣ መመስረቻ ጽሁፍ፣ የሽያጭ አቅርቦት ሰነዶች፣ የአከናዋኝ ስምምነት፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጠባቂ ስምምነት እና ሌሎች ተያያዥ ስምምነቶች እንዲሁም ውስጠ ደንብን ያጠቃልላል።

13) **“ከምዝገባ ነጻ የተደረገ አቅርቦት”** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት በግል ሽያጭ እና ለብቁ ኢንቨስቶሮች የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ነው።

14) **“የውጪ ኦዲተር”** ማለት ስልጣን ባለው አካል የኦዲት አገልግሎት እንዲሰጥ ፍቃድ የተሰጠው እና በባለስልጣኑ የጸደቀ ኦዲተር ነው።

15) **"የብቁ እና ተገቢነት መመዘኛዎች"** የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አንቀጽ 16 ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

16) **"የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች"** ማለት ወቅታዊ ወለድን የሚከፍሉ ወይም የማይከፍሉ የገንዘብ ሰነዶች ሆነው የታወቀ የመክፈያ ጊዜ ያላቸው እና ዋና ክፍያው የእዳ መክፈያ ጊዜው ላይ የሚከፈልባቸው ናቸው።

17) **"የውጭ ፈንድ"** ማለት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም በባለስልጣኑ ፈቃድን ያገኘ በውጭ ሃገር ሕግ መሰረት የተቋቋመ ፈንድ ነው።

18) **“ገቢ የሚያስገኝ ሪል ስቴት”** ማለት ከሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ጋር በተያያዘ፣ በሪል እስቴት ልማት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ አዋጅ ቁጥር 1357/2016 አንቀጽ 2(1) በተሰጠው ትርጉም አግባብ የተገነባ ወይም ግንባታው የተጠናቀቀ ሪል ስቴትን ጨምሮ በባለስልጣኑ ገቢ የሚያስገኝ ተብሎ የጸደቀ ሌላ ማንኛውም አይነት ተመሳሳይ ንብረት ነው።

19) **“አይ.ኤፍ.አር.ኤስ”** ማለት አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ነው።

20) **“አለም አቀፍ የዋጋ ምዘና” ማለት** በአለም አቀፍ የዋጋ ግመታ ደረጃዎች ካውንስል (IVSC) የተቀመጡ የዋጋ ግመታ ተግባራትን ለማከናወን የሚያገለግሉ መመዘኛዎች ነው።

21) **“አለም አቀፍ የግል ባለሃብት ፈንድ እና ቬንቸር ካፒታል ምዘና” ወይም “አይ.ፒ.ኢ.ቪ” የአሰራር መመሪያዎች** ማለት በግል ባለሃብት ፈንድ እና ቬንቼር ካፒታል ኢንቨስትመንቶችን ተመጣጣኝ ዋጋ ለማወቅ እንዲቻል በአይ.ፒ.ኢ.ቪ ቦርድ የተቀረጸ የግምታ ስርዓት ነው።
22) **"የኢንቨስትመንት ፍቃድ"** ማለት በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ስራዎችን ለመስራት ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተገኘ ፍቃድ ነው።
23) **"የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መግለጫ" ወይም "የኢንቨስትመንት ፖሊሲ”** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ላይ የተዘረዘሩትን የኢንቨስትመንት ስትራቴጂዎችን፣ አላማዎችን እና የታቀዱ ውጤቶችን የሚዘረዝር የጽሁፍ መግለጫ ነው።
24) **"ቁልፍ የኢንቨስተር የመረጃ ሰነድ"** ማለት ለመደበኛ ኢንቨስተሮች የሚቀርብ ስለፈንዱ አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ ሰነድ ነው።
25) **“የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ”** ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 ነው።
26) **"የገንዘብ ገበያ"** ማለት ከአንድ ዓመት ያነሰ የመክፈያ ጊዜ ያላቸው ሰነዶች ግብይት ማለት ነው።
27) **"አነስተኛ የቃል ኪዳን መጠን”** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 2(33) ላይ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።
28) **“የተጣራ የሃብት ዋጋ"** ማለት እዳው ተቀናሽ ተደርጎ የሚገኘው የፈንዱ ሃብት ዋጋ ነው።
29) **“ማቅረብ”** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ አንቀጽ 2(35) ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።
30) **“የሽያጭ አቅርቦት ሰነድ”** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ አንቀጽ 2(34) ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።
31) **“አከናዋኝ”** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(12) እንደተገለጸው የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ አከናዋኝ ነው።
32) **“የአፈጻጸም መለኪያ ሪፖርት”** ማለት በፈንዱ አከናዋኝ የሚዘጋጅ አንድ ኢንቨስተር የፈንዱን እንቅስቃሴ እና ውጤት እንዲገነዘብ የሚያግዝ የአፈጻጸም እና ተዛማጅ መረጃዎችን የያዘ ሪፖርት ነው።
33) **"ባለሞያ አካላት"** ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ወይም ማንኛውም ለጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ የባለሞያ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ነው።
34) **"የንብረት ኢንቨስትመንት"** ማለት ገቢ በሚያስገኝ ሪል ስቴት፣ ሪል ስቴት ልማት ወይም ገቢ በሚያስገኝ ሪል ስቴት ወይም ሪል ስቴት ልማት ያለ ጥቅምን በሚወክሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ነው።
35) **"የንብረት አስተዳዳሪ”** ማለት ከሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ወይም ሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት ከሚያደርግ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ ጋር በተያያዘ አግባብ ካለው አካል

ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ፈቃድ ያገኘ እና በዚህ መመሪያ የተፈቀዱ ስራዎችን እንዲሰራ በባለሥልጣኑ ይሁንታ የተሰጠው ሰው ነው።

36) **"ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ"** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁ. 1030/2017 ነው።

37) **"ብቁ ኢንቨስተር" ማለት** ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ አንቀጽ 2(46) ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል። ለዚህ መመሪያ ዓላማ ባለከፍተኛ ጥሪት ባለሀብት ማለት የግል ተሽከርካሪን እና ዋነኛ መኖሪያ ቤትን ሳይጨምር ቢያንስ ሃያ አምስት ሚሊዮን (25,000,000.00) ብር ወይም ሌላ ባለስልጣኑ በሚወስነው የሃብት መጠን ልክ የተጣራ ኃብት ያለው ግለሰብ ነው።

38) **"የሪል ስቴት ልማት"** ማለት በሪል ስቴት ልማትና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ አዋጅ ቁጥር 1357/2017 አንቀጽ 2(3) ስር የተመለከተው ትርጉም ይኖረዋል።

39) **"የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ"** ማለት በዚህ መመሪያ ለሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ገቢ በሚያስገኝ ሪል ስቴት የሚገኘውን ገቢ ለመቀበል እና ለማከፋፈል አላማ የተቋቋመ ፈንድ ነው።

40) **"የምዝገባ መግለጫ"** ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ አንቀጽ 2(48) ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

41) **"የተዛማጅ ወገን ግብይት"** ማለት አግባብነት ካለው ሰው ወይም አካል ጋር በተያያዘ፡-

    ሀ) ከሌሎች ሁኔታዎች መካከል ቅርበት ያለው ሰው፣ የእሽሙር ማኅበር፣ ቁጥጥር የሚደረግበት፣ በጋራ ቁጥጥር የሚደረግበት፣ ተዛማጅ በሆነ አካል ጉልህ ተጽእኖ የሚያድርበት ወይም የሚተዳደር ተዛማጅ አካል ጋር፣ ወይም

    ለ) የዚያ ሰው ቤተሰብ ወይም ቅርብ የቤተሰብ አባል ጋር፣ የሚደረግ ግብይት ነው።

42) **"መደበኛ ኢንቨስተር"** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ አንቀጽ 2(49) ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

43) **"የሙከራ ቁጥጥር ማዕቀፍ"** ማለት አዳዲስ የፋይናንስ ገበያ ምርቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም የንግድ ሞዴሎችን በባለሥልጣኑ ቁጥጥርና ድጋፍ ስር ለግዜው በተፈቀደ የቁጥጥር ምቹነት መፈተሽ የሚያስችል የቁጥጥር ማዕቀፍ ነው።

44) **"ፈንድ" ማለት** በአዋጁ አንቀጽ 2(11) ላይ የተገለጸው የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ነው።

45) **"የፈንዱ ፖርትፎሊዮ"** ማለት የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ ኢንቨስትመንቶች፣ የንብረት ኢንቨስትመንት እና ሌሎች ሃብቶች ነው።

46) **"የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገማች ድርጅት"** ማለት በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አንቀጽ 2(51) ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

47) **"የግዥ ቃልኪዳን ስምምነት"** ማለት ኢንቨስተሩ በፈንዱ ውስጥ አዲስ የወጡ የድርሻ ክፍልፋዮችን ለማግኘት ወይም ለመግዛት የሚጠቀምበት ሰነድ ነው።

48) **“ጠቅላላ ገቢ”** ማለት የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ላይ ትርፍ ክፍፍልን፣ ጥቅም እና ድልድልን እንዲሁም ማንኛውም የፈንዱ የኢንቨስትመንት ሃብቶች ላይ የተገኘ የሃብት ለውጥን ጨምሮ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ከመነሻው ኢንቨስትመንት ላይ ከዋለው ወጪ ተቀንሶ የሚገኘው የመቶኛ ውጤት ነው።

49) **“የድርሻ ክፍልፋይ” ወይም “በፈንድ ውስጥ ያለ የድርሻ ክፍልፋይ”** ማለት በባለስልጣኑ በተመዘገበ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለ አክሲዮን ወይም የባለቤትነት ድርሻ ነው።

50) **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሰው ነው።

51) በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው በሙሉ የሴትንም ጾታ ያጠቃልላል።

52) በዚህ መመሪያ አገልግሎት ላይ የዋለ ማንኛውም ሌላ ቃል በአዋጁ ላይ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1) ይህ መመሪያ፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ለመመስረት ወይም ስራ ለማካሄድ በሚፈልግ ማንኛውም ሰው፣ እና

ለ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮችን የሚወክሉ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አቅርቦት ላይ፣

ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

2) አንድ የስምምነት መዋቅር ፡-

ሀ) የፈንድ አስተዳደርን የሚያካትት ከሆነ፣ እና

ለ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ወይም ሌሎች ንብረቶችን በባለቤትነት በመያዝ፣ በይዞታ በማቆየት፣ በማስተዳደር ወይም በማስተላለፍ ሰዎች በእንደዚህ አይነት አሰራር ውስጥ እንዲሳተፉ፣ ገቢ ወይም ትርፍ እንዲያገኙ የሚያደርግ እንደሆነ እና ለዚሁ ዓላማ ገንዘብን የሚያሰባስብ ከሆነ፣

መመዝገብ ያለበት ፈንድ ተደርጎ ይቆጠራል።

3) የፈንድ ምዝገባ በዚህ መመሪያ በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ይሆናል።

<u>ምዕራፍ ሁለት፣ የፈንዱ መስፈርቶች</u>

4. <u>የፈንዱ የሕግ ቅርጽ</u>

1) ፈንዱ በንግድ ሕጉ በተቀመጠው መሰረት ከሚከተሉት በአንዱ የሕግ ቅርጽ ሊቋቋም ይችላል።

ሀ) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣

ለ) የአክስዮን ማኅበር፣

ሐ) ሁለት ዓይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር፣ ወይም

መ) በባለስልጣኑ እውቅና የሚሰጠው የኢንቨስትመንት ኩባንያ።

2) ለፈንዱ የሚፈቀደው የህግ ቅርጽ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 34 ላይ በተቀመጡት የፈንድ ዓይነቶች፣

ለ) ፈንዱ ለማሰተፍ ባሰባቸው ኢንቨስተሮች፣ እና

ሐ) በፈንዱ ፖርትፎሊዮ ውስጥ ሊካተቱ በታቀዱ ንብረቶች፣የገንዘብ ሰነዶች፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ሃብቶች አይነት ባህርይ ላይ፣

በመመስረት ይሆናል።

3) ማንኛውም ፈንድ አግባብ ባለው የመንግስት ባለስልጣን የተሰጠ የጸና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና እንደ አግባብነቱ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊኖረው ይገባል።

5. <u>አስፈላጊ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች</u>

1) ፈንዱ በማንኛውም ጊዜ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አከናዋኝ ሊኖረው ይገባል።
2) ፈንዱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 78 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ጠባቂ ሊኖረው ይገባል።
3) ማንኛውም ፈንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹትን ተግባራት በፈንዱ ስም የሚሰሩ ወይም የሚያከናውኑ አስፈላጊ የሆኑ የባለሞያ አካላት አገልግሎትን ማግኘት ይጠበቅበታል።
4) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም በባለስልጣኑ በሚመዘገበው የፈንድ አይነት መሰረት በዚህ መመሪያ የተገለጹት ተጨማሪ ባለሞያ አካላት ሊያስፈልጉት ይችላል።
5) ምንም እንኳን የፈንዱ ምዝገባ ቢኖርም የአከናዋኙ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ክልከላ፣ እግድ ወይም መሰረዝ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ መሰረት ይሆናል።

6. <u>የኢንቨስትመንት ፖሊሲ</u>

1) እያንዳንዱ ፈንድ ኢንቨስተሩ የኢንቨስትመንት እድሉን ለመገምገምና የፈንዱ የኢንቨስትመንት ዓላማ እንዴት ሊሳካ እንደሚችል ለመገምገም የሚያስችለው ትክክለኛና ግልጽ የሆነ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል።

2) የኢንቨስትመንት ፖሊሲው፡-

ሀ) ሊመዘገብ የታሰበው የፈንድ አይነት፤

ለ) እንደ የካፒታል እድገት ወይም ገቢ ያሉ የታሰቡ የኢንቨስትመንት አላማዎች፤

ሐ) የኢቨስትመንት አላማዎችን ለማሳካት የሚያስችል ስትራቴጂ እና ዘዴ፤

መ) የገንዘብ ሰነዶች፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ሌሎች ማናቸውም ሃብቶችን ጨምሮ በፈንዱ ፖርትፎሊዮ ውስጥ ያሉ ሃብቶች ባህሪ እና አይነት፣

ሠ) የፈንዱ ፖርትፎሊዮ በኢኮኖሚ ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪ፣ በጂኦግራፊያዊ አካባቢ ወይም በሌላ የኢንቨስትመንት አይነት ለመሰማራት ያለው ማንኛውም ልዩ እቅድ፤

ረ) በፈንዱ ፖርትፎሊዮ ውስጥ ያሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ወይም ሌላ ማናቸውም ሃብቶች ስብጥር እና ብዝሃነት በተመለከተ ያለውን እቅድ፣

ሰ) የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የኢንቨስትመንት ክምችት እና ብዝሃነት ገደቦች፣

ሸ) በፈንዱ የታቀደው የብድር አጠቃቀም እና በፈንዱ የመበደር አቅም ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ገደቦችን፣እና

ቀ) የኢንቨስትመንት መጠኑን እና የፈንዱ ካፒታል ወደ ኢንቨስትመንት እና ሃብቶች ለመግዛት የሚውልበትን የጊዜ ሰሌዳን ጨምሮ የፈንዱን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እቅድ

መግለጽ አለበት።

3) ለንኡስ አንቀጽ 2 አላማ የኢንቨስትመንት ፖሊሲው የአሃዝ እና መጠናዊ መረጃን መያዝ የሚኖርበት ሲሆን ፈንዱ በየትኛው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣ አውጪ ወይም ዘርፍ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ እንዳቀደ እና ያቀደውን መጠን ከፈንዱ ጠቅላላ ፖርትፎሊዮ በመቶኛ መግለጽ አለበት።

4) ፈንዱ በማንኛውም ጊዜ ሃብቱን ከኢንቨስትመንት ፖሊሲው ጋር በተጣጣመ መንገድ ስራ ላይ ሊያውል እና ሊያስተዳድር ይገባል።

5) በኢንቨስትመንት ፖሊሲው ላይ የሚደረግ ማንኛውም አይነት ጉልህ ለውጥ ከተመዘገቡት የፈንዱ ክፍልፋይ ባለድርሻዎች ውስጥ በሁለት ሶስተኛ (2/3) ድምጽ መጽደቅ ያስፈልገዋል።

ምዕራፍ ሦስት፣ የፈንድ ዓይነቶች

ክፍል 1፡ ጠቅላላ

7. በባለስልጣኑ የሚመዘገቡ የፈንድ ዓይነቶች

1) በባለስልጣኑ የሚመዘገብ ፈንድ ከሚከተሉት በአንዱ አይነት ሊቋቋም ይችላል፡-
   ሀ) የህዝብ የገንዘብ ገበያ ፈንድ፣
   ለ) የህዝብ ጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ፣
   ሐ) የህዝብ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ፣
   መ) አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ፣ ወይም
   ሠ) በዚህ መመሪያ መሰረት በባለስልጣኑ እውቅና የተሰጠው ባለ ልዩ ስያሜ ፈንድ።
2) በባለስልጣኑ ከመመዝገብ እንዲሁም ከሽያጭና ማስታወቅያ ጋር ተያይዞ የፈንዱ ስያሜ፡-
   ሀ) የተመዘገበውን የፈንድ አይነት በአግባቡ የሚያንጸባርቅ፣
   ለ) የፈንዱን የኢንቨስትመንት ፖሊሲ የሚጠቁም፣ እና
   ሐ) ተገቢ የሆነ እና አሳሳች ያልሆነ
   መሆን አለበት።
3) ለፈንዱ የተሰጠው ስያሜ፡
   ሀ) ፈንዱ ለመግዛት፣ ለመያዝ ወይም ለማስተዳደር ያሰበውን የገንዘብ ሰነድ፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ወይም ሃብት
   ለ) የታሰበውን ኢንዱስትሪ ወይም ዘርፍ ባሕርይና ሁኔታ፤ ወይም
   ሐ) እንደአስፈላጊነቱ የፈንዱን የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ሌላ ማንኛውም ቁልፍ ገጽታ
   ይበልጥ የሚገልጽ ሊሆን ይችላል።

8. የህዝብ ገንዘብ ገበያ ፈንድ መስፈርቶች

1) የህዝብ የገንዘብ ገበያ ፈንድ፡-
   ሀ) በንግድ ህጉ ላይ እንደተገለጸው የአክሲዮን ማኅበር፣
   ለ) ክፍልፋዮቹን ለህዝብ ሽያጭ በማቅረብ የተቋቋመ፣ እና
   ሐ) ክፍልፋዮቹን በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ያስመዘገበ፣
   መሆን ይኖርበታል።
2) የህዝብ የገንዘብ ገበያ ፈንድ ፈቃድ በተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የምዝገባ መስፈርቶች ውስጥ የተመለከተው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ሊኖረው ይገባል።

3) የህዝብ ገንዘብ ገበያ ፈንድ በዚህ ምዕራፍ ክፍል ሁለት ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማክበር አለበት።
4) ፈንዱ እንደ ሄጅ ፈንድ እና በባለሙያ ኢንቨስተሮች ጥቅም ላይ የሚውሉ ብዝኃነት ያላቸው ወይም ውስብስብ የሆኑ የንግድ ስልቶችን የሚጠቀም ከሆነ የህዝብ የገንዘብ ገበያ ፈንድ ተብሎ አይመዘገብም።

9. የህዝብ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ መስፈርቶች

1) የህዝብ የጋርዮሽ ፈንዱ፥
   ሀ) በንግድ ህጉ መሰረት የተቋቋመ የአክስዮን ማኅበር፣
   ለ) ክፍልፋዮቹን ለህዝብ በማቅረብ የተቋቋመ፣ እና
   ሐ) ክፍልፋዮቹን በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ያስመዘገበ
መሆን ይኖርበታል።

2) የህዝብ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ ፈቃድ በተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ገበያ የምዝገባ መስፈርቶች ላይ የተቀመጠው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ሊኖረው ይገባል።

3) የህዝብ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ በዚህ ምዕራፍ ክፍል ሦስት ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማክበር አለበት።

4) ፈንዱ እንደ ሄጅ ፈንድ እና በባለሙያ ኢንቨስተሮች ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ ወይም ውስብስብ የሆኑ የንግድ ስልቶችን የሚጠቀም ከሆነ የህዝብ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ ተብሎ አይመዘገብም።

10. የህዝብ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ

1) የህዝብ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ :-
   ሀ) በንግድ ሕጉ በተቀመጠው መሠረት የአክሲዮን ማኅበር፣
   ለ) ክፍልፋዮኖቹን ለህዝብ በማቅረብ የተቋቋመ ወይም ክፍልፋዮቹ በሕዝብ የተያዙ፣ እና
   ሐ) ክፍልፋዮቹን በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ያስመዘገበ፣
መሆን አለበት።

2) የህዝብ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ፈቃድ በተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ገበያ የምዝገባ መስፈርቶች ላይ የተቀመጠው ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታል ሊኖረው ይገባል።
3) የህዝብ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ በዚህ ምዕራፍ ክፍል አራት ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማክበር አለበት።

11. የአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ መስፈርቶች

1) አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ :-

   ሀ) በንግድ ሕጉ መሰረት እንደ አክስዮን ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ ወይም ሁለት አይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር ሊቋቋም ይችላል፤ እና

   ለ) ከምዝገባ ነጻ በሆነ አቅርቦት ይቋቋማል።

2) አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንዱ :-

   ሀ) እንደ አክስዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የተቋቋመ ከሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ወይም

   ለ) እንደ ሁለት አይነት ኃላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር ሆኖ የተቋቋመ ከሆነ ደግሞ ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ሸሪክን ያካተተ የቦርድ አቻ የሆነ ውሳኔ ሰጭ አካል፣

   ሊኖረው ይገባል።

3) እንደ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ የተመዘገበ ፈንድ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን የሚመለከታቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የገንዘብ ገበያ ፈንድ፣ የኃርዮሽ ገንዘብ ወይም ሪል እስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ሊሆን ይችላል።

4) እንደ አማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ የተመዘገበ ፈንድ በዚህ መመሪያ በተጠቀሱት መስፈርቶች መሰረት የኢንቨስትመንት ፖሊሲውን ማክበር አለበት።

12. የልዩ ስያሜ መስፈርቶች

1) የሚመዘገበው ፈንድ በዚህ ምዕራፍ ከተደነገጉት ማናቸውም የፈንድ ዓይነቶች ውስጥ የማይወድቅ ከሆነ እንደ ባለ ልዩ ስያሜ ፈንድ ሊመዘገብ ይችላል።

2) ባለስልጣኑ እንደየሁኔታው የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈንዱን ባለ ልዩ ስያሜ ፈንድ ብሎ ይመዘግባል።

   ሀ) የንብረቱን ወይም የሀብቱን ባህሪ እና አይነት፣ የኢንቨስትመንት ተግባሩን ዘርፍ ወይም ኢንዱስትሪ እና በእንደዚህ ያሉ ሀብቶች ወይም ንብረቶች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ መነሻ ምክንያቱን ጨምሮ ፈንዱ ኢንቨስት ለማድረግ ያሰበባቸው የንብረት አይነቶች፣

   ለ) የታቀደው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ፣

   ሐ) የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ስብጥር እና እንደአስፈላጊነቱ ገደቦች፣

መ) በፈንዱ የወጡ ወይም የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን፣ ክፍልፋዮችን ወይም ሌሎች የባለመብትነት ሰነዶችን ገንዘብ አከልነትን፣ የመሸጥ እና የግብይት ሁኔታን፣

ሠ) የታቀደው የፈንድ አከናዋኝ እና አስፈላጊ ባለሞያ አካላት፣ እና

ረ) በአዋጁ የተቀመጡትን ዓላማዎች ለማሳካት ባለሥልጣኑ አስፈላጊ እንደሆኑ ያመነባቸው ሌሎች ሁኔታዎች።

3) የልዩ ስያሜ ፈንድን የሚመለከቱ የአቅርቦት ሰነዶች፡-

ሀ) ከሌሎች የፈንድ ዓይነቶች ጋር ያላቸውን ልዩነቶች በማጉላት የልዩ ስያሜው ዳራ እና አውድን፣ እና

ለ) ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ማንኛቸውም አደጋዎችን፣

መግለጽ አለባቸው።

13. <u>**የፈንድ ፖርትፎሊዮ መስፈርቶች**</u>

1) እያንዳንዱ ፈንድ፡-

ሀ) ለተመዘገበበት የፈንድ ዓይነት ተስማሚ የሆነ፣ እና

ለ) ከፈንዱ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም የፖርትፎሊዮ አወቃቀር፣

ያስፈልገዋል።

2) የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን፣

ለ) አግባብነት ያላቸው የገንዘብ ሰነዶችን፣ ወይም

ሐ) የንብረት ኢንቨስትመንትን፣

ሊይዝ ይችላል።

3) የፈንዱ ፖርትፎሊዮ በኢንቨስትመንት ፖሊሲ ከተገለጸ ብቻ በመጀመሪያ ሽያጭ የተገኙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ሊይዝ ይችላል።

4) በኢንቨስትመንት ፖሊሲው መሠረት ካፒታሉን ኢንቨስት እስከሚያደርግ ድረስ ፈንዱ ጥቅም ላይ ያልዋለን ካፒታልን ለማስተዳደር በገንዘብ አከል የገንዘብ ሰነዶች ላይ ኢንቨስት ሊያደርግ ይችላል።

5) በዚህ መመሪያ የተደነገጉ መስፈርቶች ቢኖሩም ፈንዱ በኢንቨስትመንት ፖሊሲው በተገለጸው መሰረት በፈንዱ ፖርትፎሊዮ ላይ ተጨማሪ ገደቦችን ሊጥል ይችላል።

6) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ለህዝብ የቀረብ ፈንድ ከጠቅላላ ሃብቱ ቢያንስ 30 በመቶውን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የምስክር ወረቀት ካገኘበት ጊዜ አንስቶ በስድስት (6) ወራት ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ አለበት።

14. ተፈጻሚ የሚሆኑ የብድር ገደቦች

1) ፈንዱ መበደር የሚችለው ጠቅላላ የብድር መጠን ከጠቅላላ የፈንድ ፖርትፎሊዮ ሃያ በመቶ (20%) ያህሉን ብቻ ነው።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ካለው ጠቅላላ የፈንድ ፖርትፎሊዮ እስከ አርባ በመቶ (40%) ያህል ሊበደር ይችላል።
3) በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተደነገጉት የብድር ገደቦች በአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያሉ ብቁ ኢንቨስተሮች ላይ ተፈጻሚ አይደሉም።

15. በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማበድር ላይ የተጣሉ ገደቦች

1) የኢንቨስትመንት ፖሊሲው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እንዲያበድር የሚፈቅድለት ፈንድ ተጨማሪ ገቢን ለማግኘት በፈንዱ ፖርትፎሊዮ ውስጥ ካለው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የተወሰነውን ሊያበድር ይችላል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈንዱ ንብረቱ በባለሥልጣኑ በፀደቀ የመልሶ መግዛት ውል አግባብነት ካላቸው ተቋማት በማስቀመጥ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ሊያበድር ይችላል።

16. በፈንዱ ሃብቶች ላይ የተጣሉ ገደቦች

የፈንዱ አከናዋኝ ወይም ጠባቂ፦

ሀ) ግዴታው ሃብቱን ወይም መብቱን በማስተላለፍ ወዲያውኑ ሊፈጸም የሚችል ካልሆነ፣ እና

ለ) ፈንዱ ስምምነቱ ውስጥ በሚገባበት ጊዜ ሃብቱ እና መብቶቹ በፈንዱ ባለቤትነት ስር ካልሆኑ፣

በስተቀር በፈንዱ ስም የፈንዱን ሃብቶች እና ንብረቶች የመሸጥ ስምምነት ውስጥ ሊገባ ወይም ሌላ ሰው እንዲገባ ጥያቄ ሊያቀርብ አይችልም።

17. የተከለከሉ ዋስትናዎች እና ካሳዎች

የፈንዱ ሃብቶች የፈንዱ አከናዋኝ ወይም ጠባቂ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ለገባው ከዋስትና ወይም ካሳ ክፍያ የመነጩ ግዴታዎችን ለመወጣት ሊውሉ አይገባም።

ክፍል 2፡ የገንዘብ ገበያ ፈንድ

18. የገንዘብ ገበያ ፈንድ መስፈርቶች

1) በገንዘብ ገበያ ፈንድ ውስጥ ያሉ ክፍልፋዮች ለሕዝብ ሽያጭ ወይም ከምዝገባ ነጻ በሆነ አቅርቦት ሊቀርቡ የሚችሉ ሲሆን አቅርቦቱ የሚመለከተው ፈንድ እንደ አስፈላጊነቱ በሚከተሉት መሠረት መመዝገብ አለበት፦

   ሀ) በህዝብ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ መስፈርቶች፣ ወይም

   ለ) በአማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ።

2) እንደ ገንዘብ ገበያ ፈንድ የተመዘገበ ፈንድ በዋነኝነት አግባብነት ያላቸው የገንዘብ ሰነዶችን ያካተተ የፈንድ ፖርትፎሊዮ ሊኖረው ይገባል።

19. <u>የገንዘብ ገበያ ፈንድ የፖርትፎሊዮ ስብጥር መስፈርቶች</u>

1) የገንዘብ ገበያ ፈንድ ተብሎ ለተመዘገበ ፈንድ አላማ ሲባል አግባብነት ያላቸው የገንዘብ ሰነዶች የሚባሉት፡-

   ሀ) ከፍተኛው አማካኝ የቆይታ ጊዜ አስራ ሁለት (12) ወራት የሆኑ፣ እና

   ለ) የመንግስት የገንዘብ ሰነዶች፣ ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና የተደረገላቸው ወይም ዋስትና የተገባላቸው የንግድ ወረቀቶች፣ የተቀማጭ የምስክር ወረቀቶች እና ሌሎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው የሚገለጹ ተመሳሳይ ሰነዶች ናቸው።

2) የገንዘብ ገበያ ፈንድ የፈንዱን ንብረቶች ከሃያ በመቶ (20%) በላይ በአንድ ተቋም ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ አይችልም።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ገደብ በፌደራል መንግሥት የገንዘብ ሰነዶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

<u>ክፍል 3፡ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ</u>

20. <u>የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ መስፈርቶች</u>

1) የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ ክፍልፋዮች ለሕዝብ ሽያጭ ወይም ከምዝገባ ነጻ በሆነ አቅርቦት ለሽያጭ መቅረብ የሚችሉ ሲሆን የሽያጭ አቅርቦቱ የሚመለከተው ፈንድ እንደ አግባብነቱ በሚከተሉት መሠረት መመዝገብ አለበት፡-

   ሀ) በህዝብ የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ መስፈርቶች፣ ወይም

   ለ) በአማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ።

2) እንደ ጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ የተመዘገበ ፈንድ በዋነኝነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እና በአዋጁ አንቀጽ 2(35) መሰረት አግባብነት ያላቸው የገንዘብ ሰነዶችን ያካተተ የፈንድ ፖርትፎሊዮ ሊኖረው ይገባል።

3) ለጋርዮሽ ገንዘብ ፈንዱ የተሰጠው ስያሜ ፈንዱ ሊያገኘው፣ ሊይዘው ወይም ሊያስተዳድረው የሚያቅደው የፈንድ ፖርትፎሊዮ መገለጫ እና ባህሪን እና አግባብነት ያላቸውን የኢንቨስትመንት ፖሊሲውን መገለጫዎች የሚያመለክት መሆን አለበት።

21. <u>የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ ፖርትፎሊዮ ስብጥር መስፈርቶች</u>

1) የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ የፈንድ ፖርትፎሊዮ በአዋጁ አንቀጽ 2(44) ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል።

2) የጋርዮሽ ገንዘብ ፈንድ ከፈንዱ ጠቅላላ ሃብት ውስጥ ከሃያ በመቶ (20%) በላይ በአንድ ተቋም ውስጥ ኢንቨስት ሊያደርግ አይችልም።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው ገደብ በፌደራል መንግስት የገንዘብ ሰነዶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

ክፍል 4: የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ

22. ወሰን እና ገደቦች

1) የንብረት ኢንቨስትመንት ተግባር የሚያከናውን ፈንድ ተግባሩ ባለስልጣኑ በሚያጸድቀው የፈንዱ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ውስጥ በዝርዝር መቀመጡን እና ተለይቶ መጠቀሱን ማረጋገጥ አለበት።

2) ማንኛውም ፈንድ የተጣራ የሀብቱን ዋጋ ከሃያ በመቶ (20%) በላይ በገቢ አስገኝ ሪል ስቴት ላይ ሆነም በሪል ስቴት ልማት ላይ በሪል ስቴት ላይ ካዋለ የሚከተሉትን ጨምሮ በዚህ ክፍል ውስጥ የተመለከቱትን መስፈርቶችን ማክበር ይጠበቅበታል።

   ሀ) በዚህ ክፍል ውስጥ እንደተገለጸው የሥነ-ምግባር፣ የብቃት እና የግመታ መስፈርቶችን፣

   ለ) የሪል ስቴት ሀብቶችን ለማስተዳደር እና ለማከናወን ተገቢ የንብረት አስተዳዳሪ የማግኘት መስፈርትን፣

   ሐ) የፈንዱን ሪል ስቴት ሀብቶችን ለመገመት በተገቢው መንገድ ፈቃድ የተሰጠው የንብረት ግመታ አገልግሎት ሰጭን የመሾም መስፈርትን፣ እና

   መ) ጠንካራ የጥቅም ግጭት አስተዳደር የመተግበር መስፈርትን።

3) የህዝብ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ መስፈርቶችን የማያሟላ ነገር ግን በዋነኝነት በሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት የሚያደርግ ፈንድ የፈንዱ ክፍልፋዮች ከምዝገባ ነጻ በሆነ መንገድ ለሽያጭ የቀረቡ እስከሆነ ድረስ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሠረት እንደ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ ለመመዝገብ ይችላል።

23. የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ፖርትፎሊዮ ስብጥር መስፈርቶች

1) የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ቢያንስ የፈንዱን የተጣራ የሀብት ዋጋ ሰማንያ በመቶ [80%] ገቢ በሚያስገኝ ሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለበት።

2) ገቢ የሚያስገኝ ሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት ያልተደረገው ቀሪ ሂሳብ በሪል ስቴት ልማት ንብረት፣ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ አግባብነት ባላቸው የገንዘብ ሰነዶች ወይም በጥሬ ገንዘብ ላይ ኢንቨስት ሊደረግ ይችላል።

3) የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ በገቢ አስገኚ ሪል ስቴት ወይም በአንድ የንብረት ኢንቨስትመንት የገቢ ወይም የገንዘብ ፍሰት መብት ምንጭ ላይ ከፈንዱ ሀብት ውስጥ ከሃያ በመቶ [20%] በላይ ኢንቨስት ሊያደርግ አይችልም።

24. በሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ የአከናዋኙ ሚና እና ኃላፊነት

1) በዚህ መመሪያ ምዕራፍ አምስት ክፍል 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት የሚያደርግ ፈንድ አከናዋኝ የሚከተሉትን ተግባራትን እንደ ተፈጻሚነቱ የመከታተል እና የማስተባበር ኃላፊነት አለበት።

   ሀ) የንብረት ግዢ እና የንብረት ማስወገድ እና ግዢና ማስወገድን የተመለከቱ እቅዶችን፣

   ለ) ኪራይን እና መልሶ ፋይናንስ ማድረግን፣

   ሐ) የአሠራር በጀቶችን ጨምሮ የአሠራር እና የፋይናንስ ሪፖርት፣

   መ) በፈንዱ ፖርትፎሊዮ ውስጥ ያለን ንብረት ግምት፣

   ሠ) የገበያ ግምገማ፣ እና

   ረ) የሚመለከተው ፈንድ የንብረት አስተዳዳሪ ተገቢነት ያላቸው ማናቸውም ተግባራትን።

2) አከናዋኙ ከንብረት አስተዳዳሪው፣ ከገማች ድርጅቱ እና ከጠባቂው ጋር ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም የጥቅም ግጭት ለመለየት፣ ለመቆጣጠር እና ለመቀነስ የሚያስችሉ አስፈላጊ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርዓቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት።

25. የሪል ስቴት ንብረት አስተዳዳሪ ሹመት

1) አከናዋኙ በሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት ለሚያደርገው ፈንድ ተገቢ የሆነ የንብረት አስተዳዳሪ ይሾማል።

2) አከናዋኙ የንብረት አስተዳዳሪው፡-

   ሀ) ፈንዱ ለሚያከናውነው የሪል ስቴት ተግባር አስፈላጊው እውቀት፣ ክህሎት እና ሙያ ያለው መሆኑን፣

   ለ) በባለሥልጣኑ የተቀመጡ የብቁና ተገቢነት መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን፣

   ሐ) ሥራውን በተገቢው መንገድ ለማከናወን የሚያስችለውን በቂ የሰው ሃይል ፣ የአደረጃጀት እና ቴክኒካል ብቃት ያለው መሆኑን፣

መ) አጥጋቢ የሆነ በጽሁፍ የሠፈሩ የሕግ ተገዥነት አሰራርና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ያለው መሆኑን፣

ሠ) ተገቢውን ፈቃድ አግባብ ካለው የመንግስት አካል ያገኘ መሆኑን፣ እና

ረ) በባለስልጣኑ የተቀመጡ ሌሎች ማናቸውም መስፈርቶችን የሚያከብር መሆኑን፣

ማረጋገጥ አለበት።

3) የንብረት አስተዳዳሪው ሹመት የሚከተሉትን ያካተተ የጽሑፍ ውል ስምምነት ያስፈልገዋል።

ሀ) የስምምነቱን አላማዎች፣

ለ) የስምምነቱ አካል የሆኑ ንብረቶችን፣

ሐ) የስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታዎች፣

መ) በአዋጁ አንቀጽ 111 መሠረት አለመግባባቶች የሚፈቱበትን ድንጋጌዎች፣ እና

ሠ) ስምምነቱ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ እና የሚቋረጥበት ሁኔታ ጋር የተያያዙ ሌሎች ማናቸውም ደንብና ሁኔታዎችን።

4) ማናቸውም ተቃራኒ ድንጋጌዎች ቢኖሩም አከናዋኙ የንብረት አስተዳዳሪውን ከመሾሙ ወይም ከመተካቱ በፊት የባለሥልጣኑን ፈቃድ መጠየቅ እና ቅድመ-ይሁንታውን ማግኘት አለበት።

26. <u>የንብረት አስተዳዳሪው ሚና</u>

1) የንብረት አስተዳዳሪው ተግባራት የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል።

ሀ) እንደ የኪራይ ግምገማ ማካሄድ፣ የአከራይና ተከራይ ደንቦችን ማዘጋጀት፣ የኪራይ ስምምነትን ወይም ውሎችን ማዘጋጀት፣ የተከራይ መኖሪያን ማስተዳደር፣ ኪራይ መሰብሰብ እና ውዝፎችን እና ይዞታን መመለስ የመሳሰሉ የአከራይና ተከራይ አስተዳደር ሥራዎች መሥራት፣

ለ) ሕንፃዎችን እና ግንባታዎችን መጠበቅ፣ ማስተዳደር እና ማሻሻል፣

ሐ) እንደ የደህንነት ቁጥጥር፣ የኤሌክትሪክ እና የመገናኛ ስርዓቶች ያሉ መደበኛ የአስተዳደር አገልግሎቶች፣ እና

መ) ለንብረት አስተዳደር አስፈላጊ እና ከንብረት አስተዳደር ሥራ ጋር በመደበኛ ሁኔታ የሚያጋጥሙ ሌሎች መሰል ተግባራት።

2) የፈንድ አከናዋኙ የንብረት አስተዳዳሪው፡-

ሀ) ግዴታውን በጥንቃቄ፣ በብልሀትና በትጋት መወጣቱን፣

ለ) ሊያጋጥም የሚችልን የጥቅም ግጭቶችን ለመለየት እና ለመከላከል የሚያስችል በቂ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርዓቶች ያሉት መሆኑን፣ እና

ሐ) ከሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንዱ ጋር በሚደረግ ግብይት ላይ ጉልህ ፍላጎት ካለው ወይም ከእንደዚህ አይነት ግብይት ጋር በተገናኘ ተጨባጭ ወይም ተገማች የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ግንኙነት ካለ በተሟላ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ይፋ ማድረጉን፣

ማረጋገጥ አለበት።

27. <u>የንብረት አስተዳዳሪውን ስለመለወጥ</u>

1) አከናዋኙ የንብረት አስተዳዳሪውን የማንሳት፣ የመተካት ወይም ሌላ ማንኛውም የንብረት አስተዳዳሪውን የመለወጥ ዕቅድን ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

2) የንብረት አስተዳዳሪው፡-

ሀ) የመክሰር ውሳኔ ከተወሰነበት፣
ለ) በዚህ መመሪያ ወይም ከአከናዋኙ ጋር በገባው ስምምነት ላይ የተቀመጡትን ግዴታዎች እና ተግባራት ማከናወን ከተሳነው፣ ወይም
ሐ) ኢንቨስተሮችን ጥቅም እና በባለስልጣኑ በተከለከለው መሠረት የገበያውን ተዓማኒነት የሚጎዳ ማንኛውንም ድርጊት ከፈጸመ፣

ሊሰናበት ይችላል።

3) በማናቸውም ሁኔታ አከናዋኙ ለባለሥልጣኑ አስቀድሞ ሳያሳውቅ የንብረት አስተዳዳሪውን ለመለወጥ አይችልም።

28. <u>በሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንዱ ውስጥ የጠባቂው ሚና እና ኃላፊነት</u>

1) የዚህ መመሪያ ምዕራፍ አምስት እንደተጠበቀ ሆኖ በሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት የሚያደርግ ፈንድ ጠባቂ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት።

ሀ) የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶችን እና የሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንዱን ባለመብትነትን የሚያረጋግጡ ሌሎች ሰነዶችን ጨምሮ በፈንዱ ፖርትፎሊዮ ውስጥ ያሉ ሀብቶችን መጠበቅ እና በአግባቡ መያዝ፣ እና
ለ) ከአከናዋኙ በሚቀበለው ተገቢ ትዕዛዝ መሠረት በጥበቃው ስር ያሉ ሀብቶችን በሚፈለገው ቅርጽ እና መንገድ ማስተላለፍ፣ መለዋወጥ እና ማድረስ።

2) የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች እና በ ሪል ስቴቱ ውስጥ ባለመብትነትን የሚያረጋግጡ ሌሎች ሰነዶች በፈንዱ ጠባቂው መያዝ አለበት።

29. <u>ስለ ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንዱ አስተዳደር</u>

የዚህ መመሪያ ምዕራፍ ስድስት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቢያንስ አንዱ የፈንዱ ቦርድ አባል ስለ ሪል ስቴት ኢንዱስትሪ ተጨባጭ የስራ እውቀት ያለው መሆን ይኖርበታል።

30. <u>የሪል ስቴት መረጃን ይፋ ስለማድረግ</u>

1) በዚህ መመሪያ ምዕራፍ ሁለት ስለ ክፍልፋዮች ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፈንዱ የአቅርቦት ሰነዶች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርባቸዋል።

   ሀ) የሪል ስቴቱን ባህሪ፣ አይነት እና ፈንዱ ኢንቨስት ሊያደርግበት ያቀደውን ገቢ የሚያስገኝ ሪል ስቴት እና የሪል ስቴት ልማት በመጥቀስ የንብረት ኢንቨስትመንቱን መጠን መግለጽ፣

   ለ) የታቀድውን የንብረት አስተዳዳሪ ፣ የንብረት አስተዳደር አገልግሎቶችን ለመስጠት የተደረገው ስምምነት እና ስለ ፈንድ ንብረት አስተዳደር የተመለከተ ማንኛውንም ሌላ መረጃ መያዝ፣

   ሐ) የፈንዱ አከናዋኝ፣ የንብረት አስተዳዳሪ እና ሌሎች ተሳታፊ ባለሞያ አካላት ልዩ ተግባራት፣ እና

   መ) ባለሥልጣኑ ለኢንቨስተሮች ጥበቃ እና ለገበያ ተዓማኒነት አስፈላጊ ሆኖ የሚያገኘው ሌላ ማንኛውም መረጃ።

2) የአቅርቦት ሰነዶቹ ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ አቅርቦት የሚገኘው ገቢ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና የታቀደውን የኢንቨስትመንት ተግባር ከተቀበሉት ገንዘብ እና ካፒታል ስራ ላይ የሚውሉበት የጊዜ ሰሌዳ ጋር መግለጽ ይኖርበታል።

31. <u>የሪል ስቴት ግመታ ሪፖርት</u>

1) ከፈንዱ ሃብት ሃያ በመቶ [20%] በላይ በሪል ስቴት ላይ ኢንቨስት ያደረገ ፈንድ ይህንኑ ሪል ስቴት በተመለከተ የሪል ስቴት ግመታ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

2) በዚህ መመሪያ ምዕራፍ 8፡ ክፍል 5 ግመታን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ-አንቀጽ 1 ላይ በተቀመጠው መሠረት የሪል ስቴት ተግባራት የሚያከናውን ፈንድ በዓመታዊ ሪፖርቱ የንብረት ግመታ ሪፖርትን ማካተት አለበት።
3) የሪል ስቴት ግመታ ሪፖርቱ ገለልተኛ እና የጸና ፈቃድ ባለው የንብረት ግመታ አገልግሎት ሰጭ መዘጋጀት አለበት።
4) የሪል ስቴት ግመታ ሪፖርቱ ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን የ ግመታ መረሆዎች፣ ፖሊሲዎች እና ሥነ-ስርዓቶችን ማክበር፤

ለ) በንብረቱ ላይ ቅኝት የተደረገባቸውን ቀናት መግለጽ፣

ሐ) የንብረቱን ባህሪ፣ ጥቅም፣ በታ እና የንብረቱ መብት የተያዘበትን የሕግ አግባብ እንደ ኪራይ ወይም የሊዝ ስርዓት የሚለውን የሚያሳይ ማጠቃለያን ጨምሮ ለንብረት ግመታው ዓላማ አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳዊ ንብረቶች በተመለከተ ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መረጃ መስጠት፣ እና

መ) የዋጋ ግመታው ከተደረገበት ቀን በኋላ ምንም አይነት ጉልህ ለውጥ እንዳልተከሰተ የሚገልጽ መግለጫ ካልተካተተበት በስተቀር የሽያጭ ሰነዱ ወይም አመታዊ ሪፖርት ከቀረበበት ከ አንድ (1) አመት በፊት ያልሆነ እያንዳንዱ ሪል ስቴት ንብረት የተገመተበትን ቀን መግለጽ፣

አለበት።

5) የሪል ስቴቱ ግመታ ሪፖርቱ በዋጋ ግመታው ጥቅም ላይ የዋሉ ደረጃዎች እና ዘዴዎችን መግለጽ አለበት።

ክፍል 5፡ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንዶች

32. ወሰን እና ገደቦች

1) በአማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ ውስጥ ያለን ጥቅም የሚወክሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከምዝገባ ነጻ በተደረጉ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽያጭ መቅረብ አለባቸው።
2) በግል ለሽያጭ ቀርቦ የተመሰረተ ፈንድ በግል እንደተያዘ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ የሚቆጠር ሲሆን፣ የሚያወጣቸው ክፍልፋዮችም በአዋጁ አንቀጽ 75(5) ላይ እንደተገለጸው በግል የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ያካትታሉ።
3) ለብቁ ኢንቨስተር ቀርቦ የተመሰረተ ፈንድ እንደ ብቁ ኢንቨስተር አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ የሚቆጠር ሲሆን፣ የሚያወጣቸው ክፍልፋዮችም በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ እንደተመላከተው የተገደቡ ይሆናሉ።

33. በንብረት ኢንቨስትመንት ላይ ኢንቨስት ስለሚያደርግ አማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ

1) በንብረት ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማራ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ በዚህ መመሪያ ምዕራፍ 4- ክፍል 3 ላይ የተመላከተው የሪል እስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ወሰን እና ግደቦች ተፈጻሚ ይሆንበታል።

2) በንብረት ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማራ አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ የአቅርቦት ሰነዶች የሚከተሉትን ጨምሮ በአንቀጽ 28 ላይ በተገለጸው በሪል እስቴት ላይ የተገለጹትን መግለጫዎች ማቅረብ አለበት፡
   ሀ) ከምዝገባ በስተቀር፣ በዚህ ምዕራፍ በተደነገገው መሠረት የሪል እስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ መስፈርቶችን የሚያከብር ከሆነ፣ እና
   ለ) መስፈርቱን የማያሟላ ከሆነ የሚከተሉትን ጨምሮ ከሪል እስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድ ምን እንደሚለየው መግለጫ፡
      i. የፈንዱ ፖርትፎሊዮ የሚከተተው የንብረት ኢንቨስትመንት ባህርይ እና ስብጥር፣
      ii. ከፈንዱ ኢንቨስትመንት እቅድ ጋር የተያያዙ ስጋቶች፣ እና
      iii. ሌሎች ጉልህ ልዩነቶች

34. <u>በአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ በቋሚነት መረጃን ይፋ ስለማድረግ</u>

አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንዱ በግዥ ቃል-ኪዳን ስምምነቱ ወይም በተያያዥ የሽያጭ አቅርቦት ሰነዶቹ ላይ በተቀመጠው መሠረት ቢያንስ በየዓመቱ ወይም በተደጋጋሚ የሚከተሉትን ለኢንቨስተሮች እና ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

ሀ) ለፈንዱ አከናዋኝ የሚከፈለውን ክፍያ እና ለፈንዱ ወይም ለማንኛውም ኢንቨስት አድራጊ ኩባንያ የሚከፈል ማንኛውም ክፍያዎች፣
ለ) በፈንዱ ላይ ማንኛውም ወሳኝ ተጠያቂነት ካለ እና እንደተነሳ፣
ሐ) በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ቦታ በህጋዊ ወይም ተቆጣጣሪ አካላት የሚደረጉ ማናቸውም ጥያቄዎች ወይም ህጋዊ እርምጃዎች፣
መ) አከናዋኙ፣ ወይም ጠባቂው ወይም ከእነርሱ ጋር ቅርበት ያለው ሰው፣ወይም ከካፒታል ገበያዎች ጋር በተገናኘ ሙግት ውስጥ ቢሆኑ ወይም ሲሳተፉ፣ እና
ሠ) ባለስልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጋይድላይን፣ በሰርኩላር ወይም በማስታወቂያ በሚጠይቀው ማንኛውም ሌላ መረጃ።

<u>ምዕራፍ አራት፣ ምዝገባ</u>

<u>ክፍል 1 ፡ የፈንድ ምዝገባ</u>

35. <u>ክልከላ</u>

1/ አንድን አክስዮን፣ የድርሻ ክፍልፋይ፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት በፈንዱ ውስጥ ያለን ጥቅም የሚወክሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በባለሥልጣኑ ሳይመዘገቡ ለሕዝብ ማቅረብ፣ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች ላይ መመዝገብ ወይም ዋጋ መቁረጥ እና ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ በኩል መግዛትም ሆነ መሸጥ አይቻልም።

2/ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ሳያሟላ በፈንዱ ውስጥ ያለን ክፍልፋይ የሚወክሉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሽያጭ አቅርቦት ማስታወቂያዎችን ማሳተም ወይም ማሰራጨት አይችልም።

ሀ) ፈንዱ በባለስልጣኑ ካልተመዘገበ

ለ) ለህዝብ ሽያጭ ከሚቀርቡ የፈንድ ክፍልፋዮች ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ማስታወቂያ ከባለሥልጣኑ አስቀድሞ ሳይፀድቅ እና በሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 53 የተመለከቱትን መስፈርቶች ሳያሟላ።

36. የምዝገባ ማመልከቻ አቀራረብ

1) ለባልስልጣኑ የሚቀርበው የምዝገባ ማመልከቻ በዚህ መመሪያ መሰረት መሆን አለበት።
2) የማመልከቻ ቅጹ በታሰበው የፈንድ አከናዋኝ ወይም በሌላ ተገቢው ፍቃድ በተሰጠው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ይቀርባል።
3) እንደተፈጻሚነቱ የምዝገባ ማመልከቻ ቅጹ፣ ደጋፊ ሰነዶች እና ሌሎች ለምዝገባው የሚያስፈልጉ መረጃዎች በበኮምፕዩተር የተጻፈ፣ ግልጽና በቀላሉ ሊነበብ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
4) ለባለስልጣኑ የሚቀርበው የማመልከቻ ቅጽ እና ደጋፊ ሰነዶች በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሊቀርቡ ይገባል።
5) ከማመልከቻው ጋር የሚቀርብ ማንኛውም መረጃ ወይም ሰነድ በሌላ ቋንቋ የሆነ እንደሆነ መረጃው ወይም ሰነዱ ከተረጋገጠ የአማርኛ ወይም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትርጉሙ ጋር አብሮ መቅረብ ይኖርበታል።
6) የማመልከቻ ቅጹ ቀን የተቀመጠለት፣ የተፈረመ እና በማመልከቻው የቀረቡ መረጃዎች በሙሉ የተሟሉ እና እውነተኛ መሆናቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ ሊያካትት ይገባል።
7) ሁሉም ማመልከቻዎች ማመልከቻው በሚገባበት ቀን በባለስልጣኑ የክፍያ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ክፍያ መፈፀሙን ከሚያሳይ የክፍያ ማስረጃ ጋር ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

37. የማመልከቻ ቅጽ

1/ የማመልከቻ ቅጹ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፣

ሀ) ማመልከቻውን ያቀረበው ሰው ስምና አስፈላጊ ዝርዝር፣

ለ) የሚመዘገበው ፈንድ ስራን የሚገልጽ በታሰበው የፈንድ አከናዋኝ በተገቢው ሁኔታ የተፈረመ የማመልከቻ ደብዳቤ፣

ሐ) ስለታቀደው ፈንድ ዝርዝር መረጃ፣

መ) ረቂቅ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ወይም እንደ አግባብነቱ ሌላ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድ፣ እና

ሠ) ረቂቅ የግዢ ቃልኪዳን ስምምነት።

2/ ፈንዱን አስመልክቶ የሚቀርበው መረጃ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል።

ሀ) የፈንዱን ስም እና በዚህ መመሪያ ምዕራፍ 3 በተገለጸው መሰረት የሚመዘገበው የፈንድ አይነት

ለ) የፈንዱን የኢንቨስትመንት አስተዳደር ቡድን የስራ ልምድና የሙያ ብቃት ያካተተ የማንነት መረጃ፣

ሐ) የእያንዳንዱ የቦርድ አባል የማንነት መረጃ እና በዚህ መመሪያ የተደነገገውን የአስተዳደር መረጃ ጃ፣

መ) በፈንድ አከናዋኙ፣ ለፈንዱ ቅርበት ባላቸው ሰዎች፣ ወይም ጉልህ ተፅዕኖ ያላቸው ሰዎች መዋጮ እና የያዙትን የካፒታል መጠን ጨምሮ ለፈንዱ የታቀደው የካፒታል አወቃቀር፣

ሠ) ለፈንዱ የታሰበው የካፒታል መጠን ዝርዝር መረጃ እና ለሚመዘገበው የፈንድ ዓይነት አነስተኛ የግዢ ቃልኪዳን ምዝገባ መጠን ትንተናን ጨምሮ ለእንደዚህ ዓይነቱ ፈንድ የታቀዱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ፣

ረ) የፈንዱ አከናዋኝ እና ጠባቂ የፈንዱን የታቀደ የኢንቨስትመንት ስራ ለመስራት እንዲሁም የዚህን መመሪያ መስፈርቶች ለማሟላት ያላቸውን የሰው ፣ የቴክኖሎጂ አቅም እና የመሰረተ ልማት ብቃት የሚያሳይ መረጃ፣

ሰ) የሚከተሉትን ጨምሮ በፈንዱ ውስጥ የሚሳተፉ ባለሞያ አካላት መረጃ እና ከእያንዳንዳቸው ጋር ያለው ስምምነት፣

i. እንደ አስፈላጊነቱ የኢንቨስትመንት አማካሪ ወይም የሸሪዓ አማካሪ፣

ii. የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገማች ድርጅት ወይም ሌሎች የግምታ አገልግሎት አቅራቢዎች ፈንዱ ለሚመዘገብበት የፈንድ ዓይነት አስፈላጊ የሆነ ሌላ ማንኛውም ባለሞያ፣

iii. በፈንድ ውስጥ የሚሳተፉ ሌሎች ባለሞያ አካላት፣

iv. የውጭ ኦዲተር፣ እና

v. ለእነዚህ ባለሞያ አካላት የሚከፈሉ ክፍያዎች።

ሸ) ባለሥልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግበትን የካፒታል ገበያ ተግባር ለመገምገም አስፈላጊ የሆነ እና አግባብነት ያለው ሌላ ማንኛውም መረጃ።

3/ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው ውስጥ የተቀመጡት አነስተኛ መስፈርቶች ቢኖሩም ባለሥልጣኑ በሚፈለገው የካፒታል ገበያ አገልግሎት አቅራቢ ላይ ተጨማሪ የፋይናንስ፣ የሰው እና የቴክኒክ ግብአቶች የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊጥል ይችላል።

ሀ) የፈንዱን መጠን፣

ለ) የአገልግሎት አቅራቢዎችን የሥጋት አስተዳደር አቅም፣

ሐ) የአገልግሎት አቅራቢዎች የሰራተኞች ሙያዊ ልምድ፣

መ) የአገልግሎት ሰጪዎች የአሠራር አቅም፣ ወይም

ሠ) የኢንቨስተሮችን ፍላጎት ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆነ ሌላ ማንኛውም ሁኔታ።

38. <u>የማመልከቻ ደጋፊ ሰነዶች</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 37 መሰረት ለባለስልጣኑ የቀረበው የማመልከቻ ቅጽ ከሚከተሉት ደጋፊ ሰነዶች ጋር አብሮ መቅረብ አለበት፣

ሀ) አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የወጣ የንግድ ምዝገባ የንግድ ፍቃድ የምስክር ወረቀት ቅጂ፣ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

ለ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN)፣ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው የግብር ሰነዶች፣

ሐ) የሚከተሉትን ጨምሮ የምስረታ ሰነዶች የተረጋገጠ ቅጂ፣

i. የሚከተሉትን የሚያሳይ የማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ፡-

1. የፈንድ ስራን ለማከናወን ያለውን የንግድ አላማ፣

2. በባለስልጣኑ የሚጸድቅ ኢንቨስትመንት ፖሊሲ አጭር መግለጫ፣

3. የፈንድ ስራውን የሚሰራው የፈንድ አከናዋኝ፣

ii. ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ባለሞያ አካላት ጋር የተገቡ ስምምነቶች፣

መ) ቢያንስ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያለውን የሚሸፍን ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ፣

ሠ) የሚከተሉትን ጨምሮ ለጉዳዩ የተደረገን ዝግጅት ማብራሪያ በመስጠት የተጻፉ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች፣

i. ደንበኛህን እወቅ እና በወንጀል የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አድርጎ ማቅረብን ስለመከላከል፣

ii. በስራው እና በፈንዱ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶችን ለይቶ ስለማወቅ፣ ስለመቆጣጠር፣ ስለመቀነስ እና ስለመከላከል፣

iii. ለፈንዱ እንዲሁም ለአከናዋኙ እንደተፈጻሚነቱ የስጋት አስተዳደር፣

ረ) ባለስልጣኑ ለፈንዱ ምዝገባ ማመልከቻ አስፈላጊ ነው የሚላቸው ሌሎች ማናቸውም መረጃዎች።

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 37 መሰረት ለባለስልጣኑ የሚቀርበው የማመልከቻ ቅጽ በፈንዱ ውስጥ ለተሰማሩት ለእያንዳንዱ የባለሞያ አካላት እንዲሁም የፈንዱን ቦርድ እና እንደተፈጻሚነቱ የኃላፊነቱ ያልተወሰነ ሸሪክ ብቁ እና ተገቢ የመሆን መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስፈልጉ መረጃዎችንና ሰነዶችን ያካተተ መሆን አለበት።

39. <u>የማመልከቻው ሂደት</u>

1/ የምዝገባ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ከቀረበ በኋላ ማመልከቻውን በተመለከተ ወደ ባለስልጣኑ ወይም ከባለስልጣኑ የሚወጣ ማንኛውም ግንኙነት በደብዳቤ መሆን አለበት።

2/ የምዝገባ ማመልከቻው ለባለሥልጣኑ ከገባ በኋላ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ባለስልጣኑ ማመልከቻውን ይመለከታል እንዲሁም ማመልከቻውን ማጽደቁን ወይም ውድቅ መደረጉን አልያም ማመልከቻው እንዲሻሻል፣ እንዲስተካከል ወይም በመረጃዎቹ ወይም በጉድለቶቹ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥ ሊጠይቅ ይገባል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ ባለስልጣኑ በማመልከቻው ላይ ያለውን መረጃ ወይም ጉድለት ለማረም፣ ለማሻሻል ወይም ለማብራራት አስተያየቱን ከሰጠ በኋላ እንደ አዲስ መቁጠር ይጀምራል፤ በማመልከቻው ላይ የሚደረግ ማንኛውም ቀጣይ ግምገማ እና ግንኙነት በሃያ (20) የስራ ቀናት ውስጥ መሆን አለበት

4/ ባለስልጣኑ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየት ከመስጠት መዘግየቱ የምዝገባ መግለጫውን የማፅደቅ ወይም ውድቅ የማድረግ ውጤት እንዳለው ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም።

40. የምዝገባ ማመልከቻው መጽደቅ

1) የምዝገባ ማመልከቻው ከጸደቀ በኋላ ፈንዱ ከባለስልጣኑ የፈንድ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ያገኛል።

2) በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ተፈጻሚ የሚሆነው መረጃን በቀጣይነት ይፋ ማድረግ እና የአመታዊ የተገኘነት ሪፖርቱ የባለስልጣኑ የህግ ማስከበር ግምገማ እንደተጠበቀ ሆኑ የፈንዱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት፡-

   ሀ) በዚህ መመሪያ ምዕራፍ 8 ስለፈንዱ መፍረስ በተደነገገው መሰረት በፈንዱ ወይም በተወካዩ ተመላሽ ካልተደረገ በስተቀር፣ ወይም

   ለ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ላይ በተደነገገው መሰረት ፈቃድ ለተሰጠው አከናዋኝ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ካልታገደ፣ ካልተሻረ ወይም ካልተሰረዘ በስተቀር፣

ፈንዱ እስከሚቆይበት የጊዜ ገደብ እና ቆይታ በየአመቱ መታደስ ይኖርበታል።

3) የፈንዱ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በባለስልጣኑ የክፍያ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት የተከፈለውን የማሳደሻ ክፍያ አባሪ በማድረግ የምስክር ወረቀቱ የቆይታ ጊዜ ከመጠናቀቁ አንድ (1) ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ በአከናዋኙ መቅረብ አለበት።

4) በፈንዱ ውስጥ ያሉት ክፍልፋዮች መመዝገብ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፡-

   ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ምዕራፍ ሦስት ክፍል 3 የተመለከተው የምዝገባ መግለጫ ግምገማ ሂደት ተፈጻሚ ይሆናል፤ እና

   ለ) የፈንዱ የድርሻ ክፍልፋዮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በዚህ ምዕራፍ ክፍል 2 መሰረት መሆን አለበት።

41. የማመልከቻው ውድቅ መደረግ

1) ባለስልጣኑ አመልካቹ በዚህ መመርያ ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች አማልቷል ብሎ ካላመነ ማመልከቻውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

2) ባለስልጣኑ ውሳኔውን በሚያሳውቅበት ጊዜ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ማመልከቻውን ውድቅ ለማድረጉ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በጽሁፍ ማቅረብ አለበት።

3) ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ ወይም ውድቅ የተደረገበት አመልካች ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ያደረጉትን ምክንያቶች እንዲያስተካክል ወይም ማብራሪያ እንዲያቀርብ ባለስልጣኑ እድል እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል።

4) ባለስልጣኑ የአመልካቹን ማሻሻያዎች ወይም ማብራሪያዎች ከተቀበለ በኋላ የመጨረሻ ውሳኔውን በአሥራ አምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ ያሳውቃል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ባለስልጣኑ በወሰነው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል በአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት በባለሥልጣኑ ውሳኔ ላይ ይግባኙን ማቅረብ ይችላል።

ክፍል 2: ምዝገባ የሚያስፈልጋቸው የፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮች

42. ተፈፃሚነት

1/ በፈንዱ ውስጥ ያሉ ክፍልፋዮች ለህዝብ የሚቀርቡት፣ ተደራሽ የሚሆኑት፣ የሚሸጡት ወይም ለሕዝብ በማንኛውም መልኩ እንዲተዋወቁ በዚህ የመመሪያው ክፍል መሠረት መመዝገብ አለባቸው።

2/ የፈንዱን የድርሻ ክፍልፋዮች ለሽያጭ ማቅረብ በዚህ መመሪያ መሰረት የደንበኛ ሳቢ መግለጫን ከማውጣት ነፃ የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ፈንዱን ለመመዝገብ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማቅረብ አለበት።

3/ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የጸደቀ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ሳይኖረው የድርሻ ክፍልፋዮችን መሸጥ፣ ማቅረብ ወይም ለሽያጭ ለማቅረብ መጠየቅ አይችልም።

43. የክፍልፋዮች የምዝገባ መግለጫ

1) በማንኛውም ሁኔታ ለሕዝብ የሚቀርቡ፣ የሚሸጡ፣ ወይም የሚተዋወቁ በፈንድ ውስጥ ያለን ድርሻ የሚወክሉ የድርሻ ክፍልፋዮች የምዝገባ መግለጫ፡-

   ሀ) በዚህ መመሪያና እንደ አግባብነቱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብና ግብይት መመሪያን እንዲሁም በየጊዜው ተሻሽለው በባለስልጣኑ የሚወጡ ማንኛውም ተያያዥ መመሪያዎች መሰረት፣ እና

   ለ) ባለስልጣኑ በሚያዘው ቅጽ መሰረት፣

   መቅረብ ይኖርባቸዋል።

2) በአንቀጽ 37 የተጠቀሰው የምዝገባ ቅጽ ከደንበኛ ሳቢ መግለጫው እና በአንቀጽ 38 የተጠቀሱት ደጋፊ ሰነዶች ጋር አንድ ላይ በመሆን የፈንዱን የድርሻ ክፍልፋዮች ለመመዝገብ እንደ ምዝገባ መግለጫ ተደርገው ይወሰዳሉ።

3) የምዝገባ መግለጫን ከማቅረብ መስፈርት ነፃ የሆኑ የፈንዶች የድርሻ ክፍልፋዮች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 5 መሰረት ከምዝገባ ነፃ የተደረጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ያካትታሉ።

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት ከምዝገባ ነፃ የሆኑ የፈንዱ የድርሻ ክፍልፋዮች እንደ አስፈላጊነቱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብና ግብይት መመሪያ ምዕራፍ ስድስት ላይ የተቀመጡት ለባለስልጣኑ ማስታወቅን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆንባቸዋል።

44. በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች

1) በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ ለተካተቱ መረጃዎች ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች የቀረበው መረጃ የተሳሳተ፣ አሳሳች፣ ወይም ያልተሟላ በመሆኑ የተነሳ ሰዎች በመረጃው ተመስርተው ለደረሰባቸው ኪሳራ ወይም ጉዳት በአንድነትና በተናጠል ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው።

2) ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

ሀ) ደንበኛ ሳቢ መግለጫው የሚመለከተውን የድርሻ ክፍልፋይ ያወጣው አውጪ ፈንድን፣

ለ) የፈንዱ አከናዋኝን፣

ሐ) በዚህ መመሪያ በተመዘገበ ፈንድ ውስጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነና በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ ወዲያው ወይም ወደፊት የፈንዱ ዳይሬክተር ለመሆን ተስማምቶ ስሙ እንዲጠቀስ የፈቀደ ማናቸውም ሰውን፣

መ) በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ወይም ማንኛውም የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ኃላፊ ለመሆን የተስማማ እና ይሄም በደንበኛ ሳቢ መግለጫው የተጠቀሰ ሰውን፣

ሠ) የድርሻ ክፍልፋዮቹን የሚያቀርበው አውጪው ካልሆነ የድርሻ ክፍልፋዮች አቅራቢውን፣

ረ) የድርሻ ክፍልፋዮቹን የሚያቀርበው ድርጅት ሆኖ ነገር ግን አውጪው ካልሆነ የደንበኛ ሳቢ መግለጫው በወጣ ጊዜ የአቅራቢው ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ እያንዳንዱ ሰውን፣

ሰ) ከዚህ ቀደም ባሉት አንቀጾች ባይካተትም የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን ወይም የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን ይዘቶች ወይም ማናቸውንም ክፍል አስመልክቶ ፈቃድ የሰጠ እያንዳንዱ ሰው።

3) አንድ ሰው ኃላፊነት የወሰደው ወይም ፈቃድ የሰጠው በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ ላለ ለተወሰነ ክፍል ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሰ) መሰረት ሃላፊ የሚሆነው ለተወሰነው ክፍል እና ጉዳዩ

ከተካተተበት መልክ እና አውድ አንጻር ስምምነቱን የሰጠበት የተወሰነው ክፍል የተካተተ ወይም በከፍተኛ ሁኔታ የተካተተ ከሆነ ብቻ ነው።

4) ከደንበኛ ሳቢ መግለጫው ወይም ከግዢ ጥያቄ ማቅረቢያ ሰነድ የሚመነጨ ኃላፊነትን የሚያቃልል፣ የሚገድብ፣ ወይም የሚያስወግድ ማንኛውም ስምምነት፣ ድንጋጌ፣ ማስጠንቀቂያ ወይም አባባል ተፈጻሚነት አይኖረውም።

45. <u>የፈንዱ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ቅርጽ እና ይዘት</u>

1) የፈንዱ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ኢንቨስተሮች መረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ እንዲወስኑ በቂ ፣ ግልጽ ፣ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የሚሰጥ እና አሳሳች ያልሆነ መሆን አለበት።
2) የፈንዱ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ቅርጽ እና ይዘት የሚከተሉትን የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ድንጋጌዎችን ማክበር አለበት።

    ሀ) አንቀጽ 36 የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ቅርጽ እና ይዘት፣

    ለ) አንቀጽ 37 በመጥቀስ ማካተት፣

    ሐ) የምዕራፍ አራት የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ይዘት ክፍል አንድ ጠቅላላ መስፈርቶች።

46. <u>የፈንዱ ይፋ የማድረግ መስፈርቶች</u>

1) የፈንዱ ይፋ የሚደረገው መረጃ :-

    ሀ) የሚመዘገበውን የፈንዱን አይነት እና ስለ ፈንዱ ዝርዝር እና ለፈንዱ የሚጠየቁ እና አስፈላጊ የሆኑ የባለሞያ አካላት ያሉ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን፣

    ለ) የሚከተሉትን አስፈላጊ መረጃዎች፡-

        i. በዚህ መመሪያ የዚህ ክፍል 29 የተደነገጉ ጉዳዮችን፣

        ii. የውጪ ኦዲተር ስምና አድራሻ፣

        iii. ቅርበት ያላቸው ሰዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ እና ከነዚህ ቅርበት ካላቸው ሰዎች ጋር የተደረገ ማንኛውም ስምምነት፣

        iv. ቀጣይነት ያለው ግምታ አስመልክቶ ለንብረት ምዘና ፖሊሲዎች እና ሂደቶች ሁሉን አቀፍ ይፋ ማድረግን ጨምሮ በቀላሉ ተገማች የሆኑ ወይም ለገበያ የሚውሉ ንብረቶችን ጨምሮ፣ የእንደዚህ አይነት ፖሊሲዎች እና ሂደቶች ቁጥጥር፣ እና

የግምገማ ዝግጅቶች ላይ የተደረገ ስምምነትን ጨምሮ የፈንዱ የፖርትፎሊዮ ግመታ ጋር በተያያዘ አስፈላጊው መረጃ፣ እና

v. በቋሚነት መረጃዎች ይፋ ሚደረጉበት አይነት፣ ባህሪ እና ድግግሞሽን የሚመለከት መረጃ።

2) የድርሻ ክፍልፋዮችን አስመልክቶ የሚወጣው መረጃ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብና ግብይት መመሪያ ምዕራፍ 4 ክፍል 8 መሰረት የማጠቃለያ ክፍሉ እና የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ይዘት የሚከተሉትን በሚገልጽ መልኩ መቅረብ አለበት።

ሀ) የቃል ኪዳን መግብያ ዝግጅት እና የፈንዱ የካፒታል መስፈርት፣

ለ) የታቀደውን የኢንቨስትመንት ስራ ለመፈፀም መሟላት ያለበት አነስተኛ የግዢ ቃልኪዳን መጠን ካለ፣ የተጠቀሰው መጠን ላይ ለመድረስ የሚጠበቀው ጊዜ እና ይህ ካልተሳካ የሚያስከትለው ውጤት፣ እና

ሐ) ተከፋይ እንዲሆን የሚጠበቀው የካፒታል፣

መ) ከድርሻ ክፍልፋዮቹ አቅርቦቱ የሚገኘው ገቢ በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ በተገለጸው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መሰረት ጥቅም ላይ እንደሚውል የሚያመላክት ግልጽ እና ጉልህ መግለጫ።

3) ንዑስ አንቀጽ 2(መ) ቢኖርም የፈንዱ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ከክፍልፋይ ምዝገባ በኋላ በስድስት (6) ወራት ውስጥ በአንድ (1) ዓመት እና በአሥራ ስምንት (18) ወራት ውስጥ ተግባር ላይ የሚውለውን አጠቃላይ የፈንዱ ካፒታል በመቶኛ ማመልከት አለበት።

4) የፈንዱ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ስጋቶች፣ የኢንቨስትመንት እቅዶች እና የድርሻ ክፍልፋዮቹ አቅርቦት ለታለመለው ኢንቨስተር በግልጽ በሚያስረዳ መልኩ "የስጋት አይነቶች" የሚል ክፍል ሊያካትት ይገባል።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከቱት የአደጋ ስጋቶች የኢንቨስትመንት ፖሊሲው በተጠቀሰው የኢንቨስትመንት ጊዜ ውስጥ ካልተሳካ ምን አይነት አማራጭ መንገዶችን እንደሚከተል እንዲሁም ኢንቨስተሮች ድምጽ የሚሰጡበት እድል የሚያገኙ ከሆነ ሊገልጽ ይገባል።

47. <u>ፈንዱን የተመለከተ ዝርዝር መረጃ</u>

1) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ፈንዱን በሚመለከት የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

ሀ) የፈንዱን ስም፣

ለ) የዋና መስሪያ ቤቱ አድራሻ፣ እንደ አግባብነቱ የቅርንጫፎቹ አድራሻ እና በኢትዮጵያ ያለው አድራሻ፣

ሐ) በባለስልጣኑ የተመዘገበበት የፈንድ አይነት እና ፈንዱ የተመዘገበበት ቀን፣

መ) በፈንዱ የታሰቡ የኢንቨስተር አይነቶች፣

ሠ) በሽያጭ ጊዜ ውስጥ ሊደረስበት የሚገባው ዝቅተኛ የግዢ ቃልኪዳን መጠን እና በመጀመሪያው የሽያጭ ጊዜ ውስጥ እዚህ መጠን ላይ ካልተደረሰ ምን ሊከሰት እንደሚችል።

2) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው የፈንዱን የቆይታ ጊዜ፣ የሚቋረጥበትን ግዜ እና የሚቋረጥበትን ሂደት በተመለከተ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃ መስጠት አለበት፡-

ሀ) ፈንዱ የሚቆይበት ጊዜ የተገደበ ከሆነ የሚቋረጥበትን ጊዜ፣

ለ) ፈንዱ የሚቆይበት ጊዜ ያልተገደበ ከሆነ ፈንዱ ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች፣ እና

ሐ) በፈንዱ መቋረጥ ሂደት ውስጥ የሚኖሩ የኢንቨስተሮች መብቶች።

48. <u>ኢንቨስትመንት ፖሊሲውን የተመለከተ መረጃ</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ ሙሉ በሙሉ መካተት አለበት።

2) የፈንዱ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ:-

ሀ) ፈንዱ በማንኛውም ጊዜ ከኢንቨስትመንት ፖሊሲው ጋር በሚስማማ መልኩ ኢንቨስት ማድረግ ያለበት፣ እና

ለ) በኢንቨስትመንት ፖሊሲ ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ጉልህ ለውጦች ከተመዘገቡት የድርሻ ክፍልፋይ ባለቤቶች ሁለት ሶስተኛ (2/3) ይሁንታን የሚጠይቅ፣

መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ ማካተተ አለበት።

49. ስለ ፈንዱ የድርሻ ክፍልፋዮች መረጃ

1) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው የፈንዱን ካፒታል አስመልክቶ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት።

ሀ) በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ በተካተተው የፋይናንስ መረጃ በሚሸፍነው ጊዜ ውስጥ የነበሩ ለውጦችን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ የአውጪውን ካፒታል ታሪክ አስመልክቶ ገለጻ፣

ለ) የቅርብ ጊዜ የሂሳብ መዝገብ ከወጣበት አንስቶ የሚከተሉት ላይ የሚቀርብ መግለጫ፣

i. የወጣው የአክስዮን ድምር ካፒታል፣

ii. የአውጪው ድምር ካፒታል፣

iii. ሙሉ በሙሉ የተከፈሉ የወጡ የድርሻ ክፍልፋዮች ቁጥር እና ሙሉ በሙሉ ያልተከፈሉ የወጡ የድርሻ ክፍልፋዮች ቁጥር፣

iv. የእያንዳንዱ አክስዮን የተጻፈ ዋጋ፣

v. በዓመቱ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ያሉ የተጣሩ ቀሪ አክስዮኖች ቁጥር።

2) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው የፈንዱን ክፍልፋዮች አስመልክቶ

ሀ) ከድርሻ ክፍልፋዮቹ ጋር የተያያዙ የመብቶች፣ ምርጫዎች እና ማናቸውንም ገደቦች መግለጫ፣

ለ) የጊዜ ገደቡን እና ምዝገባው ባይካሄድ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ጨምሮ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ የሚደረገው ምዝገባ ያለበትን ሁኔታ እና ምዝገባውን ለማካሄድ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎችን፣

በግልፅ የሚያሳዩ መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል።

50. የትርፍ ክፍፍል ፖሊሲ

1) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው፡-

ሀ) የትርፍ ክፍፍል ፖሊሲ እና ማንኛውም ተያያዥ ገደቦች መግለጫ፣

ለ) የሚከፋፈለው ገቢ እንዴት እንደሚወሰን ማብራሪያ፣ እና

ሐ) ክፍፍሉ የሚካሄድበት ወይም የሚከናወንበት በእያንዳንዱ አመት ውስጥ ያለ ቀን ወይም ቀናትን፣ ማካተት አለበት።

2) መግለጫው የክፍፍል ወይም የትርፍ ፖሊሰው እንደ ተፈጻሚነቱ በግብር ላይ የሚኖረውን ውጤት የሚገልጽ መረጃን ማካተት አለበት።

51. ስለ ፈንድ አከናዋኙ ዝርዝር መረጃ

1) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው በፈንድ አከናዋኙ ላይ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት።

ሀ) የተቋቋመበት ወይም የተመሰረተበት ቀን እና ቦታ፣

ለ) የአክሲዮን ወይም የባለቤትነት መዋቅር፣

ሐ) የዳይሬክተሮች ቦርድ አጭር የማንነት መረጃ፣

መ) ለፈንዱ አገልግሎት የሚሰጡ የአስተዳደር እና የኢንቨስትመንት ቡድን አባላት ልምዳቸውን እና ሙያዊ ብቃታቸውን ጨምሮ አጭር የማንነት መረጃ።

2) ደንበኛ ሳቢ መግለጫው የፈንድ አከናዋኙ እንደፈቃድ ያለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭ ያለበት መልካምሁኔታ እና በአከናዋኙ ውስጥ በተሿሚ እንደራሴነት ፈቃድ የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ስራ አስኪያጅ ስም የሚያመለክት መግለጫ ማካተት አለበት።
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም ፈንዱ የፈንድ አስተዳደርና የኢንቨስትመንት የምክር አገልግሎትን ከኢንቨስትመንት አማካሪ ወይም ለሸሪዓ ተገዥ የሆነ ፈንድ በሚሆንበት ጊዜ ከሸሪዓ አማካሪ ድርጅት የሚያገኝ ከሆነ ስለእነዚህ አማካሪዎች ልምድ፣ ሙያዊ ብቃት እና ፈቃድ ያለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭ ሁኔታን ጨምሮ አጭር መግለጫ ማካተት አለበት።
4) ለተመዘገበው የፈንድ አይነት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ማንኛውም ባለሞያ አካላት የሚከፈለውን ክፍያ እና ወጪን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ መቅረብ አለበት።
5) የፈንድ አከናዋኙ ለሶስተኛ ወገን በውል ያስተላለፈውን ማናቸውንም ስራዎች እና የተላለፉ ስራዎች ዝርዝር የሚመለከት መረጃ በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ መገለፅ አለባቸው።
6) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው የክፍያውን መጠን፣ የስሌቱን ዘዴና የክፍያውን ጊዜ ጨምሮ ለፈንድ አከናዋኙ እና ለሌሎች አስፈላጊ ባለሞያ አካላት የሚከፈሉትን ክፍያዎች ማካተተ አለበት።
7) ከሃላፊነቱ ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን ጨምሮ የፈንድ አከናዋኙ ስምምነት ወሳኝ ድንጋጌዎች ማጠቃለያ በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

52. ስለ ጥበቃ አደረጃጀት ዝርዝር መረጃ

1) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ስለ ፈንዱ ጥበቃ አደረጃጀት የሚከተሉትን ጠባቂውን በሚመለከት የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት።

ሀ) የጠባቂው የተመሰረተበትን ቀን እና ቦታ፣

ለ) የጠባቂው የአክሲዮን ወይም የባለቤትነት መዋቅር፣

ሐ) የጠባቂው የዳይሬክተሮች ቦርድ አጭር የማንነት መረጃ።

2) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው፡-

ሀ) ጠባቂው እንድ ፈቃድ ያለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭ ያለበት መልካም ደረጃን የሚገልጽ መረጃ፣ እና

ለ) ለፈንዱ አገልግሎቶችን ስለሚያቀርቡ የጠባቂው ቡድን አባላት መግለጫ፣

ማቅረብ አለበት።

3) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ከኃላፊነቱ ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን ጨምሮ የጠባቂው ወሳኝ ስምምነቶች ማጠቃለያ እንዲሁም ክፍያ እና ወጪዎችን ማካተት አለበት።

4) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ለጠባቂው የሚከፈሉትን ክፍያዎች ጨምሮ የክፍያውን መጠን፣ የስሌቱን ዘዴና ድግግሞሽን ማካተት አለበት።

53. <u>የፈንዱ ቦርድ</u>

1) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ስለ ዳይሬክተሮች ቦርድ እና አስተዳደር ስርዓቱ መረጃ ማካተት አለበት።

2) ስለ ቦርዱ የሚቀርበው መረጃ መረጃ የሚከተሉትን መያዝ አለበት።

ሀ) የእያንዳንዱን የቦርድ አባል ሙሉ ስም እና የስራ ድርሻ፣

ለ) የእያንዳንዱ የቦርድ አባል ሙያዊ ብቃታቸውን እና ዋና የንግድ እንቅስቃሴዎቻቸውን ጨምሮ አጭር መግለጫ ልምዳቸውን፣ እና

ሐ) የእያዳንዱ የቦርድ አባል የስራ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና ስሌት።

3) በፈንዱ እና በእያንዳንዱ የቦርድ ዳይሬክተር መካከል ያለው የአገልግሎት ውል ዋና ዋና ክፍሎች በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ በማጠቃለያ መልክ መገለጽ አለባቸው።

54. <u>ከፈንዱ ፖርትፎሊዮ ላይ ስለሚከፈሉ ክፍያዎች</u>

1) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው የሚከተሉትን ጨምሮ ከፈንዱ ውስጥ ለታቀደው የፈንድ አከናዋኝ ሊደረጉ የሚችሉትን ክፍያዎች በግልፅ እና በጉልህ ይፋ ማድረግ አለበት።

ሀ) ለአገልግሎቱ ክፍያ እና ያጋጠሙትን ወጪዎች ተመላሽ፣

ለ) የክፍያው ዓይነት እንዲሁም አስፈላጊ የክፍያ መጠኖች፣

ሐ) እንደዚህ አይነት ክፍያዎች እንዴት እንደሚሰሉ እና መቸ እንደሚከፈሉ፣ እና

መ) ለኢንቨስትሮች እንዴት ማስታወቂያ እንደሚሰጥ ጨምሮ በክፍያ ወይም ማካካሻ ላይ የሚደረጉ ለውጦች እንዴት እንደሚደረጉ።

2) የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ከፈንዱ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሁሉንም የሚከፈሉ ክፍያዎች ማካተት አለበት።

ሀ) ለባለሞያ አካላት የሚከፈል ክፍያ፣

ለ) ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከፈል ክፍያ፣

ሐ) በፈንዱ ለሶስተኛ ወገን የሚከፈል ማንኛውም አይነት ክፍያ፣

መ) ከፈንዱ ፖርትፎሊዮ ሊከፈል የሚችል ሌላ ማንኛውም አይነት ክፍያ እና ወጭዎች።

55. <u>ሌሎች ወሳኝ መረጃዎች</u>

1) ማንኛውም በፈንድ አከናዋኙ የሚታወቅ ወሳኝ መረጃ በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ላይ መካተት አለበት።

2) ለዚህ ዓላማ ወሳኝ መረጃ ማለት ኢንቨስተሮች ወይም አማካሪዎቻቸው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ላይ እንዲያገኙት የሚጠብቁት እና በፈንዱ ላይ ኢንቨስት የማድረግን ጥቅም እና ኢንቨስት በማድረግ ውስጥ ስለሚቀበሉት ስጋቶች መጠን እና ባህሪያት እንዲያመዛዝኑ የሚያስችላቸው መረጃ ማለት ነው።

56. <u>ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነድ</u>

1) ለሕዝብ የቀረቡ የድርሻ ክፍልፋዮች ለኢንቨስተሮች የሚቀርብ ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነድ ሊኖራቸው ይገባል።
2) ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነዱ በፈንዱ፣ በፈንድ አከናዋኙ ወይም ፈንዱን በሚወክሉ ሌሎች ሰዎች ከመታተሙ ወይም ጥቅም ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ በባለስልጣኑ መጽደቅ አለበት።
3) ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነድ አንድ መደበኛ ኢንቨስተር መረጃን መሠረት ያደረገ የኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያሳልፍ እና ኢንቨስት በማድረግ ውስጥ ስለሚቀበለው ስጋቶች መጠን እና ባህሪያት እንዲያመዛዝን የሚያስችላቸውን መረጃ ጨምሮ በሚያዝ አጭር በሆነ መንገድ እና ቴክኒካል ባልሆነ ቋንቋ መፃፍ አለበት።

4) ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነድ የሚከተሉትን መረጃዎች ጨምሮ ስለፈንዱ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ማካተተ አለበት።

ሀ) የፈንዱ ስም እና አይነት፣

ለ) የፈንድ አከናዋኙ ስም፣

ሐ) በባለስልጣኑ የጸደቀው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ አጭር መግለጫ፣

መ) ከፈንዱ ውስጥ ካለው ኢንቨስትመንት ጋር ተያይዘው ከሚመጡ ስጋቶች ጋር የተገናኘ ከተገቢው መመሪያ እና ማስጠንቀቂያ ጋር የኢንቨስትመንት የስጋት እና ጥቅም አጭር መግለጫ፣

ሠ) አስፈላጊና ተገቢ ሲሆን የፈንዱ አፈፃፀም ሁኔታዎች፣

ረ) ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች እና ወጪዎች፣

ሰ) በባለስልጣኑ አስፈላጊ ተብሎ የሚታሰብ ሌላ ማንኛውም መረጃ።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 አስፈላጊ የሆኑት ጉዳዮች ይፋ ሲሆኑ ኢንቨስተሩ ምንም ዓይነት ሌላ ሰነድ ሳያጣቅስ ሊረዳው በሚችለው መልኩ መሆን ይገባል።

6) ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነዱ "ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ" የሚል ቃላትን በግልጽ መጠቀምና ሰነዱ የደንበኛን ሳቢ መግለጫ ተጨማሪ እንጂ ምትክ አለመሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ አለበት።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸው ቢኖርም የቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነድ በነዚህ ብቻ ሳይገደብ ከታቀደው ኢንቨስትመንት ጋር የተገናኘ እንደ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ፣ ዓመታዊ ሪፖርት እና ሌሎች ወቅታዊ ሪፖርቶች እና በቀጣይነት ይፋ የተደረጉ መረጃዎች የት እና እንዴት እንደሚገኙ ጨምሮ ማቅረብ አለበት።

8) በባለስልጣኑ የጸደቀ ቁልፍ የኢንቨስተር መረጃ ሰነድ ከትርጉም በስተቀር ያለ ማሻሻያ ወይም አባሪ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

ክፍል 3፡ ከምዝገባ ነጻ የተደረጉ የፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮች

57. ከምዝገባ ነጻ የተደረጉ የአማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድ አቅርቦት

1) አማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንዱ፣ የፈንድ አክናዋኙም ሆነ ሌላ ፈንዱን ወይም አከናዋኙን ወክሎ የሚሰራ ማንኛውም ሰው የአማራጭ የኢንቨስትመንት ፈንድን ጥቅም የሚወክል ማንኛውም

ሰነድ ሙዓለ ንዋይን በማስተዋወቅ ወይም ሰነዶችን በማውጣት ለህዝብ ሽያጭ ማቅረብ ወይም መጋበዝ አይችልም።

2) የአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድን የሚመለከቱ ተያያዥ የግዥ ቃልኪዳን ስምምነትን ጨምሮ የሽያጭ አቅርቦት ሰነዱ የግዥ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት፣ ሽያጭ ወይም ሌላ ካፒታል የማሰባሰብ ስራ በፈንዱ፣ በአከናዋኙ ወይም አደራጆችን ጨምሮ ፈንዱን ወይም አከናዋኙን ወክሎ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም ሰው ከመጀመሩ በፊት ለባለስልጣኑ መቅረብ አለባቸው።
3) ለአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ ብቁ የሆኑ ኢንቨስተሮች ለባለሥልጣኑ የቀረበውን ማንኛውንም የመረጃ ማስታወሻ እና የግዥ ቃልኪዳን ስምምነትን ጨምሮ አንድ ዓይነት የሽያጭ አቅርቦት ሰነድ ሊሰጣቸው ይገባል።

58. <u>ከምዝገባ ነጻ ለሆኑ ሽያጮች የኢንቨስተር መረጃ</u>

1) ከምዝገባ ነጻ የሆነ አቅርቦትን የሚመለከቱ የሽያጭ አቅርቦት ሰነዶች በዚህ መመሪያ የዚህ ምዕራፍ ክፍል 2 የተመለከቱትን መስፈርቶች እንደ አግባብነቱ ማሟላት አለባቸው።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአቅርቦት ሰነዶቹ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው።

ሀ) በፈንዱ ላይ ተፈፃሚነት ያለው የቁጥጥር እና የሕግ ማዕቀፍ አጠቃላይ ገለጻ፣

ለ) ከምዝገባ ነጻ በተደረገው አቅርቦት ውስጥ ባሉት የድርሻ ክፍልፋዮች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው የግብይት ገደቦች፣

ሐ) እያንዳንዱ ኢንቨስተር ለመመዝገብ የሚያስፈልገውን አነስተኛ መጠን እና የግዥ ቃልኪዳን የሚገባበትን እና ክፍያ የሚፈጸምበትን አግባብ የሚያካትት የግዥ ቃልኪዳን ስምምነት መግለጫ፣

መ) ኢንቨስተሮች ከፈንዱ ሊወጡ የሚችሉባቸው አማራጮች ካሉ፣

ሠ) ለኢንቨስተሮች የሚላኩት የፋይናንስ እና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ዝርዝር እና የሚላኩበት ጊዜያት፣ እና

ረ) ባለሥልጣኑ የሚጠይቀው ሌላ ማንኛውም መረጃ።

3) ፈንዱ ሁለት አይነት ኃላፊነት ባለበት የሽርክና ማህበር መልክ ከተቋቋመ ከምዝገብ ነፃ ለሆነው አቅርቦት የቀረበው ሰነድ ላይ ሃላፊነቱ ያልተወሰነው ሽሪክ የአቅርቦት ሰነዱ በታተመበት ቀን ትክክለኛ ስለመሆኑ ኃላፊነቱን እንደሚቀበል የሚገልጽ መግለጫ ማካተት አለበት።

59. <u>የግዥ ቃልኪዳን ስምምነቱ ይዘት</u>

1) በአማራጭ ኢንቨስትመንት ፈንድ የግዥ ቃልኪዳን ስምምነት ውስጥ ያለው መረጃ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት።

ሀ) ስለፈንዱ እና ስለግዢ ቃልኪዳን መስፈርቶች ዝርዝር መረጃ፣

ለ) ስለ ግዥ ቃልኪዳኑ ጊዜ እና ክፍያ እንዲሁም የካፒታል መጠን፣

ሐ) የትርፍ ክፍፍል ፖሊሲ፣

መ) የፈንድ አከናዋኙ እና የኢንቨስተሮች መብት እና ግዴታ፣

ሠ) ገዢ ህጎች፣

ረ) ኢንቨስተሮች ከፈንዱ ሊወጡ የሚችሉባቸው መንገዶች።

<u>ክፍል 4፡ የውጭ ፈንዶችን ስለመመዝገብ</u>

60. <u>የውጭ ፈንዶችን የሚመዘገቡበት ተጨማሪ መስፈርቶች</u>

1) ባለስልጣኑ በውጪ ፈንዶች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን በማጽደቅ ለውጭ ፈንዶች እውቅና ሊሰጥ ይችላል።

2) ለውጪ ፈንዱ ፈቃድ በሰጠው ወይም እንዲንቀሳቀስ በፈቀደለት ሃገር ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል የተሰጠ የመልካም ቁመና ደብዳቤ መቅረብ አለበት።

3) የውጪ ፈንዱ ቢያንስ የሚከተሉትን የሚያጠቃልል በቂ የሀገር ውስጥ እንቅስቃሴ ሊኖረው ይገባል፣

ሀ) በኢትዮጵያ የተመዘገበ ቢሮ፣

ለ) በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያለው የውጭ ኦዲተር፣ እና

ሐ) ቢያንስ አንድ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው የቦርድ አባል።

4) የውጪ ፈንድ እንደ አግባብነቱ በኢትዮጵያ እውቅና ባገኘ ማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግምጃ ቤት ወይም ፈቃድ በተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪ ኩባንያ ውስጥ የቅርብ ግዜ የባለአክሲዮኖችን ዝርዝር ማስመዝገብ አለበት።

5) ባለስልጣኑ የውጪ ፈንድን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻን በዚህ ክፍል በተገለጹት መስፈርቶች መሰረት ያጸድቃል።

61. <u>የውጪ ፈንድ አስተዳደር እና አመራር</u>

1) ማንኛውም የውጪ ፈንድ፦

ሀ) በኢትዮጵያ ፈንዶች ላይ ተፈፃሚ የሆኑ የድርጅት አስተዳደር መስፈርቶችን መተግበር፣

ለ) በባለሥልጣኑ ፍቃድ የተሰጠው ጠባቂ መሾም፣ እና

ሐ) ከባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው የፈንድ አከናዋኝ እንዲኖረው ማድረግ ይኖርበታል።

2) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አከናዋኙ በፈንዱ ላይ እንደሚሰማራበት እንቅስቃሴ አይነት የካሳ መድን እንዲኖረው ሊጠይቅ ይችላል።

<u>ክፍል 5፡ ማስተዋወቅ እና ስርጭት</u>

62. <u>ማስታወቂያዎች</u>

1) ክፍልፋዮችን ሽያጭ አስመልክቶ የሚደረግ ማስታወቂያ ወይም አቅርቦት ከመደረጉ በፊት የፈንዱ ምዝገባ ሰርተፍኬት ያስፈልጋል።
2) አንድ ማስታወቂያ ወይም ህትመት ፦

ሀ) የፈንዱ ስም እና መግለጫ ማካተት፣

ለ) ፈንዱ የተመዘገበበት ቀን

ሐ) የፈንዱ ክፍልፋዮች በባለስልጣኑ የተመዘገቡ ወይም ከምዝገባ ነጻ መደረጋቸውን

3/ ማስታወቂያው የሚከተሉትን ግልጽ ማሳሰቢያዎች ማካተት አለበት።

ሀ) ባለሥልጣኑ ለፈንዱ የፋይናንስ ጤናማነት ወይም በዚህ ረገድ ለተሰጡ መግለጫዎች ወይም አስተያየቶች ትክክለኛነት ኃላፊነቱን እንደማይወስድ፣

ለ) ፈንዱ የድርሻ ክፍልፋዮች ጋር ተያያዥ ስጋቶች እንዳሉት፣ እና

ሐ) ፈንዱ በየጊዜው ትርፍ የሚከፍል ከሆነ የፈንዱ የድርሻ ክፍልፋይ ዋጋ እና የትርፍ ክፍፍል ሊቀንስም ሊጨምርም እንደሚችል።

4/ ማንኛውም ለህዝብ ወይም ለተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል የሚቀርብ ማስታወቂያ ወይም ጥሪ ከመውጣቱ ሶስት (3) ያላነሱ የስራ ቀናት በፊት ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት።

63. **<u>በማስታወቂያዎች ላይ የአከናዋኙ ኃላፊነት</u>**

1) የፈንድ አከናዋኙ ፈንዱን ለሚመለከት እያንዳንዱ ማስታወቂያ ኃላፊነት ይወስዳል።
2) የፈንድ አከናዋኙ በማስታወቂያው ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ይዘቶች ለመደገፍ አስፈላጊ የሆኑ ሁሉንም መረጃዎች እና ማስረጃዎች መያዝ አለበት።
3) የፈንድ አከናዋኙ ማስታወቂያ በሚያወጣበት ጊዜ የፍትሃዊ አቀራረብ እና ሙሉ መረጃን ይፋ የማድረግ መርሆዎችን ማክበር ያለበት ሲሆን የተሳሳተ ወይም አሳሳች የሆኑ የአፈፃፀም ወይም የአፈፃፀም ነክ መረጃዎችን ማቅረብ የለበትም።
4) የፈንድ አከናዋኙ እንደ አግባብነቱ በአፈጻጸም ላይ የተመሰረቱ ክፍያዎች እና ወጭዎች እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎችን እና እነዚህም በፈንዱ ገቢ ላይ እንዴት እንደተንጸባረቁ መግለጽ አለበት።

ምዕራፍ አምስት፣ ባለሞያ አካላት

ክፍል 1፣ አከናዋኝ

64. **<u>የአከናዋኝነት ውል</u>**

የአከናዋኝ ሹመት ከአከናዋኙ ውጭ በቦርዱ በተፈረመ የተጻፈ፣ በተገቢው አካል የተረጋገጠ እና በባለስልጣኑ የጸደቀ ውል መሆን አለበት።

65. **<u>የአከናዋኙ በፈንዱ ዉስጥ ስለሚኖረው ድርሻ</u>**

1) አከናዋኙ ለህዝብ ሽያጭ በቀረበ ፈንድ ከተጠቀሰው ካፒታል ከአስር በመቶ (10%) የማይበልጥ የሀብት ወይም የካፒታል መዋጮ ማድረግ ይችላል።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ 1 መሠረት ካፒታል ያዋጣ አከናዋኝ የፈንዱ ክፍልፋዮች በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ከተመዘገቡበት ቀን አንስቶ ለሁለት ዓመታት ያህል ኢንቨስትመንቱን ማቆየት አለበት።

66. **<u>የአከናዋኝ ኃላፊነቶች</u>**

1) አከናዋኙ የሚከተሉትን ጨምሮ ለፈንዱ ተግባራት አስተዳደር እና አፈጻጸም ኃላፊነት አለበት፡
   ሀ) የፈንዱን የዕለት ተዕለት አጠቃላይ የንግድ ሥራን ማስተዳደር፣
   ለ) የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መቅረጽ፣
   ሐ) የፈንዱ ሁሉም የኢንቨስትመንት ተግባራት በኢንቨስትመንት ፖሊሲው እና አግባብነት ያላቸውን ህጎች ባከበረ መንገድ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ፣
   መ) በጠባቂው የተያዙ የፈንዱን ንብረቶችን በሚፈለገው አኳኋን እና መንገድ ማስተላለፍ፣ መለወጥ ወይም ማስረከብ፣

ሠ) ብቁ የስጋት አስተዳደር የአሰራር ስርአት፣ ሂደትና መቆጣጠሪያ ማዘጋጀት እና መያዝ፣

ረ) ለኢንቨስተሮች ልዩ ጥቅም ሲባል ስጋቶችን መለየት፣መገምገም፣ መቀነስ እና መከታተል፣

ሰ) የፈንዱን አፈፃፀም በቋሚነት እና በወቅቱ መገምገም፣

ሸ) አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና ስምምነቶች መሰረት የሚፈለጉትን ሁሉንም ይፋ መሆን የሚገባቸው መረጃዎች እና ሪፖርቶች በወቅቱ ማዘጋጀት እና ማቅረብ፣ እና

ቀ) ፈንዱ የጸና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

67. <u>ስለ አከናዋኙ ምግባር</u>

1) አከናዋኙ ፈንዱን፡-

   ሀ) በቅንነት እና በፍትሃዊነት፣

   ለ) በችሎታ፣ በጥንቃቄ እና በትጋት፣

   ሐ) ለፈንዱ የድርሻ ክፍልፋይ ያዡች ልዩ ጥቅም፣ እና

   መ) በስራው ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩትን የጥቅም ግጭቶች በአግባቡ በመፍታት፣ ማስተዳደር አለበት።

2) የንግድ ሕጉ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው አከናዋኙ የሚከተሉትን ያካተተ የጥቅም ግጭት ፖሊሲ እና አሰራር ስርዓት ለፈንዱ ሊኖረው ይገባል።

   ሀ) የተዛማጅ ወገን ግብይቱን ጉልህነት የሚወስኑ መስፈርቶች፣

   ለ) ሁሉንም የተዛማጅ ወገን ግብይት ለክፍልፋይ ያዡች በተገቢው ጊዜ ለማጸደቅ እና ሙሉ ለሙሉ ይፋ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች እና

   ሐ) የሚከተሉትን ክልከላዎች ጨምሮ ለፈንድ አከናዋኝ፣ ለባለሞያ አካላት ወይም አግባብነት ላላቸው ቅርበት ያላቸው ሰዎች ልዩ ጥቅም የሚያስገኙ ሁኔታዎች ላይ ያለ ክልከላ፡-

      i. የፈንድ አከናዋኙ ከፈንዱ ኢንቨስተሮች ይልቅ የራሱን ጥቅም ማስቀደም፣
      ii. ከአከናዋኙ ጋር ቅርበት ላላቸው ሰዎች ወይም ወገኖች ልዩ ጥቅም የሚያስገኙ የኢንቨስትመንት እድሎችን መስጠት፣ እና
      iii. ለተመረጡ ኢንቨስተሮች ልዩ ጥቅም ያላቸው ክፍያዎች ወይም ስምምነቶች።

3) የፈንድ አከናዋኙ ማናቸውም የተዛማጅ አካላት ግብይቶች ወይም ስምምነቶች፥

ሀ) በእውነተኛ የገበያ ዋጋ መሰረት እንዲሁም በመደበኛ የገበያ ስርአት በገለልተኛ ወገኖች መካከል ከሚደረግ የዋጋ ድርድር ሁኔታዎች ያላነሱ መሆናቸውን፣

ለ) ከፈንዱ የድርሻ ክፍልፋይ ያዦች ተገቢ የሆነው ይሁንታ በማግኘት የተከናወነ መሆኑን፣ እና

ሐ) በዚህ መመሪያ ምዕራፍ ሰባት በተቀመጠው መሰረት ይፋ መሆናቸውን፣

ማረጋገጥ አለበት።

68. <u>የተገዥነት ዝግጅት</u>

1) አከናዋኙ ለሚያስተዳድረው እያንዳንዱ ፈንድ የተጻፈ የተገዢነት ፖሊሲዎችን እና የአሰራር ስርዓቶችን ማዘጋጀት እና ብቁነታቸውን በየዓመቱ መገምገም ይኖርበታል።

2) የተገዢነት ፖሊሲዎቹ እና የአሰራር ስርዓቶቹ ቢያንስ የሚከተሉትን መሸፈን አለባቸው፡-

ሀ) የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሂደቶችን፣

ለ) የፈንዱን በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የግብይት እና የሽያጭ ልምዶችን፣

ሐ) የውስጥ አዋቂ መረጃን እና ሌሎች በአዋጁ ውስጥ የተከለከሉ ተግባራትን ማስተዳደር፣

መ) ይፋ የሚደረግ መረጃን፣ የግብይት እና ሌሎች ማስታዎቂያዎችን መገምገም እና ማጽደቅ፣

ሠ) የፈንዱ የንግድ ሥራ ቀጣይነት ዝግጅቶችን፣

ረ) የመረጃ ጥበቃ ጉዳዮችን፣

ሰ) የመዝገብ አያያዝ ልምዶችን፣

ሸ) የጥቅም ግጭት አስተዳደርን፣

ቀ) የተዛማጅ ወገኖች ግብይቶችን መለየት እና ማስተዳደርን፣ እና

በ) ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎች ማክበርን።

3) የፈንዱ አከናዋኝ ለሚያስተዳድረው እያንዳንዱ ፈንድ የተገዢነት ፖሊሲዎች እና አሰራር ስርዓቶችን ለማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት የሕግ ማስከበር መኮንን መሰየም ያለበት ሲሆን ስያሜውም በፈንዱ ቦርድ መጽደቅ ይኖርበታል።

4) የተሰየመው የሕግ ማስከበር መኮንን ብቃት እና እውቀት ያለው እንዲሁም ለፈንዱ አይነት ተስማሚ መሆን አለበት።

5) የተሰየመው የሕግ ማስከበር መኮንን አግባብነት ላለው ለፈንዱ ቦርድ የኦዲት፣ ሥጋት እና የህግ ማስከበር ኮሚቴ ሪፖርት ያደርጋል።

69. <u>የአከናዋኙ የሥጋት አስተዳደር ግዴታዎች</u>

1) የፈንዱ አከናዋኝ ለእያንዳንዱ ለሚያስተዳድረው ፈንድ የፈንዱን ባህሪ፣ ደረጃ እና ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያስገባ በቂ እና በአግባቡ የተሰነደ የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ ማዘጋጀት፣ መያዝ እና መፈጸም አለበት።

2) የስጋት አስተዳደር ፖሊሲው አከናዋኙ፣

   ሀ) ለሚያስተዳድረው ፈንድ ወሳኝ ሊሆኑ የሚችሉትን የአሰራር ስጋትን ጨምሮ ፣ የገበያ፣ የገንዘብ አከልነት እና የተቃራኒ ወገን ስጋቶችን እና ማናቸውም ሌሎች ስጋቶችን ለመለየት እና ለመገምገም የሚያስችል፣

   ለ) አሁን ያለው የስጋት መጠን ከፈንዱ የስጋት የማስተናገድ ወሰን ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማረጋገጥ እነዚህን ስጋቶች ለማስተዳደር፣ እና

   ሐ) የፈንዱ ስጋት የማስተናገድ ወሰን ላይ ተጨባጭ ወይም ተገማች የሆነ ጥሰት በሚኖርበት ጊዜ የፈንዱ ኢንቨስተሮች ጥቅም ለማስጠበቅ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ እነዚህን ስጋቶች ለመለካት እና ለመቆጣጠር፤

   የሚያስችሉትን ዘዴዎች፣ መሳሪያዎች እና መዋቅሮችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

3) ፈንዱን አሉታዊ በሆነ መልኩ ሊጎዱ የሚችሉ በገበያው ሁኔታ ዉስጥ ሊፈጠሩ በሚችሉ ለውጦች ምክንያት የሚመጡ ስጋቶችን ለመከላከል አከናዋኙ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው የስጋት ምዘና እና የስጋት ዝርዝር ትንታኔ ያከናውናል።

4) አከናዋኙ የስጋት አስተዳደር ፖሊሲውን ሙሉነትና ውጤታማነት መዳሰስ፣ መከታተል እና መገምገም እና በስጋት አስተዳደር ሂደት ውስጥ ያሉ ጉድለቶችን ለመፍታት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

5) በስጋት አስተዳደር ፖሊሲው ላይ የሚደረጉ ማናቸውም አይነት ጉልህ ለውጦች በቦርዱ መጽደቅ እና በባለስልጣኑ መታወቅ አለባቸው።

70. <u>የአከናዋኙ መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>

1) አከናዋኙ በፈንዱ ቦርድ ፈንዱን በሚመለከት ማንኛውም መረጃ ሲጠየቅ ለተጠየቁ ጉዳዮች መረጃና ዝርዝር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

2) አከናዋኙ የፈንዱ ጠባቂ የፈንዱ ግብይትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ሲጠይቅ ለፈንዱ ጠባቂ መስጠት አለበት።

3) የፈንዱ አከናዋኝ፣

ሀ) ለፈንዱ የሚከፈል ማንኛውም ክፍያዎች እና ወጪዎች እና ለአከናዋኙ የሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያዎችን፣

ለ) የሽያጭ አቅርቦት ሰነዶች ወይም የመመስረቻ ሰነዶች ካሉ ማንኛውም አይነት የሰነዶቹን ድንጋጌወች ጥሰት ሲኖር እና ሲከሰት፣

ሐ) በቁልፍ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ቡድን ውስጥ ያለ ማንኛውም ጉልህ ለውጥ፣ እና

መ) በዚህ መመሪያ የተጠየቁትን ይፋ መደረግ ያለባቸውን ሁሉንም መረጃዎች፣

ለኢንቨስተሮች ይፋ ማድረግ አለበት።

71. አከናዋኙ ሪኮርዶችን መያዝ ያለበት ስለመሆኑ

አከናዋኙ፣

ሀ) የፈንዱን ተገቢ መዝገቦችና ሪኮርዶች እንዲሁም ተግባራትና ግብይቶች ቢያንስ ለ አሥር (10) ዓመታት ይዞ ማቆየት፣ እና

ለ) እነዚህን መዝገቦችና ሪኮርዶች በፈንድ ጠባቂው እንዲመረምሩ በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ፣

አለበት።

72. አከናዋኙ ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

አከናዋኙ ፦

ሀ) ከዚህ ቀደም ለባለሥልጣኑ የቀረቡ መረጃዎች በኋላ ላይ ሐሰት ወይም አሳሳች ሆነው ከተገኘ ወይም ቀደም ሲል በቀረበው መረጃ ላይ ለውጥ ካለ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ፖሊሲውን ወይም ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎች እና መመሪያዎችን የሚጥስ ማንኛውም ክስተት ከተፈጠረ፣ ወይም

ሐ) በድርሻ ክፍልፋይ ባለቤቶች የተላለፈ ማንኛውንም ልዩ ወይም አስቸኳይ ውሳኔ ካለ፣

ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ እንዲሁም በሃያ አራት (24) ሰአት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

73. አከናዋኙ ስራዎችን በውል ለሦስተኛ ወገን አሸጋግሮ ስለማሠራት

1) አከናዋኙ በቅድሚያ ከቦርዱ የጽሁፍ ይሁንታ እና የባለስልጣኑን ቅድመ-ይሁንታ በማግኘት የአስተዳደር ተግባራቱን በውል ለሶስተኛ ወገን አሸጋግሮ ሊያሰራ ይችላል።

2) ባለሥልጣኑ አከናዋኙ የተወሰኑ ወይም ሁሉንም ተግባራቶቹን በውል ለሶስተኛ ወገን አሸጋግሮ ከማሰራት ሊከለክል ይችላል።

3) አከናዋኝ፣

ሀ) ስራው የሚሸጋገርለትን ወገን ለመምረጥ የተገቢነት ጥናት ሥርዓቶች እና ቀጣይነት ያለው ክትትል ለማድረግ አስፈላጊ የክትትል መዋቅሮች እንዲኖሩ ማድረግ፣

ለ) ስራው የሚሸጋገርለት ወገን የተሸጋገረለትን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል በቂ ልምድ እና የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣ እና

ሐ) ማናቸውንም ተግባራቶቹን በማሸጋገር የሰጣቸው ሰዎች ሁሉ ለሚፈጽሟቸው ድርጊቶች ወይም ግድፈቶች ተጠያቂ መሆን፣

አለበት።

4) ማንኛውንም ሥራውን በማሸጋገር የሰጠውን ወገን የሚመለከት ማንኛውም ክፍያና ወጪ በፈንድ አከናዋኙ የሚከፈል ሲሆን ከፈንዱ ፖርትፎሊዮ አይከፈልም።

74. የአከናዋኙ ከሥራ ስለመልቀቅ

1) አከናዋኝ :-

ሀ) በአከናዋኝነት ስምምነቱ ላይ ከፍ ያለ ቀን ካልተቀመጠ በስተቀር የሚለቅበትን ምክንያት የሚጠቅስ የስድስት (6) ወር የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለቦርዱ በመስጠት፣ እና

ለ) የፈንዱን ቀጣይነት ለማስቀጠል ያለውን አደረጃጀት በመጥቀስ ከሥራ የመልቀቅ ሀሳቡን ለባለሥልጣኑ በማሳወቅ፣

ከሥራ ለመልቀቅ ይችላል።

2) የአከናዋኙ ከሥራ መልቀቅ ተፈጻሚ የሚሆነው በዚህ መመሪያ መሠረት አዲስ አከናዋኝ ሲሾም ነው።

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተቀመጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ መሠረት አዲስ አከናዋኝ ካልተሾመ ፈንዱ በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈርሳል።

75. አከናዋኙን ስለማሰናበት

1) ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሲከሰት አከናዋኙ በቦርዱ መሰናበት ይኖርበታል።

ሀ) አከናዋኙ ፈቃዱ በባለሥልጣኑ ሲታገድበት ወይም ሲሰረዝበት፣

ለ) በአከናዋኙ የስምምነት ውል ላይ አከናዋኙን ከስራ ሊያስባርር የሚችል ሁኔታ ተደርጎ የተቀመጠ ምክንያት ሲከሰት፣

ሐ) የአከናዋኙ ንብረት ማጣራት ሂደት ውስጥ ከገባ ወይም የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፣ ወይም

መ) አከናዋኙ እንዲሰናበት በፈንዱ ክፍልፋይ ባለቤቶች አስቸኳይ ውሳኔ ከተላለፈ።

2) ቦርዱ አከናዋኙን ለማሰናበት ማቀዱን ለባለስልጣኑ ማሳወቅ እና የሚሰናበተውን አከናዋኝ ለመተካት የተደረገውን ዝግጅት ዝርዝር ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

3) በቦርዱ የሚደረግ አከናዋኙን የማሰናበት ድርጊት የባለስልጣኑን ቅድመ-ይሁንታ ካላገኘ እና ተተኪ አከናዋኝ ካልተሾመ እና ይህም በባለስልጣኑ ካልጸደቀ በስተቀር የጸና አይሆንም።

76. አከናዋኙ ከሥራ ከለቀቀ ወይም ከተሰናበተ በኋላ ስለሚኖሩበት ግዴታዎች

አከናዋኙ ሥራውን ከለቀቀበት ወይም ከሥራው ከተሰናበተበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን ጨምሮ የፈንዱን አስተዳደር የሚመለከቱ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ለፈንዱ ማስረከብ አለበት።

ሀ) በአከናዋኙ የተያዙ የፈንድ ሪኮርዶች፣

ለ) የኢንቨስትመንት ወጪዎች እና የተገመቱ የትርፍ ግኝቶች ዝርዝር ጨምሮ የፈንዱን ፖርትፎሊዮ ዝርዝር፣

ሐ) ከማንኛውም ያልተጠናቀቁ ግብይቶች ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎች እና መግለጫዎች፣

መ) በአከናዋኙ ስም የተመዘገቡ የፈንዱ ማንኛቸውም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር የተዛመዱና በአግባቡ የተፈጸሙ የዝውውር ሰነዶች፣ እና

ሠ) ከፈንዱ ጋር የተያያዘ ሌላ ማንኛውም መረጃ።

77. አዲስ አከናዋኝ ስለመሾም

1) በዚህ መመሪያ የተቀመጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ባለስልጣኑ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ምክንያታዊ የሆነ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዲያስችለው አከናዋኙ ፈንዱ ሌላ አከናዋኝ የመሾም ጥያቄውን ማቅረብ ይኖርበታል።

2) ፈንዱ በአዲሱ አከናዋኝ እና በፈንዱ መካከል የተደረገውን ስምምነት በአግባቡ የተፈረመ ቅጂ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።

ክፍል 2፣ የፈንዱ ጠባቂ

78. የፈንዱ ጠባቂ ለመሆን የሚያስፈልግ ብቁነት

1) የፈንዱ ሀብቶች በአዋጁ አንቀጽ 90(1) በተቀመጠው መሰረት ራሱን በቻለ አካል ይዞታ ስር መሆን አለበት።
2) በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አንቀጽ 65 ላይ የተደነገገው ቢኖርም የፋይናንስ ተቋማት ከመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪያቸው ተቃውሞ እንደሌለ የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ እና በባለስልጣኑ በማስጸደቅ የፈንድ ጠባቂ ሊሆኑ ይችላሉ።

3) ጠባቂው በአሰራሩ ከአከናዋኙ ጋር ገለልተኛ መሆኑን ማሳየት ያለበት ሲሆን ባለስልጣኑም የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

ሀ) የጠባቂውን ስርዓቶች እና መቆጣጠሪያዎች፣

ለ) የፈንዱን ንብረቶች ከጥፋት ወይም ከኪሳራ ለመጠበቅ የጠባቂውን የመለየት ችሎታን፤

ሐ) ጠባቂው ራሱን የቻለ የተገኘነት፣ የውስት ኦዲት እና ስጋት አስተዳደር መዋቅር ያለው መሆኑን፤

መ) ማንኛውንም ተዛማጅ ግንኙነቶች ጨምሮ የጠባቂውን የሰው ኃይል እና አስተዳደር፣

ሠ) ተጨባጭ ወይም ሊፈጠሩ የሚችሉ የጠባቂው የጥቅም ግጭቶችን፣

ረ) መ) እያንዳንዱ አገልግሎት ሰጪ ለኢንቨስተሮች ልዩ ጥቅም እና በተቀመጠላቸው ኃላፊነት መሠረት መስራታቸውን ለማረጋገጥ ባለስልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ ያመነባቸው ሌሎች መስፈርቶችን።

79. <u>የጠባቂነት ስምምነት</u>

1) የፈንዱ ጠባቂ ሹመት በፈንዱ እና በጠባቂው በተፈረመ የጽሁፍ ውል መረጋገጥ ይኖርበታል።

2) በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አንቀጽ 84 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠባቂነት ውል የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል።

ሀ) የጠባቂውን የኃላፊነትና የግዴታ ወሰንን ጨምሮ በፈንዱ፣ በአከናዋኙ እና በጠባቂው መካከል ያለውን ግንኙነት የሚይዙ ድንጋጌዎች፣ እና

ለ) በአዋጁና በባለሥልጣኑ መመሪያዎች የተጣሉበትን ተግባራትና ግዴታዎች እንደሚከተል እና እንደሚያከብር ጠባቂው የሚሰጠው ማረጋገጫ።

80. <u>የጠባቂው ኃላፊነቶች</u>

1) የፈንዱ ንብረት እና ሀብቶች ለጥበቃ ዓላማ ወይም ለምቹ አያያዝ ሲባል በጠባቂ ሥር መሆን አለባቸው።

2) ጠባቂው የፈንዱ ሀብቶች ለፈንዱ ክፍልፋይ ያዦች ጥቅም በመመስረቻ ሰነዶች፣ በባለስልጣኑ መመሪያዎች እና አግባብ ባላቸው ሁሉም ሕጎች ድንጋጌዎች መሠረት በአግባቡ መያዛቸውን እና መተዳደራቸውን ማረጋገጥ አለበት።

3) ጠባቂው ለሚከተሉት ተግባራት ኃላፊነት አለበት።

ሀ) የክፍልፋይ ግዢ ቃልኪዳን ከፍያዎችን ከኢንቨስተሮች መቀበል፣

ለ) ለፈንዱ የሚከፈሉ ማናቸውም ገቢዎችን መሰብሰብ እና መያዝ፣ እና
ሐ) በፈንዱ እና በፈንዱ ስም የተቀበለውን ገንዘብ ማስቀመጥ።

4) ጠባቂው ከፈንዱ የማቋቋሚያ ሰነዶች ጋር የሚጣረሱ ካልሆኑ በስተቀር የፈንዱን ኢንቨስት ሊደረግ የሚችል ገንዘብን ኢንቨስት ማድረግን በተመለከተ ከአከናዋኙ የሚሰጡትን ትዕዛዞች ማከናወን አለበት።

5) ጠባቂው ሁሉንም የስብሰባ ማሳወቂያዎች፣ ሪፖርቶች፣ ሰርኩላሮች፣ የውክልና መጠየቂያዎች እና እንደ አንድ የተመዘገበ የክፍልፋይ ያዢ የተቀበላቸውን ሌሎች ማናቸውም መሰል ሰነዶችን በተቀበለ በሀያ አራት (24) ሰዓት ውስጥ ለአከናዋኙ ማስተላለፍ አለበት።

6) ጠባቂው የፈንዱን ንብረቶችና ሀብቶች ጥበቃ ዝግጅቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

81. **<u>የፈንድ ጠባቂው የጥበቃ ግዴታ</u>**

1) ጠባቂው ለጥበቃ ተግባር የተሰጡት ንብረቶች እና ሀብቶች ከሚከተሉት ተለይተው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለበት።

ሀ) ከራሱ ሀብቶች፣
ለ) ከአከናዋኙ እና ከአከናዋኙ ጋር ቅርበት ካላቸው ሰዎች ሀብቶች፣
ሐ) ከኢንቨስትመንት አማካሪ ወይም የሸሪዓ አማካሪ እና ከእነርሱ ጋር ቅርበት ካላቸው ሰዎች ሀብቶች፣ እና
መ) ከሌሎች ፈንዶች ሀብቶች።

2) ጠባቂው በሚከተሉት ዉስጥ የሚወድቅ ካልሆነ በስተቀር በአደራ የተሰጡ ንብረቶችን በመያዣ ወይም በማበደር የሚደረጉ ግብይቶች እንደማይከናወኑ ማረጋገጥ አለበት።

ሀ) ግብይቱ የሚፈጸመው ለፈንዱ ከሆነ፣
ለ) ግብይቱ ለፈንዱ ጥቅም እና ለፈንዱ ክፍልፋይ ባለቤቶች ጥቅም ሲባል ከሆነ፣ እና
ሐ) ጠባቂው የአከናዋኙን ህጋዊ ትዕዛዞችን እየተገበረ ከሆነ።

82. <u>የጠባቂነት ስራዎችን በውል ለሦስተኛ ወገን አሸጋግሮ ስለማሠራት</u>

1) በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አንቀጽ 81 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠባቂው ፡-

ሀ) የማቋቋሚያ ሰነዶቹ የሚፈቅዱ ካልሆነ፣

ለ) በፈንዱ ቦርዱ ካልጸደቀ፣ እና

ሐ) ውል ከመግባቱ በፊት ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ካላሳወቀ እና ባለስልጣኑም ካላጸደቀው፣

በስተቀር ማንኛውም ሥራውን ወይም ግዴታውን ለሦስተኛ ወገን አሸጋግሮ ማሰራት አይችልም።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ጠባቂው የፈንዱን ባለመብትነት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ጠባቂ የመሆንን ተግባር ለማንም ሰው አሸጋግሮ ማሰራት አይችልም።

3) ማንኛውም ተግባራቱን በሽግግር ያሰራ እንደሆነ ጠባቂው፡-

ሀ) ለሽግግሩ ተጨባጭ ምክንያት መኖሩን ማሳየት፣

ለ) ጠባቂው ሥራውን በሽግግር ሊሰጥ ያሰበውን ማንኛውም ሦስተኛ አካል በሚመርጥበት እና በሚሾምበት ጊዜ በብልሃት፣ ተገቢውን ጥንቃቄ እና ትጋት ማድረግ፣

ሐ) ሦስተኛው አካል ከፈንዱ ዓይነት፣ ተፈጥሮ እና ውስብስብነት ጋር በቂ እና ተመጣጣኝ የሆነ የአሰራር መዋቅር እና የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ) ማንኛውም ተግባሩን በሽግግር ለሰጠው ማንኛውም ተወካይ ድርጊት ወይም ግድፈት ተጠያቂ መሆን፣

ይኖርበታል።

4) አሸጋግሮ ከማሰራቱ ጋር የተገናኙ ማናቸውም ክፍያዎችና ወጭዎች በጠባቂው መከፈል ያለባቸው ሲሆን ከፈንዱ ፖርትፎሊዮ ሊከፈሉ አይችሉም።

83. <u>የጠባቂው ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ</u>

ጠባቂው፡-

ሀ) አስቀድሞ ለባለሥልጣኑ የቀረበ መረጃ በኋላ ላይ ሐሰት ወይም አሳሳች ሆኖ ከተገኘ ወይም ቀደም ሲል በቀረበው መረጃ ላይ ለውጥ ካለ፣ ወይም

ለ) የማቋቋሚያ ሰነዶችን፣ የዚህ መመሪያ ወይም ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸውን መመሪያዎችን ወይም ሕጎችን የሚቃረን ማንኛውንም ድርጊት በአከናዋኙ ሲፈጸም፣

ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ እና በሃያ አራት (24) ሰአት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

84. <u>የጠባቂው ከሥራ መልቀቅ እና መተካት</u>

1) የጠባቂው ከሥራ መልቀቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 74 ላይ በተገለጸው አኳኋን ይሆናል።

2) ፈንዱ ተፈጻሚነት ባለው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ተተኪ ጠባቂ ማግኘት ካልቻለ፣ ጠባቂው በክፍልፋይ ያዠች ስብሰባ ላይ ፈንዱ እንዲፈርስ ምክረ-ሐሳብ ማቅረብ ይኖርበታል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የጠባቂውን ሐሳብ ባለአክሲዮኖች ያልተቀበሉት እንደሆነ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ አዲስ ጠባቂ እስኪሾም ድረስ ጠባቂው በሥራው ላይ ይቆያል።

4) የጠባቂው ከሥራ መልቀቅ ተፈጻሚ የሚሆነው የፈንዱ ሐብት እና ንብረት አዲስ ለተሾመው ጠባቂ ከተላለፈበት ቀን አንሥቶ ነው።

85. <u>ጠባቂውን ስለማሰናበት</u>

1) የባለስልጣኑ ቅድመ-ይሁንታን ማግኘት እና ለጠባቂው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

    ሀ) በካፒታል ገበያ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አንቀጽ 66 መሠረት፣ ወይም
    ለ) የጠባቂ ለውጥ ለኢንቨስተሮች ጥቅም አስፈላጊ እንደሆነ በተረጋገጠበት በፈንድ አከናዋኙ ወይም በቦርዱ በሚቀርብ በጽሁፍ ማመልከቻ መሠረት፣

   ጠባቂው ከሥራው ሊሰናበት ይችላል።

2) በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አንቀጽ 66(1) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለፈንዱ ክፍልፋይ ባለቤቶች የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት ቦርዱ ጠባቂውን ሊያሰናብተው ይችላል።

3) የጠባቂውን መሰናበት ባለስልጣኑ ካላጸደቀው በስተቀር የጸና አይሆንም።

ክፍል 3፣ ሌሎች ባለሞያ አካላት

86. የሌሎች ባለሞያ አካላት ሹመት

1) የፈንድ አከናዋኙ የሚከተሉትን ጨምሮ በባለሥልጣኑ የተመዘገበውን የፈንድ ዓይነት ለማስተዳደር የሚያስፈልጉትን ባለሞያ ወገኖች መሾም አለበት።

   ሀ) የንብረት አስተዳዳሪ፣

   ለ) የሸሪዓ አማካሪ፣ ወይም

   ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 89 መሠረት ሌላ ማንኛውም የኢንቨስትመንት አማካሪ።

2) የሚከተሉትን ጨምሮ ለፈንዱ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ማናቸውም ባለሞያ ወገኖችን ፈንዱ ይሾማል።

   ሀ) የውጭ ኦዲተር፣ እና

   ለ) የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገማች ድርጅት ወይም ሌሎች የግምታ አገልግሎት የሚሰጡ አካላትን።

3) በአከናዋኙ ወይም በቦርዱ የሚደረግ ሌላ ማንኛውም ባለሞያ ወገኖች ሹመት ከሹመቱ መሠረታዊ ድንጋጌዎች መግለጫ ጋር በአቅርቦት ሰነዶቹ ወይም በቀጣይነት መረጃን ይፋ በማድረጊያ ሰነዶች ላይ ለኢንቨስተሮች መገለጽ አለበት።

4) በአስፈላጊ የባለሞያ ወገኖች ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ በጽሁፍ ከሚቀርብ ማስታወቂያ ጋር በ ሀያ አራት (24) ሰዓት ውስጥ ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል።

87. የውጭ ኦዲተሮች

1) ፈንዱ በሚመዘገብበት ጊዜ እና ከዚያ በኋላ የውጭ ኦዲተር ያስፈልገዋል።

2) የፈንዱ የውጭ ኦዲተር ከአከናዋኙ፣ ከጠባቂው፣ ከፈንዱ ቦርድ እና ለፈንዱ አገልግሎት ከሚሰጥ ከሌላ ማንኛውም ባለሞያ አካል ገለልተኛ መሆን ይኖርበታል።

88. የሸሪዓ አማካሪ

1) የኢስላሚክ ፈንድ ተግባራትን ለማከናወን ያሰበ አከናዋኝ የሸሪዓ አማካሪን መሾም አለበት።

2) የሸሪዓ አማካሪው የፈንዱ ሁሉም ተግባራት አግባብነት ባለው አካል የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

3) በአከናዋኙ የሚፈጸሙ የፈንዱ ሃብት ወይም ንብረት ግዥ እና ሽያጮች ተፈጻሚነት ያላቸውን የሸሪዓ መስፈርቶች የማይጥሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሸሪዓ አማካሪውን ማማከር አለበት።

4) የሸሪዓ አማካሪው ፈንዱ የሸሪዓ መስፈርቶችን ማክበሩን የሚያረጋግጡ ወቅታዊ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለአከናዋኙ ማቅረብ አለበት።

89. <u>የአማካሪዎች ከሥራ መሰናበት ወይም መልቀቅ</u>

1) አግባብነት ባለው ስምምነት የበለጠ ጊዜ ካልተቀመጠ በስተቀር አንድ አማካሪ ለአከናዋኙ እና ለቦርዱ የሦስት (3) ወር የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከሥራ ሊለቅ ይችላል።

2) አንድ አማካሪ፣

   ሀ) ፈቃዱ በባለስልጣኑ ከታገደ ወይም ከተሰረዘ፣

   ለ) በአማካሪነት ስምምነት ውል ላይ ከስራ ሊያስባርር የሚችልን ሁኔታ ተደርጎ የተቀመጠን ምክንያት ከተነሳ፣ ወይም

   ሐ) አማካሪውን ለማሰናበት ወይም እንዲሰናበት በፈንዱ ውሳኔ ከተላለፈ።

   ከሥራ ሊሰናበት ይችላል።

3) ስለታሰበው አማካሪን ከሥራ የማሰናበት ሀሳብ ዝርዝር መረጃ ለባለስልጣኑ ሊቀርብ ይገባል።

<u>ክፍል 4፣ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች</u>

90. <u>ክፍያዎችና ወጭዎች</u>

1) ክፍያዎችና ወጭዎች የሚከፈሉት በማቋቋሚያ ሰነዶች የተፈቀዱ እና ተጨባጭ፣ ፍትሃዊ እና ግልጽ በሆነ መንገድ የተሰሉ ከሆነ ብቻ ነው።

2) የማቋቋሚያ ሰነዶቹ የሚከተሉትን መግለጽ አለባቸው።

   ሀ) የሚከተሉትን ተገቢነት ያላቸው ሁኔታዎችን ጨምሮ ለጠባቂው የሚከፈለው ክፍያ መጠን እንዴት እንደሚወሰን፣

      i. የሚከፈለውን ክፍያ ትክክለኛ መጠን ወይም ዋጋ፣
      ii. ክፍያዎቹ የሚከፈሉባቸው ጊዜያት፣
      iii. ክፍያዎቹ እንዴት እና መቼ እንደሚከፈሉ፣ እና
      iv. ሊከፈል የሚችለው ከፍተኛው ክፍያ መጠን ወይም ዋጋ፣ እና

ለ) ከፈንዱ ጋር የተገናኙ ተግባራትን በመፈጸም ሂደት ውስጥ የወጡ ወጪዎች እንዴት ተመላሽ እንደሚሆኑ።

3) አከናዋኙ ለፈንዱ አገልግሎት እንዲሰጡ የውል ስምምነት ከገባባቸው ባለሞያ አካላት የሚከፈለውን ክፍያ ይፋ ማድረግ አለበት።

4) ክፍያዎች እና ወጭዎች በአገልግሎት ሰጭው ስህተት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት የሚመነጩ ካልሆነ በስተቀር ከፈንዱ ሃብት ተከፋይ ይሆናሉ።

ምዕራፍ ስድስት ፣ አስተዳደር

ክፍል 1፣ ፈንዱን ስለመቆጣጠር

91. የዳይሬክተሮች ቦርድ

1) እያንዳንዱ ፈንድ :-

ሀ) በአክሲዮን ማኅበር ወይም በሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አይነት የተቋቋመ ከሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ወይም

ለ) ሁለት አይነት ሀላፊነት ያለበት የሽርክና ማኅበር ሆኖ ከተቋቋመ አቻ አካል፣

ሊኖረው ይገባል።

2) ቦርዱ ቢያንስ አምስት ድምጽ መስጠት የሚችሉ አባላት ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን ሰብሳቢውን ጨምሮ አብላጫዎቹ አባላት ገለልተኛ ሊሆኑ ይገባል።

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አላማ የማንኛውም ፈንድ የቦርድ አባል ገለልተኛ የሚባለው :-

ሀ) ከማናቸውም ባለሞያ አካላት ጋር ቅርበት ያለው ሰው ካልሆነ፣

ለ) ከማናቸውም ባለሞያ አካላት ጋር ጉልህ የሆነ የገንዘብ፣ የንግድ ወይም የስራ ግንኙነት ከሌለው፣

ሐ) የአከናዋኙ ተቀጣሪ ካልሆነ፣

ነው።

4) የፈንዱ አከናዋኝ ድምጽ መስጠት የማይችል የቦርድ አባል ሊሆን ይችላል።

5) ቦርዱ በፈንድ እና በኢንቨትመንት አስተዳደር፣ በፋይናንስና ግመታ አገልግሎት፣ በኦዲትና ስጋት አስተዳደር እንዲሁም በሕግ ማስከበር ስራዎች ልምድ ያላቸውን ጨምሮ ተገቢው ሙያዊ ብቃት ባላቸው ሰዎች ስብጥር ሊዋቀር ይገባል።

6) እያንዳንዱ የቦርዱ አባል የብቁ እና ተገቢነት መመዘኛዎችን ማሟላት አለበት።

7) ቦርዱ ማንኛውም ሰው በቦርድ አባልነት ሲሾም ወይም አባልነቱ ሲያበቃ ለባለስልጣኑ ወድያውኑ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

92. የቦርዱ ሚና

1) ቦርዱ የኢንቨስተሮቹን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የፈንዱን ስራ አመራርና የአሰራር ሁኔታ ውጤታማ በሆነ እና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

2) ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፡-

ሀ) የፈንድ አከናዋኙን፣ ጠባቂውን፣ የውጭ ኦዲተሩን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገማች ድርጅትን ወይም ሌላ የግምታ አገልግሎት ሰጪ አካልን መሾም እና ሹመትን መሻር፣

ለ) የፈንዱ ስራ አመራርና ኢንቨስትመንቶች በፈንዱ የማቋቋሚያ ሰነዶችና በኢንቨስትመንት ፖሊሲው መሰረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ) የፈንድ አከናዋኙ የማቋቋሚያ ሰነዶችና ኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን በተቃረነ ሁኔታ የሰራቸውን ስራዎች ማስተካከሉን ማረጋገጥ፣

መ) የፈንዱ ጠባቂ ስራውን በጠባቂ ስምምነቱ መሰረት ማከናወኑን ማረጋገጥ፣

ሠ) የማቋቋሚያ ሰነዶችን ወይም የኢንቨስትመንት ፖሊሲውን በመጣስ ከፈንዱ ንብረት ወይም ሃብት የተከፈሉ ክፍያዎችን በሚመለከት ጠባቂው ማስተካከያ ማድረጉን ማረጋገጥ፣

ረ) የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ላይ የሚኖሩ ለውጦችን መገምገም፣

ሰ) የፈንዱ ሃብትና ንብረት ግመታ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርዓቶች ላይ የሚነሱ ጉዳዮችን መፍታት፣

ረ) በፈንዱ የሚከፈሉ የትርፍ ክፍፍል ክፍያዎችን ፣ የአገልግሎት ክፍያዎችን እና ወጪዎችን ማፅደቅ፣

ሰ) የሒሳብ ሪፖርቶችን እና በቀጣይነት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎችን ማጽደቅ፣

ሸ) ማናቸውንም የጥቅም ግጭቶች በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት መከታተልና መፍታት፣

ቀ) ፈንዱ ተገቢው የሕግ ማስከበር፣ ኦዲት እና ስጋት አስተዳደር አሰራር ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣

በ) ባለሞያ አካላቶች ተገቢው ፈቃድ ያላቸውና ሁሌም ለፈንዱ ተስማሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ተ) ሌላ ማንኛውም ስትራቴጂካዊ ውሳኔዎች መወሰን፡፡

3) ቦርዱ :-

ሀ) ትክክለኛ የአስተዳደር እና የሂሳብ አያያዝ ሂደቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ዘዴዎች መተግበራቸውን፣ እና

ለ) ስጋቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ ክትትል እና አስተዳደር እንዲደረግባቸው ተለይተው መታወቃቸውን፣

ለማረጋገጥ የሚያስችል ተገቢ ስርዓቶች፣ ሂደቶች እና አሰራሮች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት።

4) ቦርዱ የፈንዱ ሒሳብ በውጭ ኦዲተር መመርመሩን እና የፋይናንስ መግለጫዎች በማቋቋሚያ ሰነዶች ላይ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ይፋ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት።

5) ቦርዱ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ የተሰየመውን የሕግ ማስከበር መኮንን የሕግ ማስከበር ሪፖርቱን እንዲያቀርብ ማድረግ አለበት።

6) ቦርዱ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አንቀጽ 162 የተደነገጉትን የሙያ ስነምግባሮች መከተል አለበት።

93. <u>የቦርድ ኮሚቴዎች</u>

1) ቦርዱ የቦርድ አባላትን ብቻ ያካተተ የኦዲት፣ ስጋት እና የህግ ማስከበር ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።
2) ቦርዱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩን የሚመለከቱ ዳይሬክተሮችን ያካተቱ ሌሎች ኮሚቴዎችን ማቋቋም ይችላል።
3) ቦርዱ የሚቋቋሙትን ኮሚቴዎች ስብጥርና ሥልጣን በማጣቀሻ ደንቦች ይወስናል።
4) የቦርዱ ሰብሳቢ የኦዲት፣ ስጋት እና ህግ ማስከበር ኮሚቴ(ዎች) አባል መሆን አይችልም።
5) አከናዋኙ የኦዲት፣ ስጋትና ህግ ማስከበር ኮሚቴ(ዎች) አባል መሆን አይችልም።
6) የኦዲት፣ ስጋት እና ህግ ማስከበር ኮሚቴ(ዎች) በገለልተኛ ዳይሬክተር መመራት አለባቸው።

94. <u>የጥቅም ግጭቶች</u>

1) ቦርዱ :-

ሀ) ፈንዱ የጥቅም ግጭትን ለመለየት፣ ለመቆጣጠር እና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ስርአቶች ያሉት መሆኑን ያረጋግጣል፣

ለ) ማንኛውንም የጥቅም ግጭቶች የኢንቨስተሮቹን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ይቆጣጠራል እንዲሁም ይፈታል፣ እና

ሐ) የጥቅም ግጭትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በቃለ ጉባዔ ጭምር በአግባቡ ተመዝግበው መያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት።

2) ቦርዱ የተዛማጅ ወገኖች ግብይቶች በድርሻ ክፍልፋይ ባለቤቶች ማስጸደቅን ጨምሮ በፈንዱ በጸደቁ የጥቅም ግጭት ፖሊሲዎች መሰረት መፈጸማቸውን ማረጋገጥ አለበት።

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አላማ ቦርዱ የሚከተሉትን ማየት ይኖርበታል፡

ሀ) ማንኛውንም ከተዛማጅ ወገኖች ጋር የሚደርግን ግብይት፣ ውል፣ ስምምነት እና ማሻሻያዎቻቸውን፣

ለ) ማንኛውንም ለተዛማጅ ወገኖች የአገልግሎትና ሌሎች ክፍያዎችን መፈጸምን የሚያካትቱ ስምምነቶች፣

ሐ) በውል ማስተላለፍ ወይም በውክልና ለተዛማጅ ወገኖች የሚሰጡ ማናቸውም ስራዎች።

ክፍል 2፣ የአሰራር ሁኔታ

95. በፈንዱ ላይ የሚደረጉ ለውጦችን በክፍልፋይ ያዦች ስለማፀደቅ

1) አከናዋኙ የሚከተሉትን ጨምሮ በፈንዱ ላይ ሊደረጉ የታሰቡ ለውጦችን ከማድረጉ በፊት ቢያንስ የሰላሳ (30) ቀናት የጽሁፍ ማስታወቂያ ለባለስልጣኑ መስጠት አለበት፡-

    ሀ) የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ወይም የማቋቋሚያ ሰነዶች ላይ የሚደረጉ ለውጦችን፣

    ለ) ማንኛውም ውህደት፣ ጠቅልሎ መያዝ ወይም ሌላ ጥምረት ወይም የፈንዱን መፍረስ።

2) በፈንዱ ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ጉልህ ለውጦች በክፍልፋይ ያዦች ሁለት ሶስተኛ ድምጽ መጽደቅ አለባቸው።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸው በፈንዱ ላይ የሚደረጉ ጉልህ ለውጦች የሚከተሉትን ይጨምራል:-

    ሀ) የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ላይ የሚደረጉ ለውጦች፣

    i. ፈንዱ ኢንቨስት የሚያደርግበት ሃብት ወይም ንብረት አይነቶች፣
    ii. ፈንዱ ኢንቨስት የሚያደርግበት ሃብት ወይም ንብረት ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው መጠን ወይም ገደቦች፣
    iii. የተፈቀዱ ግብይቶች መግለጫ፣ ወይም
    iv. ፈንዱ መበደር የሚችለው የገንዘብ መጠን ላይ የተጣሉ ገደቦች።

    ለ) በሽያጭ ሰነዶች ውስጥ ከተሰጡት መግለጫዎች የወጡ ወይም የተለወጡ ጉዳዮች፣ ወይም

    ሐ) ለፈንዱ አከናዋኝ የሚከፈለው ክፍያ ወይም ወጭዎች ጣሪያ ላይ የሚኖር ጭማሪ።

4) የለውጦች ጉልህነትን ለመወሰን የፈንዱ የክፍልፋይ ያዦች ክፍልፋዮቹን ካገኙ ወይም በኢንቨስትመንት ፖሊሲ ላይ ድምጽ የመስጠት እድል ካገኙ ጀምሮ ያሉ ሁሉም ለውጦች ድምር ውጤት ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

5) በፈንዱ ላይ ለሚደረጉ ማናቸውም ጉልህ ለውጦች እንዲጸድቁ የክፍልፋይ ያዦችን የተለየ የውሳኔ ሃሳብ የሚፈልጉ በሚሆኑበት ጊዜ እያንዳንዱ ውሳኔ በተናጠል በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጽደቅ ይኖርበታል።

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ቢኖርም ሁለት አይነት ሃላፊነት ባለበት የሽርክና ማኅበር አይነት የተቋቋመ ፈንድ አግባብነት ባላቸው የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት ይተዳደራል።

96. <u>የክፍልፋይ ያዦች ጉባዔ</u>

1) አከናዋኙ ወይም ከእርሱ ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች የጉባዔው ሰብሳቢ መሆን አይችሉም።

2) ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአከናዋኙን ወይም ከእርሱ ጋር ቅርበት ያላቸውን ሰዎች ፍላጎት ጋር የሚገናኝ ካልሆነ በቀር በአከናዋኙ ወይም ከእርሱ ጋር ቅርበት ባላቸው ሰዎች የተያዙ ክፍልጋዮች ድምፅ የመስጠት መብትን ይሰጣሉ።

3) ጠባቂው በእያንዳንዱ የክፍልፋይ ያዦች ጉባዔ ላይ የመገኘት መብት አለው።

4) በእያንዳንዱ ጉባዔ ላይ የነበሩ ሁሉም ሂደቶች እና የተላለፉ ውሳኔዎች በአከናዋኙ በአግባቡ መመዝገብ አለባቸው።

<u>ምዕራፍ ሰባት፣ በቋሚነት መረጃን ይፋ ስለማድረግ</u>

<u>ክፍል 1 ፡ ጠቅላላ ግዴታዎች</u>

97. <u>ተፈጻሚነት</u>

1) ሁሉም ፈንዶች ለኢንቨስትመንት ውሳኔ ወሳኝ የሆ የፈንዱን አፈጻጸም፣ የስጋት እና የፋይናንስ ውጤት መረጃዎችን በትክክል እና በተሟላ ሁኔታ በወቅቱ ይፋ ማድረግ አለባቸው።

2) በአቅርቦት ሰነዱ ወይም በግዥ ቃልኪዳን ስምምነቱ ላይ በልዩ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በቋሚነት መረጃን ይፋ ስለማድረግ የተቀመጡ ግዴታዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት ለህዝብ ሽያጭ በቀረቡ ፈንዶች ላይ ብቻ ነው።

3) በቋሚነት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ትክክለኛ በሆነ መንገድ መገለጽ ያለባቸው ሲሆን በአሳሳች ወይም በሚያታልል መንገድ መቅረብ እንዲሁም ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን ማስቀረት የለባቸውም።

98. <u>መስፈርቶች</u>

1) በዚህ መመሪያ የተሻሻሉ እና ተጨማሪ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የማንኛውም ፈንድ በቋሚነት መረጃን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች በሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብና ግብይት መመሪያ ላይ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በመከተል ሊሆኑ ይገባል፡፡

2) ፈንዱ በቋሚነት ይፋ እንዲያደርጋቸው የሚጠበቁ መረጃዎች በዚህ መመሪያ በተገለጸው አግባብ ወዲያው ይፋ የሚደረጉ እና ወቅታዊ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎችን ያካትታል፡፡

99. <u>ወዲያው ይፋ መደረግ ያለባቸው መረጃዎች</u>

በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ክፍል 5 ንዑስ ክፍል 2 ከተገለጸው በተጨማሪ ወዲያው ይፋ መደረግ ያለባቸው መረጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራል፣

ሀ) በፈንዱ ላይ ጉልህ ተጠያቂነት ወይም ሃላፊነት የሚያመጣ ማንኛውም ጉዳይ እንደተከሰተ፣
ለ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ በህግ ወይም ተቆጣጣሪ አካላት የሚደረጉ ማናቸውም ጉልህ ምርመራዎች ወይም ሕጋዊ እርምጃዎች፣
ሐ) ፈንድ አከናዋኙ ወይም ጠባቂው ወይም ከእነርሱ ጋር ቅርበት ያለው ሰው ከካፒታል ገበያ ጋር በተገናኘ ያጋጠሙት የሕግ ወይም አስተዳደራዊ ሙግቶች፣
መ) ባለስልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጋይድላይን፣ በሰርኩላር ወይም በማስታወቂያ የሚጠይቀው ማንኛውም ሌላ መረጃ፡፡

<u>ክፍል 2፣ ወቅታዊ መረጃን ይፋ ስለማድረግ</u>

100. <u>ወቅታዊ መረጃን ይፋ የማድረግ መስፈርቶች</u>

1) የፈንዱ ዝቅተኛው ተፈላጊ ወቅታዊ መረጃን ይፋ ማድረግ አመታዊ እና የግማሽ አመት ሪፖርቶችን ማካተት አለበት፡፡

2) ፈንዱ በሽያጭ አቅርቦት ሰነዱ ላይ ከተገለጸ ወይም ክፍልፋዮቹ በተመዘገቡበት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ከተጠየቀ ተጨማሪ ወይም በተደጋጋሚ ወቅታዊ መረጃዎችን ይፋ እንዲያደርግ ሊገደድ ይችላል፡፡

3) ፈንዱ የክፍልፋይ ያዦች እና ለባለስልጣኑ፡
   ሀ) የሂሳብ አመቱ በተጠናቀቀ በዘጠና (90) የካላንደር ቀናት ውስጥ አመታዊ ሪፖርቱን፣ እና

ለ) ግማሽ አመቱ በተጠናቀቀ በአርባ አምስት (45) የካላንደር ቀናት ውስጥ የግማሽ አመት ሪፖርቱን፣

አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት።

4) በወቅታዊነት ይፋ የሚደረጉት የፋይናንስ መረጃዎች ተቀባይነት ባገኙና አግባብነት ባላቸው የአለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሰረት መዘጋጀት አለባቸው።

101. **<u>በወቅታዊነት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ይዘት</u>**

1) ሁሉም በወቅታዊነት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ፈንዱ ሀብቶቹን በኢንቨስትመንት ፖሊሲው መሰረት ኢንቨስት እያደረገ እና እያስተዳደረ ስለመሆኑ ግልጽ መግለጫ ማካተት አለባቸው።

2) ሁሉም በወቅታዊነት ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

ሀ) ስለ ወጭው እና ዋጋ የሚገልጽ የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ዝርዝር መረጃ፣

ለ) የተጣራ የሀብት ዋጋው በእያንዳንዱ ክፍልፋይ ስላለው እንቅስቃሴ መግለጫ ፣

ሐ) የኢንቨስትመንት ፖሊሲው እና በፖሊሲው ላይ የተደረጉ ለውጦች መግለጫ፣

መ) ስለፈንዱ ፖርትፎሊዮ ስብጥር ማብራሪያ፣

ሠ) የተከፈሉ ወጪዎችን፣ ትርፍና ኪሳራቸውን ጨምሮ ፈንዱ ስለገዛቸው እና ስላስተላለፋቸው የፈንዱ ፖርትፎሊዮ አካል ስለሆኑ ሀብቶች ዝርዝር፣

ረ) የኢንቨስትመንት ክምችት ስጋት ፣ የውጭ ምንዛሬ ስጋት፣ የገንዘብ እከል ንብረት እጦት ስጋትን ጨምሮ ፈንዱ ሊያጋጥሙት ስለሚችሉ ማንኛውም ጉልህ ስጋቶች ወቅታዊ መረጃ፣

ሰ) ለአከናዋኙ ፣ ለጠባቂው እና ለሌሎች ባለሞያ አካላት የሚከፈል ወይም የተከፈለ ክፍያ፣

ሸ) የስራ ማስኬጃ እና የግብይት ወጪዎችን ጨምሮ ፈንዱ ወይም ፈንዱ ኢንቨስት ያደረገባቸው ኩባንያዎች የከፈሏቸው ክፍያዎች፣

ቀ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ በህግ ወይም ተቆጣጣሪ አካላት የሚደረጉ ማናቸውም ጉልህ ምርመራዎች ወይም ህጋዊ እርምጃዎች፣

ተ) ለአከናዋኙ ወይም ጠባቂው ወይም ከእነርሱ ጋር ቅርበት ያለው ሰው ወይም የቦርድ አባል ከካፒታል ገበያ ጋር በተገናኘ የገቡባቸውን የህግ ወይም አስተዳደራዊ ሙግቶች፣

ቸ) ሪፖርቱ በሚሸፍነው ጊዜ ውስጥ የተከናወኑ ማንኛውም የተዛማጅ ወገን ግብይቶች ፣

ኀ) ባለስልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጋይድላይን፣ በሰርኩላር ወይም በማስታወቂያ የሚጠይቀው ማንኛውም ሌላ መረጃ።

102. የተዛማጅ ወገን ግብይቶችን ይፋ ስለማድረግ

1) የንግድ ሕጉ፣ የዓለም አቀፍ የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች እና ማንኛውም ለፈንዱ አግባብነት ያላቸው ደረጃዎች የሚያስቀምጧቸው መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የተዛማጅ ወገን ግብይቶችን በተመለከተ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች፣

    ሀ) የተዛማጅ ወገኑን ማንነት እና የግንኙነት አይነት መግለጽ፣

    ለ) ስለግብይቱ ዝርዝር መረጃ መስጠት፣

    ሐ) ግብይቱ በፈንዱ የፋይናንስ ሁኔታ፣ በአፈጻጸሙ ወይም በስጋት ተጋላጭነቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት ማብራርያ መስጠት፣

    አለባቸው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተገለጹት የግብይት መረጃዎች የሚከተሉትን መግለጽ አለባቸው።

    ሀ) የግብይቱን አይነት፣

    ለ) ደንብ እና ሁኔታዎችን ፣

    ሐ) የግብይቱን ዋጋ፣ የግመታውን ዘዴ፣ ገለልተኛ ግመታ ስለመደረጉ መግለጽን ጨምሮ ዝርዝር የፋይናንስ መረጃዎችን።

3) የተዛማጅ ወገን ግብይቶችን ይፋ የሚያደርግ መረጃ፡-

    ሀ) ግብይቱ የተፈጸመው በፈንዱ በጸደቀው የጥቅም ግጭት ፖሊሲ መሰረት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ መግለጫ ማካተት፣ እና

    ለ) ግብይቱ እንዲፈጸም የክፍልፋይ ያዦች ይሁንታ ስለመስጠት አለመስጠታቸው መግለጽ፣

    አለበት።

103. የግማሽ ዓመት ሪፖርት

1) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 98 ላይ የተገለፀው ወቅታዊ መረጃን ይፋ ከማድረግ በተጨማሪ የፈንዱ የግማሽ አመት ሪፖርት፡-

    ሀ) የአከናዋኙን ሪፖርት፣

    ለ) የአፈጻጸም ምዘና ሪፖርትን፣ እና

    ሐ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 141 መሰረት የግማሽ አመት የፋይናንስ መግለጫን፣

    ማካተት አለበት።

2) እንደአስፈላጊዝነታቸው የሌሎች ባለሞያ አካላት ሪፖርቶች በግማሽ አመት ሪፖርት ውስጥ መካተት አለባቸው።

104. <u>ዓመታዊ ሪፖርት</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 111 ላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የፈንዱ አመታዊ ሪፖርት የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

   ሀ) የአከናዋኙን ሪፖርት፣

   ለ) የአፈጻጸም ምዘና ሪፖርት፣

   ሐ) የጠባቂውን ሪፖርት፣

   መ) የፈንዱን ጠቅላላ ዋጋ ግምታ ሪፖርት፣

   ሐ) ኦዲት የተደረገ አመታዊ የፋይናንስ መግለጫ፣

   መ) በባለስልጣኑ በጸደቀ የውጭ ኦዲተር የተዘጋጀ የኦዲት አስተያየትን ያካተተ የኦዲት ሪፖርት፣

   ሠ) ባለስልጣኑ የሚጠይቀው ሌላ ማንኛውም መረጃ።

2) እንደአግባብነቱ የሌሎች ባለሙያ አካላት ሪፖርቶች በአመታዊ ሪፖርት ውስጥ መካተት አለባቸው።

3) አመታዊ ሪፖርት በሰነደ ሙአለ ንዋዮችን ለሽያጭ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 143 ስር የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።

<u>ክፍል 3 ፣ ከባለሙያ ወገኖች ስለሚቀርቡ ሪፖርቶች</u>

105. <u>የአከናዋኙ ሪፖርት</u>

1) የሚከተሉት በአከናዋኙ ሪፖርት ውስጥ ሊካተቱ ይገባል፣

   ሀ) በፈንዱ በባለስልጣኑ የተመዘገበበትን የፈንድ አይነት የሚያመላክት መግለጫ፣

   ለ) የሚከተሉትን አካላት ስምና አድራሻ፣

      i. የአከናዋኙን፣
      ii. የጠባቂውን፣
      iii. የኢንቨስትመንት ወይም ሽሪዓ አማካሪ፣
      iv. የውጭ ኦዲተሩን፣ እና
      v. ለፈንዱ አይነት አግባብነት ያላቸው ማናቸውንም ባለሞያ አካላት፣

ሐ) ኢንቨስትመቶችን፣ የሃብት ግዥዎችን እና ወጭያቸውን ጨምሮ ሪፖርቱ በሚሸፍነው ጊዜ ውስጥ የነበሩ የፈንዱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ማጠቃለያ ፣

መ) ከፈንድ አከናዋኙ ጋር ቅርበት ካላቸው ሰዎች ጋር የተደረጉ ግብይቶችን ማጠቃለያ፣

ሠ) ከፈንዱ የተከፈሉ ማናቸውም የአገልግሎት ክፍያዎችና ወጪዎች እንዲሁም ለፈንድ አከናዋኙ የሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያዎች፣

ረ) የአቅርቦት ሰነዱን ወይም የማቋቋሚያ ሰነዱን በመጣስ የተፈጸመ ማንኛውም አይነት ድርጊት፣ እና

ሰ) የክፍልፋይ ያዦች በሪፖርቱ ጊዜ ውስጥ ስለነበሩ የፈንዱ እንቅስቃሴዎችና በሪፖረቱ ጊዜ ማብቂያ ላይ በተከናወኑ ተግባራት ላይ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ እንዲሰጡ የሚያስችላቸው ማንኛውም አይነት ጉልህ መረጃ።

2) የፈንድ አከናዋኙ ሪፖርት፣

ሀ) የፈንዱን ኢንቨስትመንት ፖሊሲ እና በፖሊሲው ላይ የተደረጉ ለውጦችን መግለጽ፣ እና

ለ) በፖሊሲው ላይ የተደረጉትን ለውጦች የክፍልፋይ ባለቤቶች ስለማጽደቅ አለማጽደቃቸው መግለጽ፣

አለበት።

106. <u>የጠባቂው ሪፖርት</u>

1) አመታዊ ሪፖርት በማቋቋሚያ ሰነዶች እና በዚህ መመሪያ የሚጠየቁ መረጃዎችን ያካተተ የጠባቂውን ሪፖርት ማካተት አለበት።

2) ከጠባቂው የሚቀርበው ሪፖርት የሚከተሉትን የሚያሳይ መግለጫ ማካተት አለበት፡-

ሀ) የአከናዋኙ ፈንዱን በኢንቨስትመንት ፖሊሲው፣ በማቋቋሚያ ሰነዶች እና በዚህ መመሪያ በተቀመጡት ገደቦች መሰረት ያስተዳደረ ስለመሆኑ፣ እና

ለ) ካልሆነም በዚህ ረገድ ጠባቂው የወሰዳቸውን እርምጃዎች።

107. <u>ከሌሎች ባለሞያ አካላት ስለሚቀርቡ ሪፖርቶች</u>

1) ለሸሪዓ መርህ ተገዢ የኢንቨስትመንት እንስቃሴዎችን የሚያደርግ ፈንድ አመታዊ ሪፖርቱ እንቅስቃሴዎቹ ተፈጻሚነት ያለው የሸሪዓ መርህን የተከተሉ ስለመሆናቸው መግለጫ እና የሸሪዓ አማካሪውን ማረጋገጫ ማካተት አለበት።

2) እንደ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ እና መልካም አስተዳደር የመሳሰሉ ልዩ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ የሚሰሩ ፈንዶች አመታዊ ሪፖርት እንደዚህ ያሉ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈጻሚ

የሚሆኑ መስፈርቶችን አክብሮ የሰራ ስለመሆኑ መግለጫና አግባብነት ያለውን ባለሙያ አካል ማረጋገጫ ማካተት አለበት።

ክፍል 4፣ የፈንዱ አፈጻጸም ሪፖርት

108. ከአፈጻጸም ጋር የተገናኙ መረጃዎች

1) አከናዋኙ ምንም ዓይነት ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ በአፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶቹ ውስጥ ማካተት የለበትም።

2) የፈንዱ ትክክለኛ አፈጻጸም ከታሪካዊ፣ ከጽንሰ ሃሳብ ወይም ከወደፊት አፈጻጸም ጋር መያያዝ የለበትም።

3) የፈንድ አከናዋኙ ማመሳከሪያን ወይም ኢንዴክስን ለስጋት እና ገቢ ትንታኔው መጠቀም ከፈለገ፣ ጥቅም ላይ የሚውለው ማመሳከሪያ ወይም ኢንዴክስ ለፈንዱ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ አግባብነት ያለው መሆን ያለበት ሲሆን እና አከናዋኙም የማመሳከሪያውን እና የኢንዴክሱን ስም፣ ቁልፍ ባህርያቱን እና ድግግሞሽ በአፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቱ ማካተት አለበት።

4) የአከናዋኙ የተጣራ የሀብት ዋጋን ሲያቀርብ የፈንዱን የተጣራ የሀብት ዋጋ በአንድ የድርሻ ክፍልፋይ ስንት እንደሆነ በብር መግለጽ አለበት።

5) በአፈጻጸም ምዘና ሪፖርት ውስጥ የሚቀርቡ ሁሉም መረጃዎች በተመሳሳይ የገንዘብ ምንዛሪ አይነት መቅረብ አለባቸው።

109. የአፈጻጸም ምዘና ሪፖርት

1) የአፈጻጸም ምዘና ሪፖርት ኢንቨስተሩ የፈንዱን ትክክለኛ አፈጻጸምና የመፈጸም አቅሙን በአግባቡ እንዲረዳ የሚያስችሉትን ሁሉንም ወሳኝ መረጃዎች ማካተት አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጹት ወሳኝ መረጃዎች ቢያንስ ለአንድ አመት እና የፈንዱን የአፈጻጸም ታሪክ ለመገንዘብ አስፈላጊ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ በአፈጻጸም ምዘና ሪፖርት ውስጥ መካተት አለባቸው።

3) የአፈጻጸም ምዘና ሪፖርቱ ፈንዱ የተመዘገበበትን ቀን እና የፈንዱን የአፈፃፀም መረጃዎች በእያንዳንዱ ጊዜ በሚከተለው መልኩ ማስቀመጥ አለበት።

   ሀ) በፈንዱ በአስተዳደር ስር ያለ ጠቅላላ ሀብት፣

   ለ) የፈንዱ ትርፍ በቀረበባቸው በእያንዳንዱ ጊዜያት የነበረ ድምር የፈንዱ ትርፍ፣ እና

ሐ) የጠቅላላ ወጪዎች ንፅፅር፣

4) በፈንዱ በአስተዳደር ስር ያለ ጠቅላላ ሀብት፣ ጠቅላላ ገቢ የጠቅላላ ወጪዎች ንፅፅር በሚቀርቡበት ወቅት ከሪፖርት ጊዜው አስቀድሞ ያለው የሪፖርት ጊዜ ተነጻጻሪ አሀዞችም ለማነጻጸሪያነት መቅረብ አለባቸው።

5) የአፈጻጸም ምዘና ሪፖርት ለጉልህ ስህተቶች ማረሚያ የሚሰጥ መረጃን ሊያካትት ይችላል።

6) ማንኛውም ስህተት ጉልህ የሚባለው በፈንዱ አስተዳደር ስር ካለው የተጣራ የሀብት ዋጋ አስር በመቶ (10%) ወይም ከዚያ በላይ የሚያህል ተጽዕኖ ሲኖረው ነው።

7) መግለጫው የታወቁ ስህተቶችን፣ ስህተቶቹ ያስከተሏቸውን ተፅዕኖዎች፣ ስህተቱ ከመስተካከሉ በፊት እና በኋላ ያሉ የዋጋ ልዩነቶች እና ስህተቱ ዳግም እንዳይከሰት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ማካተት አለበት።

110. <u>አፈጻጸም ስለሚሰላባቸው ዘዴዎች</u>

1) በፈንዱ አስተዳደር ስር ያለ ጠቅላላ ሀብት የፈንዱ ሀብቶች እና ንብረቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ጠቅላላ ድምር መሆን አለበት።

2) የፈንዱ ጠቅላላ ገቢ የሚከተሉትን ጨምሮ ከሁሉም ውጪዎች ተጣርቶ መቅረብ አለበት፣
   ሀ) ለፈንዱ ሀብቶች ሽያጭ እና ግዢ የወጣ ወጪ፣ የኢንቨስትመንት ድለላና የግብር ወጪዎችን የመሳሰሉ ሁሉም የግብይት ወጪዎች፣
   ለ) ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የሚከፈል ክፍያ፣
   ሐ) ማንኛውም አፈጻጸምን መሰረት ያደረገ ክፍያ፣
   መ) እንደ ኦዲት፣ የሕግ ማማከር፣ የጠባቂ እና የባለአክሲዮን ስብሰባዎችን የመሳሰሉ አስተዳደራዊ ወጪዎች።

3) የፈንዱ ጠቅላላ የወጪ ንፅፅር የፈንዱን ጠቅላላ ወጪ በፈንዱ አስተዳደር ስር ባለው የፈንዱ ጠቅላላ ሀብት በማካፈል መሰላት አለበት።

4) ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የተገኙ ገቢዎች አመታዊ ገቢን በሚያንጸባርቅ መልኩ በዓመቱ ውስጥ የተገኙ ተደርገው መቅረብ የለባቸውም።

5) የፈንድ አከናዋኝ ገቢን ሲያሰላ ለአፈጻጸም ምዘና ጥቅም ላይ የዋለውን የስሌት ዘዴ ወጥ በሆነ ሁኔታ መተግበር አለበት።

ክፍል 5 ፣ የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ዋጋ ግመታ

111. የዋጋ ግመታ ሪፖርት

1) የዋጋ ግመታ መሰራት ያለበት ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙአለ ንዋይ ገማች ድርጅት፣ ወይም የባለስልጣኑን ይሁንታ ባገኘ ሌላ ፈቃድ ባለው የግመታ አገልግሎት ሰጪ ነው።

2) የዋጋ ግመታ ሪፖርት የሚከተሉትን በማሟላት አመታዊ ሪፖርት ውስጥ መካተተ አለበት

   ሀ) የግመታ ሪፖርቱን ያዘጋጀው አካል ፊርማ፣

   ለ) የተዘጋጀበት ቀን፣

   ሐ) የተሟላና ትርጉም ያለው የፈንዱን ፖርትፎሊዮ ትንተና ማካተት አለበት፤ እና

   መ) የሪል እስቴትን፣ የሰነደ ሙዓለንዋዮች እና ሌሎች የገንዘብ ሰነዶች ጨምሮ ለእያንዳንዱ የፈንዱ ፖርትፎሊዮ ውስጥ ያለ ሀብት ግልጽ ዋጋ።

3) የሪል እስቴት ዋጋ ግመታ በሚያስፈልግበት ወቅት፣ በዚህ መመሪያ ምዕራፍ 4 ክፍል 3 ላይ የተመለከቱት ተጨማሪ መስፈርት ተፈጻሚ ይሆናል።
4) ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ የፈንዱን የዋጋ ግመታ ሂደት ከአመታዊ ሪፖርቱ ዝግጅት ጋር አብሮ መገምገም አለበት።

112. የዋጋ ግመታ መረሆዎች፣ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች

1) የዋጋ ግመታው መሰራት ያለበት በቅን ልቦና ትክክለኛና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተገቢውን የግመታ ፖሊሲዎችና አሰራሮችን በመከተል ነው።

2) የዋጋ ግመታ በፍትሃዊ የምዘና መርሆዎች ላይ ተመስርቶ መሰራትና እውነተኛ የፈንዱን ሀብት ዋጋ የሚያንጸባርቅ መሆን ይኖርበታል።
3) ተፈጻሚ የሚሆኑ የዋጋ ግመታ ደረጃዎች እንደ አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ዝግጅት ስርዓት፣ የአለም አቀፍ የዋጋ ምዘና ደረጃ፣ አለም አቀፍ የግል ባለሀብት ፈንድ የዋጋ ግምገማ አሰራርን ጨምሮ በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ የግምገማ ደረጃዎች መሆን አለባቸው።

4) የግመታ ፖሊሲዎችና የአሰራር ስርዓቶች በአከናዋኙ እና በቦርዱ መጽደቅ ይኖርባቸዋል።

5) የፈንዱ ሀብቶች በወጥነት በጸደቁት ፖሊሲዎችና የአሰራር ስርዓቶች መሰረት መገመት ይኖርባቸዋል።

6) የገንዘብ ሰነዶችን የሚያካትቱ ሀብቶች ላይ የሚከተሉት ተፈጻሚ ናቸው፣

ሀ) ለግመታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዋጋዎች በሰነደ ሙአለ ንዋይ ገበያው በግብይት ቀን መዝጊያ በነበረው ዋጋ ውይም አግባብነት ባላቸው ህትመቶች በሚረጋገጥ መልኩ መሆን፣ እና

ለ) በሰነደ ሙአለ ንዋይ ገበያ ላይ ላልተመዘገቡ ሰነዶች ወይም በጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ወቅታዊ የግብይት መረጃ የሌላቸው ሲሆኑ ግምቱ የሚሰራው የአከናዋኙ በገለልተኛ ባለሞያ አካል አማካሪነት በሚሰጠው ጥሩ የግምት ዋጋ ነው።

7) ለግመታው መሰረት የሆኑ ሙሉ መረጃዎች በፈንዱ መዛግብት እና ሪከርዶች ወስጥ በአግባቡ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው።

ምዕራፍ ስምንት፡ ስለ መዋሃድ፣ ለቁጥጥር የሚያበቃ የክፍልፋዮች ግዢ እና ስለመፍረስ

113. ስለመዋሃድ፣ ለቁጥጥር የሚያበቃ የክፍልፋዮች ግዢ እና ሌሎች አይነት ጥምረቶች

1) አግባብነት ያላቸው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ውህደቶች፣ ለቁጥጥር የሚያበቁ ግዢዎች እና ሌሎች አይነት ጥምረቶች ሊከናወኑ የሚችሉት ለዚሁ አላማ ፕሮፖዛል ቀርቦ ባለስልጣኑ ሲያጽድቀው ብቻ ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው ፕሮፖዛል በፈንዱ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ካልጸደቀ በስተቀር ሊተገበር አይችልም።

3) ውህደቶች፣ ለቁጥጥር የሚያበቁ ግዢዎች እና ሌሎች አይነት ጥምረቶች የሚካሄዱት የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ያልሆነ ሌላ አይነት አካል ለማቋቋም ከሆነ ከመፈረስ ጋር የተያያዙ የህግ ድንጋጌዎችን በመከተል ፈንዶቹን ማፍረስ እና የፈንዶቹን የምዝገባ ምስክር ወረቀቶች መመለስ ይኖርባቸዋል።

4) ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች እንዲዋሃዱ ወይም እንዲጣመሩ ሃሳብ የቀረበ እንደሆነ ፕሮፖዛሉ መዋሃዱ ወይም መቀላቀሉ በሚመለከታቸው ሁሉም ፈንዶች የድርሻ ክፍልፋይ ባለቤቶች መጽደቅ ይኖርበታል።

114. <u>የፈንዱ መፍረስ</u>

1) አግባብነት ያላቸው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አንድ ፈንድ ሊፈርስ የሚችለው ለባለስልጣኑ ለዚሁ አላማ ቀርቦ በሚጸድቅ ፕሮፖዛል መሰረት ነው።

2) አንድ ፈንድ በሚፈርስበት ግዜ የፈንዱ መዝገቦች እና ሪከርዶች ተገቢ ለሆነ ጊዜ በአግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል።

3) አከናዋኙ የመፍረስ ሂደቱ ከመጠናቀቁ በፊት ፈንዱ ያሉበት ሁሉም እዳዎች ተከፍለው እንዲጠናቀቁ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት።
4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው ግዴታ፣

   ሀ) የመፍረስ ሂደቱ ከመጠናቀቁ በፊት አከናዋኙ አስቀድሞ የሚያውቃቸው ወይም እንዲያውቃቸው የተደረጉ፣ ወይም

   ለ) አከናዋኙ የመፍርስ ሂደቱ ከመጠናቅቁ በፊት የፈንዱን እዳዎች ለማወቅ ተገቢውን ጥረት ቢያደርግ ሊያውቃቸው የሚችላቸውን ሁሉንም እዳዎች ያጠቃልላል።
5) አከናዋኙ ፈንዱ እዳዎቹን መክፈል የማይችል መሆኑን ካመነበት ይህንኑ ለቦርዱ እና ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

6) ቦርዱ የፈንዱ የመፍረስ ሂደቱ በአግባቡ እንዲከናወን ለአከናዋኙ ተገቢውን ትብብር ማድረግ ይኖርበታል።

115. <u>የሂሳብ አያያዝ እና ሪፖርቶች</u>

1) መረጃን በቋሚነት ይፋ የማድረግ ግዴታዎች ፈንዶች በመፍረስ ሂደት ላይ እያሉም የሚቀጥሉ ይሆናል።

2) የፈንዱ የመፍርስ ሂደት ሲጠናቀቅ በዛ ጊዜ ያለው የሂሳብ ጊዜ እንደ መጨረሻ አመታዊ የሂሳብ ጊዜ ተደርጎ ይቆጠራል።

3) ከመጨረሻው የሂሳብ ጊዜ ጋር የተያያዙ የፈንዱ፣ የፈንድ አከናዋኙ እና የጠባቂው ወቅታዊ ሪፖርቶች ታትመው ለባለስልጣኑ እና በፈንዱ ውስጥ ኢንቨስተር ለነበረ ሁሉም ሰው የመጨረሻው የሂሳብ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ወዲያወኑ ሊላኩ ይገባል።

4) የፈንዱ የውጭ ኦዲተር የኦዲተሩን አስተያየት እና የመጨረሻው ሂሳብ አግባብነት ባላቸው የሂሳብ አያያዝ መርሆች መሰረት ስለመዘጋጀቱ የሚገልጽ የመጨረሻ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት።

116. **<u>የመጨረሻ ሪፖርት</u>**

1) አከናዋኙ የመፍረስ ሂደቱ እንዴት እንደተከናወነ እና የፈንዱ ንብረቶች በምን አግባብ እንደተሸጡ የሚያሳይ የመጨርሻ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት።
2) የመጨረሻው ሪፖርት በቦርድ የጸደቀ እና በአከናዋኙ የተፈረመ መሆን አለበት።

<u>ምዕራፍ ዘጠኝ፣ ተገዥነት፣ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ህግ ማስፈጸም</u>

<u>ክፍል 1፣ ጠቅላላ</u>

117. **<u>የህግ ተገዥነት ሪፖርት</u>**

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ የፈንድ ምዝገባ መስፈርቶችን መከብሩን ለማረጋገጥ ክትትል ያደርጋል።
2) ፈንዱ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ባለስልጣኑ በሚወስነው መሰረት ከዛ በላይ በሆነ ጊዜ የህግ ተገዥነት ሪፖርት ለኢንቨስተሮች ከሚቀርብ አመታዊ ሪፖርት ጋር ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት።
3) ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከተው የህግ ተገዥነት ሪፖርት የሚከተሉትን ያጠቃልላል ፦

   ሀ) በዚህ አንቀፅ ውስጥ የተመለከቱትን ጉዳዮች የሚመለከት ከህግ ማስከበር መኮንን የተገዥነት ደብዳቤ፣ እና

   ለ) የቦርዱ የኦዲት፣ ስጋት እና ህግ ማስከበር ኮሚቴ ስለ የህግ ተገዢነት ሪፖርቱ ምሉእነት እና ትክክለኛነት ማረጋገጫ።

4) ለንዑስ አንቀፅ 3 አላማ ሲባል በተሰየመው የህግ ማስከበር መኮንን የሚዘጋጀው የተገዥነት ደብዳቤው የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

   ሀ) የክፍልፋዮች አቅርቦት በቀጣይነት በመካሄድ ላይ ያለ ወይም ማንኛውም የክፍልፋዮች ሽያጭ የተካሄደው በሂሳብ ዘመን ጊዜ ውስጥ መሆኑን፣

   ለ) የፈንዱ ካፒታል ማሳደጊያ ግቦች እና መስፈርቶች መሟላታቸው ወይም አለመሟላት እና የዚሁ ውጤቱ ምክንያት፣

   ሐ) በኢንቨስትመንት ፖሊሲ ውስጥ በተቀመጠው መሰረት የፈንዱ የታቀዱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ሁኔታ፣

   መ) የገቢ ማሰባሰብ ሁኔታን ጨምሮ እንደ አስፈላጊነቱ ኢንቨስተሮችን መልሶ ስለመክፈል ወይም ካፒታልን ወደ ኢንቨስትመንቶች ስለማዋል በአሁኑ ጊዜ በመካሄድ ላይ መሆኑን፣

ሠ) ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት ፈንድን በሚመለከት ለፈንዱ የድርሻ ክፍልፋይ ባለቢቶች የተከፋፈለውን የኪራይ ገቢ መጠንን፣ እና

ረ) ቁጥጥር ለሚደረግበት ፈንድ አስፈላጊ የሆነ ሌላ ማንኛውም ተጨማሪ መረጃ።

5) የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አንቀጽ 17(4) እንደተጠበቀ ሆኖ የፈንዱ አከናዋኝ የህግ ማስከበር መኮንኑ በዚህ መመሪያ፣ ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች እና በቅን ልቦና ተግባራቱን በማከናወኑ የተነሳ ማንኛውንም አይነት እርምጃ ሊወስድበት አይገባም።

118. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

1) ባለስልጣኑ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን መከታተል ያለበት ሲሆን ድንጋጌዎቹ ሲጣሱ ወይም ሳይከበሩ ሲቀሩ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ውስጥ አንዱን ወይም በማጣመር እርምጃ የመውሰድ ስልጣን አለው:-

ሀ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

ለ) የገንዘብ ቅጣት መጣል፣

ሐ) የፈንዱን ፈቃድ በጊዜያዊነት ማገድ ወይም መሰረዝ፣

መ) ፈንድ ለማቋቋም እና ለመስራት የሚደረግ እንቅስቃሴን በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ማገድ፣

ሠ) የፈንድ ስራን ማገድ ወይም መከልከል፣

ረ) መመሪያውን የሚጥሱ ተግባራት እንዲቆሙ ማዘዝ፣

ሰ) የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማዘዝ፣

ሸ) የፈንዱን አከናዋኝ፣ ጠባቂ ወይም ማንኛውም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ፣ የፈንዱን የቦርድ አባል ወይም አባላት፣ አደራጆች ወይም መመሪያውን የጣሰ ወይም እንዲጣስ ያደረገን ማንኛውም ሰው በጥቁር መዝገብ እንዲሰፍር ማድረግ ወይም፣

ቀ) በባለሥልጣኑ በየጊዜው የሚደነገጉ ሌሎች ማንኛውም እርምጃዎች።

2) በአዋጁ፣ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ እና ሰነደ ሙአለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ላይ የተደነገጉ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

<u>ክፍል 2፣ ቅጣቶች፣ የገንዘብ መቀጮዎች እና ሌሎች ሕግ የማስከበር ተግባራት</u>

119. <u>ያልተፈቀደ ህትመት</u>

1) ከፈንዱ ወይም ከፈንዱ የድርሻ ክፍልፋዮች ጋር የተያያዙ ያልተፈቀዱ ህትመቶች የተከለከሉ ናቸው።

2) በዚህ ረገድ ያልተፈቀዱ ህትመቶች የሚባሉት በነዚህ ብቻ ሳይገደቡ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣

ሀ) ከባለሥልጣኑ ይሁንታ ሳያገኙ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማሳተም፣

ለ) ከባለስልጣኑ ይሁንታ ሳያገኙ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ማሳተም፣

ሐ) ከባለሥልጣኑ ይሁንታ ሳያገኙ ማንኛውም አይነት ማስታወቂያዎችን፣ ፖስተሮችን፣ የማህበራዊ ሚዲያ ፅሁፎችን ወይም ማንኛውንም ሰነድ ጨምሮ ፈንዱን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች ማሳተም፣

መ) ከባለሥልጣኑ ይሁንታ ሳያገኙ ወሳኝ የኢንቨስተር መረጃ ሰነዶች ማሳተም፣

ሠ) ከባለሥልጣኑ ይሁንታ ሳያገኙ ቀዳሚ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ረቂቅን ማከፋፈል ወይም የአደባባይ ሽያጭ ምዝገባ ማከናወን።

3) ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 154 (3) (ሀ) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ እንደ ተፈጸመው ጥሰት የተፈጸመበትን ሁኔታ፣ ክብደት እና ፈጻሚ በመመልከት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተናጥል ወይም በማጣመር ሊወስድ ይችላል።

ሀ) የገንዘብ ቅጣት፡-

i. ጥሰቱ የተፈጸመው በአደራጅ ከሆነ በህትመቱ ከተሰበሰበው ወይም ሊሰበሰብ ከታሰበው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ላይ ከ10% እስከ 25%፣

ii. ጥሰቱ የተፈጸመው በአከናዋኝ ከሆነ በህትመቱ ከተሰበሰበው ወይም ሊሰበሰብ ከታሰበው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ላይ ከ10% እስከ 25%፣

iii. ጥሰቱ የተፈጸመው በፈንዱ ከሆነ በህትመቱ ከተሰበሰበው ወይም ሊሰበሰብ ከታሰበው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ላይ ከ0.1% እስከ 1%፣

ለ) ሌሎች ቅጣቶች በነዚህ ብቻ ሳይገደቡ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

i. ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ፣

ii. ባለስልጣኑ በሚያዘው መሰረት ፈንዱ ወይም የፈንዱ አከናዋኝ ያልተፈቀደውን ህትመት እንዲሰርዝ ወይም የሚሽር ህትመት እንዲያወጣ ማዘዝ፣

iii. ሽያጩን ወይም የሽያጭ አቅርቦቱን መሰረዝ።

120. <u>ያልተፈቀዱ ተግባራት</u>

1) ከፈንድ ጋር በተያያዘ ያልተፈቀዱ ተግባራት የተከለከሉ ናቸው።

2) የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ረገድ ያልተፈቀዱ ተግባራት በነዚህ ብቻ ሳይገደቡ የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 91(1) ላይ የተደነገጉ ክልከላዎችን መተላለፍ፣

ለ) የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መተላለፍ፣

ሐ) ከፈንዱ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ተቃራኒ የሆኑ ስራዎችን መስራት፣

መ) የባለስልጣኑን ይሁንታ ያገኙ የፈንዱን ፖሊሲዎች እና አሰራሮች የሚቃረኑ ስራዎችን ማከናወን፣

ሠ) ፈንዱ ሳይመዘገብ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ተግባራትን ማከናወን፣

ረ) በማናቸውም አሳሳች የጋራ ኢንቨስትመንት መዋቅሮች መሳተፍ።

3) ባለሥልጣኑ እንደ ጥሰቱ አይነት፣ ክብደት እና እንደፈጸሚው ሁኔታ ከሚከተሉት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ውስጥ ተገቢ የመሰለውን በተናጥል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፣

ሀ) የገንዘብ ቅጣት፡-

i. ጥሰቱን የተፈጸመው የአከናዋኙ ከሆነ ከብር አንድ መቶ ሺ (100,000) እስከ ብር ሁለት ሚሊዮን (2,000,000)፣

ii. ጥሰቱ የተፈጸመው በጠባቂው ከሆነ ከብር አንድ መቶ ሺ (100,000) እስከ ብር ሁለት ሚሊዮን (2,000,000)፣

iii. ጥሰቱ የተፈጸመው በፈንዱ ከሆነ ከብር አንድ መቶ ሺ (100,000) እስከ ብር ሁለት ሚሊዮን (2,000,000)።

ለ) ሌሎች ቅጣቶች በእነዚህ ብቻ ሳይገደቡ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

i. ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ፣

ii. የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪን ፈቃድ መሰረዝ ወይም ማገድ፣

iii. የፈንዱን የምዝገባ የምስክር ወረቀት መሰረዝ ወይም ማገድ፣

iv. የፈንዱን የቦርድ አባል ወይም አባላት ከአባልነታቸው እንዲታገዱ ወይም እንዲነሱ ማዘዝ።

121. <u>ለህዝብ ሽያጭ የሚቀርቡ የፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮች ጋር የተያያዙ ሰነዶችን አዘግይቶ ማቅረብ</u>

1) ለሕዝብ ሽያጭ ከሚቀርቡ የፈንድ የድርሻ ክፍልፋዮች ጋር በተያያዘ ለባለስልጣኑ መቅረብ ያለባቸው አባሪ የደንበኛ ሳቢ መግለጫዎች እና የድልድል ሪፖርቶችን ጨምሮ መቅረብ ያለባቸው ማሳወቂያዎች እና ሪፖርቶች በሰነደ ሙአለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ድንጋጌዎች ላይ በተቀመጡ የጊዜ ገደቦች ውስጥ መቅረብ አለባቸው።

2) ባለሥልጣኑ እንደ ነገሩ ሁኔታ እና ክብደት እና ሪፖርቱን በጊዜው ያላቀረበው ሰው ማን እንደሆነ ከግምት ውስጥ በማስገባት በአከናዋኙ ላይ በተናጠል ወይም ከሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች ጋር በጣምራ ከብር አንድ ሚሊዮን (1,000,000) እስከ ብር ሶሰት ሚሊዮን (3,000,000) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ሊጥል ይችላል።

122. **<u>በቀጥይነት ይፋ መደረግ ያለባቸውን መረጃዎች አዘግይቶ ይፋ ማድረግ</u>**

1) ከፈንዱ በቀጣይነት መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች ጋር በተያያዘ ይፋ መደረግ ያለባቸው መረጃዎች በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ስር በተቀመጡ የጊዜ ገደቦች ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡

2) ባለስልጣኑ እንደ ጉዳዩ ሁኔታና ክብደት በተናጥል ወይም ከሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች ጋር በማጣመር ለተፈጸመው ጥሰት ሃላፊ የሆኑ አካላት ላይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፣

   ሀ) ከብር አስር ሺ (10,000) እስከ ብር ሃያ ሺ (20,000) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና መረጃው ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ተጨማሪ አንድ ሺ ብር (1,000) ብር የገንዘብ መቀጮ፣

   ለ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ፡፡

123. **<u>የአከናዋኝ ግዴታዎችን አለመዎጣት</u>**

1) የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለስልጣኑ ሃላፊነቱን እና በዚህ መመሪያ የተጣሉበትን ግዴታዎች ባልተወጣ የአከናዋኝ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡

2) እንደ ጉዳዩ ሁኔታና ክብደት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ባለሥልጣኑ በተናጥል ወይም ከሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች ጋር በማጣመር የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

   ሀ) ከብር አስር ሺ (10,000) እስከ ብር አንድ መቶ ሺ (100,000) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እና ጥፋቱ ለቀጠለበት እያንዳንዱ ቀን ከብር አንድ ሺ (1,000) እስከ ብር አስር ሺ (10,000) የሚደርስ ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት፣

   ለ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ፡፡

124. **<u>ሌሎች ጥሰቶች</u>**

በዚህ ምእራፍ ካልተደነገገ በስተቀር የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መጣስ የገንዘብ ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ ከብር አስር ሺ (10,000) በማያንስ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

<u>ምዕራፍ አስር፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

125. **<u>አለመግባባቶችን ስለመፍታት</u>**

የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በፈንድ ውስጥ በሚሳተፉ ወገኖች መካከል ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የባለስልጣኑ መመሪያዎች ጋር በተያያዘ የሚነሱ የፍትሃ ብሄር ጉዳይ አለመግባባቶች በአዋጁ አንቀጽ 111 መሰረት በሽምግልና ወይም በግልግል ዳኝነት ይፈታሉ፡፡

126. <u>ተፈጻሚ አለማድረግ</u>

1) የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ ከተደነገገው የተለየ ጊዜያዊ አደረጃጀት ሊያዘጋጅ ይችላል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚኖረው ጊዜያዊ አደረጃጀት፡-
    ሀ) የባለሥልጣኑን ዓላማዎች ለማስፈጸም ሲባል፣ እና
    ለ) በዚህ መመሪያ ከተደነገገው የበለጠ ከባድ ግዴታዎችን የሚጥሉ መሆን የለባቸውም።

3) ባለሥልጣኑ አዳዲስ የካፒታል ገበያ ምርቶችን፣ አገልግሎቶችን ወይም የንግድ ሞዴሎችን በሙከራ ቁጥጥር ማዕቀፉ መሠረት እንዲሞከሩ ሊፈቅድ ይችላል፤ በዚህ ማዕቀፍ ተፈቅዶላቸው የሚንቀሳቀሱ ተሳታፊዎች በእነዚህ መመሪያዎች ውስጥ በተጠቀሰው መጠን ይህንን መመሪያ ሙሉ በሙሉ ከመከተል ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ።

127. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

128. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ይፋዊ ድህረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ነሃሴ 2017 ዓ.ም

ሃና ተኸልቁ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባልስልጣን ዋና ዳይሬክተር